ሰው እና ሰው

አጫጭር ልብወለድ ታሪኮች

From the Library of
ፍሰሃ አትላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ከፀሐዬ መሠለ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency
112719 30933
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa. Ethiopia

የኮፒራይት ህግ ማስጠንቀቂያ
የሸፍጎ ጌጤ መጽሐፍ ሕገ-ወጥ ኮፒ ማድረግ ወይም ማሰራጨት በሕግ ያስጠይቃል

መጀመሪያ ሕትመት 1985

የሸፋን ስዕል ብርሃነሕይወት ጌታቸው

ማውጫ

ተ.ቁ	ይዘት	ገጽ
1	ሰውና ሰው	5
2	ንቃት—ንቃቃት	28
3	ባለ—ጉዳይ	46
4	የማከያው ጥያቄ	65
5	'ወሬ ኮማሪው'	84
6	የእንጀራ ገመድ	107
7	ጥብቅ መመሪያ	137
8	ሥጋ ብያት	151

ሰውና ሰው

የእጅ መዳፍ በምታክለው ክብ ፊቱ ላይ ተጐልጉለው የሚታዩት የቀያይ ዓይኖቹ ፈጣን እንቅስቃሴ ከጦር ሜዳ ተሸንፈው የተመለሱ ወታደሮቹን የሚገላምጥ ባሻ ያስመስሉታል ። እንደ ጠወለገ የጐመን ቅጠል ዮተዝለፈለፉትን ቀርበታ ጀሮዎቹንና ቀጥ ብሎ የወረደውን ረጅም አፍንጫውን ከስንዝር ቁመቱ ጋር ያመዛዘነ ሳቅ ይመጣበታል ። እስከጀሮዎቹ በሚደርሰው የአፉ ቅድ አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉት ጥርሶቹ ሰነፍ ገበሬ ያቆመውን አጥር በሞዬልነት የሚገልጹ ናቸው ። ገምቦ ሜንቅላቱን ከደቃቃ ሰውነቱ ጋር ያገናኘው አንገቱ ፡ በዳበሳ ካልሆነ ማየት አዳጋች ነው ።

ሲጋራ ከአፉ ፡ ብዕር ከጣቶቹ አይለይም ። የሚጽፈው ጠረጴዛው ላይ ተደፍቶ እንደመሆኑ የሚራመደውም ወደ ኋላው ክፉኛ ተለጥጦ ስለሆነ ኩሩ ያስመስለዋል።

ነጋ ጠባ ፡ ከግራ ከቀኙ ፡ ከፊት ከኋላው ተቆልሎ የሚጠብቀውን ፋይል ሲያገላብጥ ይውላል ። መዝገብ ቤቱ አንዲት መስኮት እንኳ የለውም ። በዚህ ላይ የሚበንበት አቧራ ለጉድ ነው ። እናም አይኖቹ ተዳክመዋል ። ይህን ችግሩን በተደጋጋሚ ለሚመለከታቸው ቢያቀርብም ሲያፈ ዙበት "በእቅድ ተይዟል! ባጀት ሲፈቀድልን እንደሚሆን እናደርግልሃለን" ከማለት ወዲያ የፈየዱለት ነገር የለም ።

አይናቹን ለመርዳት ሲልም የጠርሙስ ቂጥ የመሰለ መነፅር መደንቀር ከጀመረ አሥራ አራት ዓመቾአልፎታል ። ያም ቢሆን በህኪም-የታዘዘለት አይደለም ። ጽሑፍ አጉልቶ ስለሚያሳይ ብቻ የሚች ጐረቤቱን የቁስ ማህደረ ሥላሴን መነፅር ከባለቤታቹው ከወይዘሮ መርአዊት ላይ በሦስት ወራት ክፍያ በሃያ አምስት ብር ገደማ ገዝቶ ይጠቀምበታል ። ታዲያ ይኸው መነፅር ለደከሙት ዓይኖቹ እገዛ ቢያደርግለ ትም ፡ "ዶክተር"ና "ፕሮፌሰር" በተሰኙ የስም ቅጥያዎች የክረረ ፌዝ አስከትሎበታል ።

ለሥራ ሲገባ ከሁሉም ሠራተኛ ቀድሞ ፡ ከሥራ ሲወጣም ከሁሉም ዘግይቶ ነው ፤ ከማንም ጋር ላለመገናኘት። በተለይም በፋይናንስ መምሪያ ውስጥ ያሉት ወጣት ኤክስ ፐርቶች ካገኙት ሠላም አይሰጡትም ።

ዘመናዊ ትምህርት ቤት ገብቶ እውቀት አልቀመሰም ። ለማስረጃነት የሚያገለግለው አንድም ሰርቲፊኬት የለውም ። አፈር ይቅለላቸውና የላሊበላው መሪጌታ ክንፉ ትምህርት ነው አሁን ለሚገኝበት ሥራ ያበቃው ። ድሮ ማንበብና መፃፍ የሚችል ሥራ የማግኘት ዕድሉ ሰፊ በነበረበት ጊዜ ነበር በዚሁ መስሪያ ቤት በተላላኪነት የተቀጠረው ። በተማሪነቱ ዘመን ቅኔ ሳይዘርፍ አልቀረም ፡ ጥሩ ገጣሚ ነው ። አዘውትሮ አይፃፍ እንጂ ፡ አልፎ አልፎም ቢሆን ቆሎ በሚመስለው አጣጣሉ የሚያሰፍራቸውን ግጥሞቹን የሚያነቡለት ያደንቁ ታል ። በተላላኪነት አሥራ አምስት ዓመት ያክል እንደሠራ ፡ የማንበብና የመፃፍ ችሎታው ተመዝኖና የሥራ ትጋቱ ታይቶ በዕድገት ወደ ረዳት መዝገብ ቤት ፀሐፊነት ተዛውሮ

ደመወዙም 127 ብር ደረሰለት ።

ታዲያ ኤክስፐርቶቹ ይህንን እያወቁ "ስኮላር ሞልተ ሃል ወይ ?...መምሪያ ሃላፊ ለመሆን ታጭተሃል...ለሚኒስትር ነት ትታማለህ..." እያሉ ያሾፉበታል ። በሌላ ቀን ደግሞ "ከሹመት ጋር ወደ ሌላ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ልትዛወር ስለሆነ ለመሸኛ ግብዣ አዋጡ እየተባልን ነው... የመዝገብ ቤት ማስትራትህን ያገኘኸው ከኢስት አንግሊያ ዩኒቨርሲቲ ነው ይባላል ።..." በማለት ከላዩ የማይነጥለውን አሮጌ ነፍስ ያማር ኮቱን እየጐተቱ እረፍት ይነሱታል ። ይስቁበታል ። ይቀልዱበታል ። እያከበራቹው ፡ ይዘልፉታል ። እየፈራቹው ፡ ይደፍሩታል ። ከአለባበሱ ጀምሮ እስከ ተፈጥሮው አቃቂር እያወጡ ፡ በአራዳ ቋንቋ እያፈዙ ጊዜ ያሳልፉበታል ። እርሱ ግን ሲታመሙ ይጠይቃቹዋል ። አደጋ ሲደርስባቹውም ከልቡ ያዝንላቹዋል ። በፀሎቱም ምህረት ይለምንላቹዋል ።..

አንድ ቀን ጠዋት ፡ የዕለት ሥራ ስላልነበረው ፡ እንደ ትላንት ዕፎ የጨረሰውን ዶሴ መልሶ ይገለብጣል ። በዚህ ጊዜ የመዝገብ ቤቱ ዋና ሹም ፀሃፊ የከንፈር ቀለም ካልቀባ ሁህ እያለች እየታገለቻው ፡ ሁለት ጀሮዎቹን ወደላይ እየጐተተች ካስካካችበትና ከቀለደችበት በኋላ "አቶ በድሪ በአስቸኳይ ጠርተውሃል" ብላው ፈንዳራ መቀመጫዋን እያነጠረችበትና በሹል ተረከዛም ጫማዋ ወለሉን እያስጮኸ ችበት ወጣች ።

ሰውነቱ በላብ ዝፍቅ አለ ። አቶ በድሪ የሚጠሩት ለቁም ነገር ቢሆንም ብዙ ከቀለዱበት በኋላ ነው ቁምነገሩን

የሚነግሩት ። የሁሉንም ቀልጅ ባይወድም የሳቸው ደግሞ በጣም ያስጠላዋል ። ድርቅ ያለ ቀልድ ነው ። ራሳቸው ተናግረው ከጣራ በላይ ይስቃሉ ።

ላለመሄድ ፈልጎ ነበር ። እምቢተኛነት መሰለው ። የበላይ ዐለቃን ትዕዛዝ ቢጥስ ከሙሴ ህጐች አንዱን እንደጣሰ ይሰማዋል ። የሙሴን ህጐችን በጥብቅ የሚያከብረውን ያ'ክል አለቃውንም ያከብራል ።

በፋይል ከተጨናነቀው ቢሮው ወጥቶ አቶ በድሪ ወደሚገኙበት ክፍል ሲያመራ አራት ወጣት ሠራተኞች አገኙት ።

"ታዲያስ ጓድ ከፍያለው?" አለው ከወጣቶቹ አንዱ ።

"ክብሩ ይስፋ !" ሲል መለሰለት ፡ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ወደላይ እያንጋጠጠ ። ሁሌም ቢሆን እንጋጠ ነውና የሚራመደው ለስሙ ያህል ተንጠራራ እንጂ ተመልካች አልተገነዘበለትም ።

"የት ነህ?"

"አቶ በድሪ ዘንድ !"

ኮቱን ወደኋላ እየጐተቱ ፡ ጭንቅላቱን እየደባበሱ ፡ እየሣቁ ፡ እያውካኩ ለጥቂት ርቀት ካጀቡት በኋላ ተለዩት ።...

የአቶ በድሪን ቢሮ አንኳኩቶ ከፍቶ እንደገባ ከወገቡ ጐንበስ ብሎ እጅ ነሳ ። አቶ በድሪ የወትሮውን ቀልዳቸውን አልወረወሩም ። ድምቡሽ ፊታቸውን አኮሳትረው ፡ እሳት ጐርሰው ነበር የጠበቁት ።

"ቅሌታም ወራዳ ! አንተ በኛ ላይ ልታፌዝ ያምርሃል ? ሜርድ !..." ከፍ ዝቅ አድርገው ሰደቡት ።

"በህግ !... በባንዲራው ! ... በመንግስት አምላክ !..." እላቸው ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ።

"ለበዓል የሚቀርብ ዕውፍ አዘጋጅ ብትባል ይህንን ነው የምትወረውርልን ? ጅላንፍ !"

"በህግ ! በባንዲራው !..." አላቸው እየተንቀጠቀጠ ።

"አንበው እስኪ ጮክ ብለህ !" በማለት አንድ ወረቀት ሊያቀብሉት እጃቸውን ዘረጉ ።

"ጌታዬ ! የፈለጉትን ይጠይቁኝ ።... ግን አይስደቡኝ ... እንደናንተው ሰው ነኝ ። እንደ ሁሉም ሰው በአርአያ ሥላሴ ነው የተፈጠርኩት ። ሰውን መስደብ እኮ..."

አላስጨረሱትም ።

"ይህንን ግጥም ብለህ ለምን ፃፍክ ?"

"የታየኝን ብያለሁ !"

"እንዴት የታየኝን ?" ጣታቸውን ቀሰሩበት ።

"ባይጥምዎት ቀደው አይጥሉትም ? ለርስዎ የሚጥም ልጽፍ ዋስ አልጠራሁ..." አለ ፡ እንዴት እንደሚያስረዳ እየጨነቀው ።

"ላንብልህ አድምጥ !" አሉና በረጅሙ ተነፈሱ ።

በግራ እጃቸው የግራ አገጫቸውን ደግፈው ፡ በቀኝ እጃቸው ወረቀቱን ራቅ አድርገው ይዘው ማንበብ ጀመሩ ።

‘‘ዝምታ – ዕድሜ ቀጥል መላ’’

ከት ከት ብሎ ሳቀ – የባህር ማሽላ

....

– የአበው ብሂል

– ማን ይቅር ሊል?

ጥንትም – ያው ነበር ደንቡ ፣

– አለመድረሻ መጋለቡ ።

እኔ እኔ እያሉ ከተሞላቀቁ ፣

መች ይቀራል – ትንቅንቁ!

አንቺስ ብትሆኝ!

ማነሽ ቢሉሽ ... ማነኝ ልትይ?

የዕለት እንጀራሽን ... ስታበስይ፣

አበባ ተገኘሽና ... እሾህ ውስጥሽ!

በይሁን ይሁን ... ሆታ ሲወርድልሽ ፣

ባንቺ ያዘኑ ... “ኤዲያ !” ያሉሽ

“አበባየ ሆይ – ለምለም” ሲሉሽ ፣

– ቅር የማይልሽ!

ሆድ ለሆድ!...

ለማታውቂን – ለምናውቅሽ ፣

ቅምጥሎችሽ – እንዳሻቸው ፣

“እኛ ! እኛ!” – ለራሳቸው ፣

ሲሉን – ዝም አልሻቸው?

“አበባየ ሆይ ...!” – እስቲ አድምጪን ፣

“ሆ ብለን መጣን...! – ሆ!” ብለን ፣

– ስንዘፍንልሽ ፣

ምን ሊሉን ነው – ቅልቦችሽ?

— ጦር ሊሰብቁብን

— ስድብ ሊያወርዱብን ?

– ጠይቂያቸው!

– ዝም አትበይ – ከለላ ጐጆአቸው ።

* * *

አንበው እንደጨረሱ ዓይኖቻቸውን አጉረጠረጡበት ።

“ታዲያስ! ማን ፃፈው?” አሉት

“እኔ ... እ...እ...” ለጋ ቅቤ እንዳላሉት ሀፃን ተንተባተበ ።

“ትርጉሙ ምንድነው? ምን ግንኙነት አለው ከበዓሉ?”

የሚመልሰው ጠፋው ። ግጥሙን ዕር ሲሰጥ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ይመጣብኛል የሚል ግምት አልነበረውም ። ቁጭት አደረበት ። የዛሬን ብቻ መውጪያ እንዲያገኝ ፈጣሪውን ተማፀነ ።

“ትርጉሙ ምንድነው? አትናገርም?” አምባረቁበት ።

“ትርጉም የለውም ብለው ምነው አይጥሉትም?”

“ወረቀቱ አይጣልም! ማስረጃ ነው ።”

“አሁን ምን ፍጠር ይሉኛል?”

“ፖለቲካ ጀመርክ አይደል? ቆሎ ያረረብህ የዚች ዓለም

መናጢ ድሃ መሆንክን ዘንግቲህ ... አንተ ብሎ ባለቅኔ!... ቆይ!...''

''ኧረ! ... በስመአብ ይበሉ ጌታየ!... ደግም አልተና ገሩ። የምን ፖለቲካ አመጡ! ስብሃት ለአብ...'' አማተበ ።

''ጌት አውት!'' አሉት ጠረጴዛውን በቡጢ ደ. እያደ ረጉ ።

''ኧረ በቅዱስ ላሊቢላ!''

''ውጣ!''

ቆሌው እንደተገፈፈ አቀርቅሮ ወጣ ።...

* * *

''የደመወዝ ዕድገት አገኘሁ እንዳትለኝ!'' በማለት ገና ከመግባቱ ፀሐፊዋ ለከፋዋን ጀመረችው ።

ፋይሎች ከዋጡት ጠረጴዛው አጠገብ የተቀመጠው ፍዝዝ እንዳለ ነበር ። መንፈሱ እንኳ ሁልግዜም አንደቀዘቀዘ ነው ። ጀምሮት የነበረውን ዕሁፍ ግልበጣ ወደጐን ገፋ አድርጐ አመት ሙሉ ከደመወዙ አጠረቃቅሞ የገዛውን አሮጌ ሮመር ሰዓት ተመለከተ ። ስድስት ሰዓት ይላል ።

ለምሳ የመውጪያ ሰዓት ቢሆንም ዘግይቶ መውጣት ነበረበት ። ስድስት ከሩብ ላይ ግስላ ሲጋራውን ለኩሶ ፡ በራ ሜንቅላቱ ላይ ብን ብን የሚሉ ፀጉሮቹን እየደባበሰ ወደ ቤቱ ገሠገሠ ፡ ለምሳ ።

ምግብ የሚያዘጋጁለት ሴትዮ ቤቱንም ያከራዩት ናቸው ። እንደፈለጉ ያዙበታል ። እፍ ቢሉት የሚበር ዓይነት እንጀራ በድቁስ አቅርበውለት አንድ ብር ያስመዘግቡታል ።

ቃል አይመልስላቸውም ። በሃያ ብር የተከራያት ጠባብ ክፍልም ብትሆን የሳቸው ናት ማለት ይቻላል ፡ የእትየ ወርቄ። ከአገር ቤት እንግዶች ሲመጡባቸው ፈቃድ ሳይጠይቁት በዚያች ጠባብ ክፍል ያሰፍሩበታል ።

''ምሣ'ትየ ወርቄ!'' አላቸው ፡ ርጥብ እጁን አያሻሸ ።

''ቀስ! ምነው... ምን መጣ?''

ቂጣ አይሉት እንጀራ ፡ የተሰነጣጠቀ ጉድ ፡ ባልፈላ ሽሮ አቀረቡለት ። ወጉ እንዳይቀርም የወይፈን ቀንድ የሚያክል ቃሪያም ሰሀኑ ላይ አጋድመውለታል ። የከርስ ነገር ነውና ከርሱን መሙላት ጀመረ ።...

ሰዓቱን ሲመለከት ስድስት ተኩል ይላል ። መስሪያ ቤቱ ለመድረስ በቂ ግዜ እንዳለው እያሰበ እጆቹን ታጠበና ግድግዳው ላይ በተሰቀለው የአሮጌ ቀሚስ ትልታይ የረጠቡ እጆቹን አደራረቀ ።

ግስላ ሲጋራውን የወይራ ፍም ላይ ለኩሶ አረፍ አለ ፡ መዘዝ እያስከተለበት ያለውን ግጥም እያሰበ ።

ከቀረበለት ምግብ ምንም ሳያስተርፍ ጥርግ ማድረጉን የተመለከቱት'ትየ ወርቄ እየተቆናጠሩ ሳህኑን አንስተው ወደ ጓዳ ገቡ ።...

''አንተ ፡ ምን የሚሉት ትምባሆ ነው ደግሞ የዛሬው?'' አፋቸውንና አፍንጫቸውን በግራ እጃቸው አፍነው ጠየቁት።

''እ... ያው የወትሮው ነዋ!''

አቋረጡትና ''ትምባሆውን ራስህ ነህ የምትሠራው ልበል? ምናለ እንደሰዎቹ ጥሩውን አይተህ ብትገዛ!?''

''ገንዘብ ያስፈልጋል!... እ... ዋጋው ይለያይል ...''

አላቸው ጢሱን እፍ እያለ ።

“ማን ግድ አለህ!ኤአትተወውም?”

“ሲጋራ ከመተው ምግብ መተው ይሻላል!”

“ለነገሩማ የቁስ ልጅ ነበርኩ ትል የለም? ሃጢያት ነው!”

“ጓደኛ ነዋ! ጓደኛ አበላሽኝ ።… ገና አዲስ አበባ እንደገባንና አሜሪካን ግቢ እንደሠፈርን እ…ራብ ያስታግሳል እየተባለ.. ለመድነው!”

ሰዓቱን በድጋሚ ተመለከተ ። አውንም ስድስት ተኩል! ሰዓቱ መቆሚ ስለገባው በድንጋጤ ፊቱ ባንዴ ልውጥውጥ አለ ። ወደ ሥራው ከማንም በፊት ቀድሞ መግባት ነበረ በት ።…

በፍጥነት እየተራመደ መስሪያ ቤቱ ሲደርስ ሰባት ከሩብ ሆኗል ። ደግነቱ ከሚቀልዱበት ባልደረባዎቹ ማንም አላጋጠመውም ። ቀድመውት ገብተዋል ። ከአንድ የፈረንጅ ቡችላ ጋር እየተዛለሉ የሚያውካኩት ዘበኞች ብቻ ነበሩ ።

ስምንት ሰዓት ላይ በአዲስ ካኪ ላሪያን ኮትና ሱሪ የተለበጠ ተላላኪ አንድ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ ለት ። ወረቀቱ የያዘው መልዕክት “የአስተዳደር መምሪያ ባልደረባ የሆኑት ወይዘሪት ሶፊያ በዝውውር ወደ አሰብ ስለሚሄዱ ለመሸኛ ግብዣ የተቻላችሁን ያክል ፈርሙ!” የሚል ነበር ። አሥር የሚሆኑ ሠራተኞች ከስማቸው ፊት ለፊት የገንዘብ መጠንና ፊርማቸውን አስፍረዋል ። ሰላሳ… ሃያ… አሥራ አምስት… አሥር ፣ … ስምንት…፣…

እዚያ ላይ ከፍያለው በጣም ጨነቀው ። ለእስከዛሬው

ግድ አልነበረውም ። የመዋጮ መፈረሚያ ወረቀት ከቢሮ ቢሮ ሲዞር ውሎ እሱ ወደሚገኝበት መዝገብ ቤት መድረሱ የማይቀር ቢሆንም አንድ ግዜ ብቻ አዲሱን የአስተዳደር መምሪያ ሃላፊ አቶ ስመኝን ለመቀበል ለተደረገ ግብዣ አንድ ብር ፈርሚል ። ሌላ የሚያስታውሰው የለም ።

የአሁኑ አሳሰበው ። ሶፊያን በጣም ይወዳታል ። እንደሌሎቹ አትዘልፈውም ። አትቀልድበትም ። ብትሰማ እንኳ በቀልዱ እጇን አታስገባም ። መግቢያ ፣ መውጪያ በሮች ላይ እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገናኙ ሰላምታ ታቀርብለ ታለች ፣ ‘ጋሼ ከፍያለው…’ እያለች ። ከዚህም ሌላ በብርድ በሽታ ታሞ በነበረበት ግዜ ሃያ ብር ሰጥታዋለች ። ስለዚህ ውለታ አለበት ። በሶፊያ የመሸኛ ግብዣ ላይ የተቻለውን ያክል አለመፈረምና በሌላ ግዜ እንደሚያደርገው ከግብዣው ቢቀር ውለታ – ቢስነት መስሎ ታየው ።

“ፈጠን በል እንጂ! ሃውልት’ኮ አይደለሁም!” ሲል ቁልቁል የሚመለከተው ተላላኪ አፈጠጠበት ።

“ይቅርታ ወንድሜ!እ… ሰዎች ስንባል ማሰብ አለ ብን። እ…”

“እፋ!” ተላላኪው የተሰላቸ መሰለ ።

“ብዙ የቆምክ አይመስለኝም ። እ… አትቸኩል ። እ…” ማጅራቱን እየፈተገ አንድ ብር ከሃምሳ መዘገበና ፈረመ ።

ተላላኪው የመጣበትን ሣቅ ለመመለስ አፉን በእጁ አድርጐ ፣ ወረቀቱን ይዞ ወጣ ።

የግብዣውን ዕለት ላለመርሳት በቁራጭ ወረቀት ‘ሰኔ–

2'ብሎ ፃፈና ግድግዳው ላይ ለጠፈው ። ሁለት ቀን ብቻ ነበር የቀረው ።

ለግብጥው ዕለት ለእንደሱ ዓይነት ድሃ የአለባበስ ጉዳይ ትልቅ ፈተና መሆኑን ያውቃል ። አሁን የቸገረው የልብስ ጉዳይ አልነበረም ። ያለውን ያጥበዋል ። አብዛኞቹ ልብሶቹ ላዩ ላይ ያለቁ ቢሆኑም አማራጭ አልነበረውም ። አዲስ ልብስ ለመግዛት አቅም የለውም ። ለልብስ መግዣ ልበደር ቢልም ፡ ዕዳውን ከፍሎ ለመጨረስ ዓመታት ያስፈልጉት ይሆናል ። በዚያ ላይ የሶስት ወር የቤት ኪራይ 'ትየ ወርቁ ይጠብቁበታል ።

የቸገረው የጫማ ጉዳይ ነበር ። የእስከዛሬው ጫማው ባለመስኮቱ የገመማ ጫማ ነው ። አልሳካለት ብሎት እንጂ ሊቀይረው ካሰበ ብዙ ጊዜ ሆኖታል ። በዚህ ጫማ በርካታ ፌዞች ደርሰውበታል ። ሌላ ቀርቶ ፡ 'ህጋዊ–ወያኔ' ተብሎበ ታል ።

ከሥራ ባልደረቦቹ ብድር እንዳይጠይቅ ፡ ሲያገኙት ከማፈዝ አልፈው ለሱ ችግር ደንታ እንደሌላቸው ያውቃል ። የመስሪያ ቤቱ የቁጠባና የብድር ማህበር ታወሰው ። የማህበሩ አባልና መስራችም ነው ። ግን የማህበሩ ፀሃፊ ወንድይራድ በሱ ላይ ከሚያፈዙት አንዱና ዋነኛው በመሆኑ ሊያነጋግረው አልፈለገም ።

አውጥቶ፡ አውርዶ አማራጮቹን ሁሉ ወረቀት ላይ ካሠፈረ በኋላ በምክንያት እያስደገፈ፡ አማራጭ ሊሆኑ የማይችሉትን ሰረዛቸው። የሚያዋጣው የቁጠባና የብድሩ ማህበር ብቻ መሆኑን ወሰነና አንድ በቅጡ ያልተፃፈ ማመል

ከቻ ይዞ ወደ ቢሮ ቁጥር 128 ሄደ። የቢሮውን በር አንኳኩቶ ሲገባ ፡ የማህበሩ ፀሐፊ ውንድይራድ አንድ የውጭ መጽሔት እያገላበጠና ሲጋራ እያቦነነ አገኘው።

ወንድይራድ ከፍያለውን እንዳየ፡ ለፈገግ በቋመጠ አቀራረብ ከተቀመጠበት ተሽከርካሪ ወንበር ብድግ ብሎ ተቀበለው። ጠረጴዛው ላይ የነበሩትን መፃህፍት፡ ወረቀቶች፡ ...ወደ ግራ ወደ ቀኝ እየገፋ መልክ ካስያዘ በኋላ "ሻይ ወይስ ቡና?" አለው፡ አለቃው እንደመጣበት ሁሉ።

ከፍያለው ምንም መልስ ሳይሰጥ ወንበር ስቦ ተቀመጠና ማመልከቻውን ሰጠው።

"ምን ችግር ገጥሞህ ነው?" አለው ወንድይራድ።

"ችግሩ የግሌ ነው። ስለእግዜር ብለህ ብድር ብትፈቅድልኝ። እ... የመቶ ብር ብድር...ሁለተኛ አላስቸግርም። እ...የማህበሩ አባል ነኝ። እ..." እጆቹን እያወናጨፈ ለማስረዳት ሞከረ።

"ዬክ ልትገዛ ነው ? ቪዲዮ እያሳየህ ከመንደር ልጆች ገንዘብ ልትገፍ ! ሃሃሃ ... ! የታንሳ ሙዚቃና ቪዲዮ መደብር ቋሚ የቪዲዮ ካሴት ደምበኛ ለመሆን እንዳቀድክ ሰምቻለሁ። ግን ለምን የመዝገብ ቤት ትምህርት ተቋም አትከፍትም? ሌክቸረር ትሆናለህ። ... " የመጨረሻው የውስጥ ጥርሱ እስኪታይ ድረስ ሣቁን ለቀቀው፡ ሃሃሃ...!

"ስለእግዜር ብለህ !መቶ ብር ብቻ ...የማህበሩ መስ

ራች ነኝ።እ…አንተ እንኳ ከመጣህ ሶስት ዓመትህ ነው። እ…እና ባክህ …”ማጅራቱን ቆከከ። →

“ሂሳብ እያደረግን ስለሆነ ካለፈው ሰኞ ጀምረን ብድር ከልከለናል። እና አይቻልም” በማለት ወሸመጡን ቆረጠ በት፡ የግንውን ጢስ እና፡ እያለበትና መተርከሻው ላይ እያወደመ።

የወንድይራድ የሲጋራ ጢስ፡ ሱሱን ቀሰቀሰበትና ከፍ ያለው ከውስጥ ኪሱ ግስላ ሲጋራ አወጣ።

”ኣ!ኣ!… እሱን ተወው…! አስም ስላለብኝ ነው” አለና ወንድይራድ አንድ ሮዝማን ሲጋራ ከፓኬቱ አውጥቶ እጁን ዘረጋለት።

“እግዜር ይስጥልኝ! ስወጣ የራሴን አጨሳለሁ። እና የብድሩ ጉዳይ…እ…”

“እሱንማ ነገርኩህ! በቃ።”

“ባስቀይምህ ይቅርታ አድርግልኝና ትላንት ወዲያ ለአቶ ስብሃት?….ማለቴ ለጓድ ስብሃት ፈቅዳችኋል። እ…”

“ያማ ስፔሻል ኬዝ ነው!”

“ምን አልከኝ?”

“ስፔሻል ሚንስ ‘ልዩ’ ልዩ ችግር..!”

“ልዩ ችግር? አየህ ወንድይራድ!” ተነስቶ ቆመ። “ችግር ለተሸከመው ሁሉ ያው ችግር ነው። እ…የችግር ልዩ የለውም። እ…አጣዳፊ ችግር፡ ቀላል ችግር ሊኖር ይችላል። ግን ለሁሉም ችግር፡ ችግር ነው። ደግሞ እ…”

ወንድይራድ አቋረጠውና “ችግርን በተመለከተ አንድ ሪሰርች አቅርበህ ማሳተም ነው። ሃ…ሃ….ሃ…!ይቺን ካደርግ ሽማ ከፌ! የጠቅላይ ሚኒስትርነት…ቢያንስ ደግሞ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርነትሽን ቀጨም አደረግሽ ማለት ነው ። ሃ…ሃ…ሃ…!”

እምባ የተናነቀው ከፍያለው “ ከማህበሩ አባልነት ሰርዙኝና ያዋጣውት ይመለስልኝ። እ…ችግር ነው። ምን ይደረግ? ” አለ።

“ከመስከረም ሁለት በኋላ ጠይቀን” አለው ሌላ ሮዝ ማን ሲጋራ እየለኮሰ።…

ከፍያለው ንዴትና ብስጭት እየተሰማው፡ እምባ እየተ ናነቀው በመጣበት እግሩ ተመልሶ ወጣና ወደ ሚኒስትሩ ቢሮ ሄደ።

ሚኒስትሩን ለማግኘት እንደሚፈልግ የፅህፈት መኪና ታቅፋ ሹራብ የምትሠራውን ፀሐፊ ቢጠይቃትም “ስብሰባ ይዘዋል !” በማለት እንቅፋት ሆነችበት ። ሚኒስትሩ ግን ስብሰባ ላይ አልነበሩም ።

ግማሽ ሰዓት ያክል ጠበቀ።…

“እባክሽ ንገሪልኝ! ሰዎች መረዳዳት አለብን! …እ…” አላት እያስተዛዘነ።

“ኤጭ!” አለችና ፀሃፊዋ የስልኩን እጀታ አንስታ ቁጥሮችን ጠቅ ጠቅ አደረገች። ጥቂት ከተነጋገረች በኋላ

"ግባ!" አለችው።

የሚኒስትሩን ቢሮ በር ከፍቶ ሲገባ ሆዱን ባር ባር አለው። ሴተኛ —አዳሪ ቤት የገባ ጀማሪ ጎረምሳ ይመስል ፍርሃት ወረረው። የሚኒስትሩ ቢሮ ውበትና ወለሉ ላይ የተነጠፈው ቀይ የፋርስ ምንጣፍ፣ እንዲሁም የሚያብረቀርቅ ቀው ጠረጴዛና የሚኒስትሩ የተቆጣ ፊት፣ ይህ ሁሉ ተዳምሮ ፀፀት አሳደረበት። "በቀረብኝ!" አለ በሆዱ።

"ጌታየ እኔ እ…ችግር አለብኝ። እ…የቁጠባና የብድር ማህበሩን እ … ብድር ጠየቅኩ ። እ … ግን ጓድ ወንድይራድ እ…" መንተባተቡ ሹራቩን ባሰበት ።

"ምንድነህ?" ብለው ሚኒስትሩ ድንገት ሲባርቁበት አንገቱን ደፋ።

"ጌታየ እኔ በዚህ መስሪያ ቤት እ…ለረዥም ዓመታት እ…በታማኝነት…"

"ውጣ ባክህ! ክፉዚ!… የብድር ይግባኝ ሰሚ መሰል ኩት እንዴ ? …" አሉና ሚኒስትሩ በብስጭት ቡጢ ጨበጡበት ።

ከዓይኖቹ ፍልቅ ያለውን እምባ እየጠረገ ተመልሶ ወጣ።

ሌላ አማራጭ ብልጭ አለለት። በአስተዳደራዊ ሥራ አንጋፋነታቸው፡ ባለጉዳይን አዝናንተው ችግሩን አድምጠው ፡ ከቻለ ችግሩን ፈተው ፡ ካልቻሉ ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ጠቁመው በማስተናገድ የሚታወቁት የአስተዳደር

መምሪያው ሃላፊ አቶ ስመኝ፡ ከፍያለውን ፈገግ ብለው ነበር የተቀበሉት። ፈገግታ አይለያቸውም።

"አቶ ከፍያለው! ዛሬ ምን እግር ጣለህ?" አሉት እንዲቀመጥ ባዶ ወንበር እያመለከቱት ።

አንገቱን ቁልቁል አጥፎ ዝም።

"በል እንጂ!" አሁንም ፈገግ እያሉ ።

ከነተበው ነፍስ—ይማር ኩቱ የውስጥ ኪስ ለወንድይራድ ሰጥቶት የነበረውን ማመልከቻ አውጥቶ አቀበላቸው።

ማመልከቻውን እያነበቡ፡ ጭንቅላታቸውን ግራ ቀኝ እያወዛወዙ፣ ከንፈራቸውን መጠጡና "ከዚያስ?" አሉት።

ትከሻውን ሽቅብ መታ።

ማስታወሻቸውን ገልጠው ከፃፉ በኋላ አንድ ባለ ሃምሳ ብር ኖት ከመሳቢያቸው አውጥተው ሰጡት። ጉልበታቸውን ሊስም አጎንብሶ ሲጠጋቸውም "አይገባም! ነውር ነው!" ብለው ከለከሉት።…

ምሽት ላይ ከፍያለው በእድሳት የተቃና አሮጌ ቆዳ ጫማ በአሥራ ሁለት ብር ገዝቶ ወደ ቤቱ ገባና እግሮቹን አጥቦ ካደራረቀ በኋላ ለካው። ወዲያና ወዲህ እያለ ሞከረው። የጫማውን ጫፍ በጣቶቹ እየነካካ፡ ያረጀውን የጣውላ ወለል እየተመተመ ፈገግ አለ።

"ጫማ ገዛህ እንዴ ?" አሉት 'ትዬ ወርቁ ማማሰያቸውን ከሚንተከተከው ዶኪ አውጥተው መዳፋቸውን በማስነካት እየቀመሱ ።

"ከመስሪያ ቤት ነው የተሰጠን። እ…ለሁላችን/!" ፈገግ እያለ። ለ'ትየ ወርቁ ያዘጋጃት መልስ ነበረች። ይህቺ ውሸት ምናልባት በህይወቱ የመጀመሪያ ልትሆን ትችላለች።

"ወታደር መሆንህ ነው ? ወሽካታ ! ቢሻው ቀበሌ ፡ ቢሻው ማዘጋጃ ቤት ይስጥህ። እኔ የምፈልገው ገንዘቤን ነው። ገንዘቤን ጠብ አድርግ! አለበለዚያ ጉድ ይፈላል።"

ሰሞኑን አንድ የቀበሌ ጥበቃ—ጓድ በውሽማነት ስለያዛቸው የተጣሉትን ሁሉ ' ጉድ ይፈላል! ' ማለት ጀምረዋል። ከፍያለውም ምን ማለታቸው እንደሆነ ገብቶታል።

"ነግሬሃለሁ! ኋላ እንዳታዝንብኝ" አሉትና እንደ ሀረር ሰንጋ የሚያረግደው ዳሌያቸውን እያወዛወዙ ወጡ።… እሁድ በማለዳ ከመኝታው ተነስቶ ቀጨኔ መድሃኔዓለም ቤተክርስትያንን ተሳልሞ ከተመለሰ በኋላ አዲሱ ጫማ ውንና ቀዳዳዎቹ ተጠግነው፣ ታጥፎ የተተኮሰ ሱሪውን አጠለቀ። ሱሪው ትንሽ ቢያጥረውም አዲሱ ጫማውን በደንብ የሚያሳይለት በመሆኑ አልከፋውም።

አንድ የተበጣጠሰ ካናቴራ ለብሶ፣ በላዩ ላይ የመጀመሪያ ቀለማቸውን ለመለየት አዳጋች የሆኑ ሁለት ሽሚዞችን ደረበ። ታጥቦ፣ ተተኩሶ፣ በጋዜጣ ተጠቅልሎ ከተቀመጠ ስድስት ወር የሚደፍነውን ጥቁር ነፍስ— ይማር ኮት ከትልቁ ካርቶን አውጥቶ ለበሰና የሠፈሩ የዕድር ዳኛ የሰጡትን የፍየል ምላስ የምታክል ዝንጉርጉር ክራቫት በአንገቱ አጠለቃት።

በተሰነጣጠቀችው መስተዋት ራሱን ሲያይ ከልቡ ሳቀ። የኋላውንም፣ የፊቱንም እየተዟዟረ ካስተዋለ በኋላ፣ በራ ሞንቅላቱ ላይ አልፎ አልፎ የበቀሉትን ፀጉሮቹን ወደኋላ አስተኛቸው።

በህይወቱ እንደዚህ ሽክ ብሎ አያውቅም። በዚያ ቀንም የ'ትየ ወርቁ ቂጣና ያልፈላ ዶኪ አላስኘውም።

በአዲሱ ተረከዛማ ጫማው አሮጌውን የጣውላ ወለል እያንሳጠጠ ሲወጣ "ምሣ አትበላም እንዴ ?" አሉት አለባበሱን እያስተዋሉና የሽሙጥ እያዩት።

"ዛሬ ምሣ አልበላም። ምክንያቱም እ…"

"ታዲያ ማን ሊበላልህ ነው! የማትበላ ከሆነ ለምን አሰራኸኝ?"

"እንዴት መሰለዎት'ትየ ወርቄ ! ዛሬ ግብጣ ስላለ …"

"ድንቄም!" አሉና ቀጭን የሽሙጥ ሣቅ ስቀው "አንተም ተጋበዝክ! አልበላም ካልክ እኔ ድሃዋ አልክስርም። ሂሳቤን ትመዘግባለህ። አለበለዚያ ዋ!"

እሱም ምልልስ አልፈለገም። መዝግቦላቸው ወደ ግብጣው ቦታ ሄደ። ግብጣው ቅድስት ማርያም ጀርባ ከሚገኘው ትልቅ ግቢ ነበር። በሶፊያ ቤት።

የቤቱ ትልቅነትና ዘመናዊነት ፣ የግቢው ማማር አስደነገጠው። የድግሱን ሁኔታ ማመን አቃተው። ካሰበው በላይ ሆነበት። እሱ የሚያውቀው ድግስ፣ ማህበር፣ ዝክር፣ ፍታት፣ ክርስትና፣ …በእነዚህ ላይ ደግሞሁለት ወይም ሶስት ዓይነት

ወጥ ቀምሶ፡ ሶስት ብርጭቆ ያክል ጠላ አጋብቶ ከመመለስ ውጪ የሞቀና የደመቀ ሁኔታ ገጥሞት አያውቅም።

የሙዚቃው ጩኸት፡ የአስተናጋጆች ሽርጉድና ቅጥየለሽ ውካታ፡የቢራ ጠርሙሱ ኳኳታ፡ የሲጋራው ጢስ ትንፋሽ፡ የምግቡ ሽታ… ሁሉ ለጉድ ነው።

ከፍ ያለው አንድ ወንበር ስቦ ተቀመጠና ዙሪያ ገባውን አማተረ። አስተናጋጇቹ ያመጡለትን ምግብ ጥርግ አድርጎ ከበላ በኋላ፡ በሁለት ሰዎች ግራና ቀኝ ተይዞ ከሚዞረው የቢራ ሣጥን ላይ አንድ ጠርሙስ አንስቶ አስከፈተና ተጎነጨ። ግስላ ሲጋራውን አውጥቶ ለኮሰ። አንዴ ማግ አድርጎ፡ ጢሱን በአፍንጫውና በአፉ ሲያወጣ አጠገቡ የነበረው ወጣት የቢራ ጠርሙሱን እንጠልጥሎ ከፍያለውን እየገላመጠ ፊት ለፊት ከነበሩት ሴቶች ጋር ተቀላቀለ።…

ግብግቡ መልኩን እየቀየረ መምጣት ጀመረ። ትርምስ በዛ። አሥር የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች የቢራ ጠርሙሳቸውን እንደያዙ፡ ከመጠን በላይ በሚጮኸው የፈረንጅ ሙዚቃ መውረግረግ ጀመሩ። ከፍያለው አፉን ከፍቶ ይመለከታቸዋል። በተለይም የሴቶቹ እንደዚያ መሆን አላስደሰተውም።…

ደንገዝገዝ ማለት ሲጀምር ተስተናጋጇ ሁሉ ለየለት። አፍ ለአፍ ገጥሞ የሚያወራው ፡ ቀሚስ ገልቦ ጭን የሚያሸው፡ ከንፈር ለከንፈር ገጥመው የሚሳሳሙትን፡ ተቃቅፈው በሰመመን እንደ ቅቤ የሚቀልጡትን ሲያይ ላብ ላብ አለው። የጠጣው አራት ጠርሙስ ቢራም ናላውን አዞረው። አቅለሽለሸው። ሞቅ እያለው በሄደ ቁጥር ምክንያቱን ሳያውቀው ነገር ነገር አለው።

በመካከሉ "ሃሎ ሌዲስ ኤንድ ጀንትልሜን! ሃሎ ሌዲስ ኤንድ ጀንትልሜን!" የሚል ድምፅ በጭብጨባ ታጅቦ ሲያስተጋባ ሁሉም ፀጥ አለ። የቆመው እንደቆመ፡ የተቀመጠው በተቀመጠበት ሆኖ ወደሚያዜበጭበው ወጣት አፈጠጠ ።

"ሰላም ለሁላችን ! ተዝናኑ ተጫወቱ ! ኢንጆይ ዩር ሰል ቭስ! ወይዘሪት ሶፊያ ሁለተ ጠርሙስ ስኮች ውስኪ ጀባ ስትለን አምስት ባልደረቦቿ ደግሞ አምስት ጠርሙስ ቲቸርስ ዊስኪ አቅርበዋል። እሸር ናይት ነው ዳንሱ!እኬ! …"

ንግግሩን ሳይጨርስ ተስተናጋጇ ጭብጨባውን አቀለጠው ። ፀጥ ብሎ የነበረው ሙዚቃ ወደነበረበት ተመለሰ ። …

ከፍያለው ግን ብዥ ብዥ አለበት። የሆነ ስሜት መንፈሱን አወከው ። መላው ተስተናጋጇ ፀጥ ብሎ እንዲያደምጥ በማድረግ "አሁን እኔ ወንድማችሁ አያደለሁም?" ሊል ፈለገ። ምን እንደገፋፋው አያውቅም።

ለዚሁ ዓላማ ከወንበሩ ለመነሣት ሲሞክር ተንገዳገደና ተመልሶ ዘጭ አለ። የሚያየው ሁሉ ሀልም መሰለው። 'መሬት ትዞራለች የሚባለው ሃቅ ነው' አለ ፡ በልቡ ።

ያለ የሌለ ሃይሉን አሟጦ ተነሳና እየተንገዳገደ ወደ ሽንት ቤት ሲሄድ "አሲስታንት ፕሮፌሰር ከፍያለው ደመና...ጀኔራል ዳይሬክተር አቭ ኢትዮጲያን..." አለው ወንድይራድ፤ በተሳሰረ አንደበት። እዚያ የነበረ ሁሉ ሣቀ። ወንድይራድ ለማለት የፈለገውን በሳቅ አቋረጠው።

በቦዙ ዓይኖቹና በአፍንጫው እየተመራ ወደ ሽንት ቤት ሲሮጥ በገጠመው ነገር አፉን ከፍቶ ቀረ። ያየውን ማመን አቃተው። ከመስሪያ ቤቱ ባልደረቦች ጌድዎንና ማርታ ጨለማን ተገን አድርገው መርፌና ክር ሆነዋል።

"በስመአብ ወልድ !" የሚል ቃል አመለጠው። በድን ጋጤ ስካሩ ለቀቀው። በቀጥታ ግቢውን ለቆ ወጣ።

የቀጨኔ መንገድ ጭር ብሏል። አልፎ አልፎ ብቻ መኪናዎች ሽር እያሉ ያልፋሉ። ከዚያ ውጪ የሚንቀሳቀስ ነገር አይታይም።

ዋናውን መንገድ እየለቀቀ ፣ ወደ ቤቱ የሚያደርሰውን ኮረኮንቻማ መንገድ ሲያያዝ ፍርሃት በመላ አካላቱ ተሰራጨ በትና የሚረግጠውን ሳያስተውል ሩጫ ጀመረ። ግራና ቀኝ፣ ፊትና ኋላ እየተገላመጠ መንገዱን ቀጠለ። እህል ውሃ የሚያሰኝ ድንጋይ አንስቶ ዙሪያ ገባውን እየቃኘ ቢገሠግሥም ልቡ ድው ድው እያለች ፈርታ ታስፈራዋለች።

ድልድዩን እንደተሻገረ አንዳች ነገር ማጅራቱ ላይ አረፈበት። ከዚያ በኋላ ትንፋሹ አጠረ። የልቡ ምትም ቀነሰ።...

ለምን ያህል ግዜ እንዲያ ሆኖ እንደቆየ ባይታወቀውም ዓይኖቹን ገልጦ አካባቢውን ሲቃኝ ያለበትን ማወቅ ተሳነው። ጥቅጥቅ ጨለማ ከቦታል። የነፍሳት ሲርሲርታ ይሰማል። የጅብ ጩኸት አካባቢውን ያምሰዋል።

በዚህ ጥቅጥቅ ጨለማ አፍጦ ዙሪያውን ቃኘ ። አካላቱን ቢዳስስ ልብሱ በሙሉ ተወስዷል። የቀረው ቢኖር የታጠቀው አሮጌ የውስጥ ሱሪው፡ የተቦጫጨቀ ካኒተራውና አንድ ሽሚዝ ብቻ ነበር። ሃያ ብር ገደማ ያስቀመጠባት ጥቁሩ ኑፍስ ይማር ኮቱ፡ ሮመር ሰዓቱ፡ ጫማው...ሁሉም የሉም። መነፅሩን እንኳ አላስቀሩለትም።

እየተንገዳገደ ቤቱ ደርሶ በዝግታ ጓዳውን ከፍቶ ገባ። 'ትየ ወርቁ ተኝተዋል። የጠፍር አልጋው ላይ በደረቱ ድፍት አለ።

በማግሥቱ ሥራ አልገባም። ፈቃድም አልጠየቀም። መጥቶ የጠየቀውም አልነበረም ፣ ከ'ትየ ወርቁ በቀር ፣ ለዚያውም ለሂሣባቸው ሲሉ።

የጠፍር አልጋው ላይ ቃዩፍቶ ውሎ ቀትር ላይ አይኖቹን ከፈት ሲያደርግ ሣንቲሞች የሚያጠራቅምባት ትንሿ ሣጥኑ ተሰባብራለች። በመኝታ ክፍሉ ውስጥ የነበረው ኮተቱ ሁሉ የለም። 'ትየ ወርቁ እንደተካሱበት ለማወቅ ግዜ አልፈጀበትም። ደግነቱ አላባረሩትም። ትርፍራፊ ይጥሉለታል። ውሃ ያቀብሉታል።

ለሁለት ሣምንት ያክል ከማቀቀ በኋላ ፣ ከሙታን ሠፈር መቃብሩን ፈንቅሎ የወጣ ጣረሞት መስሎ በምርኩዝ እየተ

ረዳ ይሠራበት ወደነበረው መስሪያ ቤት ሊያዘግም ሞከረ። ግን ከአሮር ጉዞ በኋላ አቃተው። ሌላ የሚሄድበት ቦታም አልነበረውም። በአቅራቢያው ከሚገኝ አጥር ሥር ተቀመጠና እጆቹን ዘረጋ፡ ለልመና።

ሐምሌ 1981·
ለመምህር አቢይ የሻነው
ጉድጉዳ

ንቃት...ንቃቃት

ሜርምትምቱ በድንጋይ ተቃንቶ "ዘመናዊ ፀጉር አስተካካይ" የሚል ጽሑፍ ባለተመጣጠኑ ፊደላት የሰፈሩበት ቆርቆሮ የተንጠላጠለባት ፡ የማዘጋጃ ቤት ፕላን የማያውቃትና የሃብታም ቤት ግምብ ተንተርሳ የቆመች ዛኒጋባ ናት ። በፀሐይ መውጪያ በኩል የቆመው የጭቃ ልስን ግድግዳዋ ለስሙ ያህል በስሱ ኖራ ሽው ያለበት ቢሆንም ፡ የተቀሩት ግድግዳዎች ምርጋቸው ረግፎ የሸረሪት ድር ለብሰዋል ።

ወደ ውስጧ ጐራ ሲባል ፡ ከጣራዋ አግዳሚና ወራጅ የተንዠረገገው ጥቅርሻ ያስፈራራል ። በእበት በተለሰነ የሸምበቆ ግድግዳ ተከፍላለች ። የመጀመሪያዋ ክፍል ባልቻ ፀጉር የሚያስተካክልባት ስትሆን ፡ ጓዳይቱ ደግሞ በትርኪ ምርኪ የተጨናነቀች ሆና ፡ አይን የሚገባ ነገር ቢታይባት ካሊም የተነጠፈባት የባልቻና የሚስቱ ፡ የአንጓች ፡ የጠፍር አልጋ ነው ።

የባልቻ ክፍል ፡ በእርሱ አባባል 'ቢሮው' ፡ በጋዜጦች የተለበጠች ስትሆን ፡ አልፎ አልፎ ከውጭ መፅሄቶች ላይ ያለምንም ጥንቃቄ የተገነጠሉ ስእሎች በአጋም እሾህ ተቸንክረውባታል ። በግራ በኩል አራት እግሮቹን ትናንሽ ጠፍጣፍ ድንጋዮች ላይ ያሳረፈና ፡ ለጥንቃቄ ያህል ፡ አንደኛው እግሩ ከሸምበቆው ግድግዳ ጋር በወፍራም ሲባጉ የተጠፈረ ሞላላ ጠረጴዛ አለ ። ሁለት የዛጉ የፀጉር መቀምቀሚያ መኪናዎች ፡ ጣት ማስገቢያቸው ላይ ፈሔርቅ የተጠመጠመባቸው ሶስት መቀሶችና ያገለገሉ በርካታ ምላጮች ተዝረክርከው ይገኙበታል ። በቆረቆንዳ የተወተፉ ስድስት ያህል ጠርሙሶችም ይታያሉ ። አንደኛው ውኃ ፡ ሁለተኛው አልኮል ፡ ሦስተኛው ባልቻ 'ኮሎኝ' ፡ የአገሬው ሰው ግን ሽቶ የሚለው ፈሳሽ ፡ አራተኛው ቀለሙ ከቀይ ወደ ቢጫ ፡ ወይም ከቢጫ ወደ ቀይ እየተለወጠ የሚሄድ ፡ ምስጢሩንም የሚያውቅ ባልቻ ብቻ ነው ፡ የፎረፎር መድኃኒት ይዟል ። የተቀሩት ሁለቱ ባዶ ናቸው ። ከጠረጴዛው ሥርም ካፍ እስተገደፉ የሞላ የፀጉር ማጠራቀሚያ ካርቶን አለ ። ይህ ሳይሆን አይቀርም ፡ ቤቱን አንዳንዴ ፡ በሚሰነፍጥ ሽታ የሚሞላው ።

ከጠርሙሶቹ ከፍ ብሎ ስንጥቅ የበዛበትና በፕላስተር የተጠጋገነ አንድ ገጣባ መስተዋት በፍየል ቀንዶች ተደግፎ ተሰቅሏል ። በየጊዜው የሚፀዳ ባለመሆኑም ቆሽሾ መልክ በውል አያሳይም ።

ሸንበቆ ግድግዳው ላይ ከተንጠለጠሉት ሁለት አዳፋ ፎጣዎችና አንድ የአንሶላ ትልታይ ግርጌ የፊሊፕስ ራዲዮ አለ ። ባልቻ ራዲዮውን በጣም ይወደዋል ። ተአምራዊ እቃ አድርጐ ነው የቆጠለከተው ። ከምንም በላይ ይህን ራዲዮ

የሚወድበትም ምክንያት አለው ። ፀጉር አስተካካይ ከነበሩት ከአባቱ ከባሻ መኩሪያ በውርስ ያገኘው ከፍተኛው ሀብት ከመሆኑም በላይ ለሃያ ሁለት አመታት አብሮት ኖሯል ። የሚያሰራጨው ዜናና መልእክትም በስብእናው ላይ ትልቅ ተፅእኖ አሳድሮበታል ። ስለዚህ ካጠገቡ ሊያርቀው አይፈል ግም ።

ነፍሳቸውን ይማረውና ፡ አባቱ ባሻ መኩሪያ ከራዲዮ የሚተላለፍ፡ ዜና አንተርሰው የራሳቸውን ግምታዊ ትንታኔ በመስጠት ዝናን ያተረፉ ሰው ነበሩ ። እናም ባልቻ ይህንንም ዝና አብሮ ወርሷል ። አባቱ ሲሞቱ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነበር ። ግን ምንም አማራጭ ስላልነበረው ወዲያው ትምህር ቱን አቋርጦ በአባቱ እግር የፀጉር ማስተካከል ስራውን ጀመረ። እስከ አምስተኛ ክፍል መማሩም ያስገኘለትን እው ቅት መሰረት አድርጐ ከራዲዮ የሚያገኘውን ዜና በማስመል ከት በተለያዩ አገሮችና መንግስታት ላይ ትችት አሰጣጡ ከአባቱ አልቆታል ። በዚሁ ባህርይው ‘‘የመንግስት ተቃ ዋሚ!’’ ተብሎ በአንድ ወቅት ለሶስት ወራት ያህል ዘብጢያ ወርዶ ነበር ። ‘ንቃት’ አማኝቶ መውጣቱም ይበልጥ ፖለቲ ከኛ አድርጐት በጓደኞቹ ዘንድ የአለምን ውስብስብ ገፅታ ዎች አንጠርጥሮ እንደሚገነዘብ ውስጥ አዋቂ ተቆጥሮ አክብሮትንና አድናቆትን አትርፏል ።

ፀጉር ቤቱ እምብዛም ደምበኛ የላትም ። ከተማይቱ ከጊዜ ወደጊዜ ዘመናዊነትን እየተላበሰች በመጣች ቁጥር በሽርፍ ተራ እንደ አሸን የሚፈሉት የፀጉር ማስተካከያዎች ከደምበኞች እያራቁቱት ሄደዋል ። በቀን የሁለት ሀሣናት ፀጉርና የሶስት ያህል ሽማግሌዎች ፂም ቢያስተካክልና ቢላጭ ነው ። በዚች ገቢው ጐጆውን ቀጥ አድርጐ መያዝ ባለመቻሉ

ውራጅ ልብሶች ፡ ያረጁ ራዲዮኖችና የተጠገኑ ሰአቶች ደላላ ሆኗል ። አንዳንዴም ፡ ትርፍ የጋራ ፡ የሎተሪ ቲኬቶች ከአዟሪዎች እየተቀበለ ከመስተዋቱ አጠገብ ሰቅሎ ይሸጣል።

ባልቻ ሲበዛ ወሬኛ ነው ። ወንበር ላይ ከተቀመጠው ተስተካካይ ጀርባ ተገትረው ነጠላ እየቋጩ ፡ ወይ መልካቸ ውን በመስተዋቱ ለማየት እየተንጠራሩ ፀጉራቸውን ከሚያበ ጥሩና ፂማቸውን ከሚከረክሙ ደላሎችና ስራፊት ጓደኞቹ ጋር በሚያደርገው ክርክር ይመሰጣል ። ላለመሸነፍ ሲልም በግራ እጁ የሚይዘውን ሚዶ ወደ ተሚጋቹ እየቀሰረ ፡ በቀኝ እጁ የሚይዘውን መቀስ በማንቀጫቀጭ ብቻ የሚያሳልፈው ጊዜ ይህ ነው አይባልም ።

በዚህ ሳቢያ ከበርካታ ደምበኞቹ ጋር ዱላ ተማዝዟል ። በክርክሩ ስለሚመሰጥ ሳይታወቀው ጉንጭ የሚሸነትርበ ትም ጊዜ እንዳለ መወራቱና ባልታዘዘው ልክና መልክ እየሸለተ ማበሳጨቱ ለደምበኞቹ መራቅ ዋነኛ ምክንያቶች ሳይሆኑ አልቀሩም ።

ጓዳዋ ተከትታ እንካስላንትያውን ስታዳምጥ ከምትው ለው ሚስቱ ጋርም ስምምነት የለውም ። በፖለቲካው ዳግመኛ ዘብጢያ እንዳይወርድባት ትሰጋለች ። ከስራ ፈቶች ጋር ከሚፈጥረው መቋጫ የሌለው ንትርክ ይልቅ በርትቶ አንዲሰራና ጐጆዋቸውን ለማሻሻል ጥረት እንዲያደርግ ትመ ክረዋለች ፡ ታስመክረዋለች ። እርሱ ግን ምክሯን መቀበል ቀርቶ ጭራሹን አያዳምጣትም ። እንዳውም ማይምነቷን እየጠቀሰ ያንቋሸሻታል ። የስድብ ናዳ ያወርድባታል ። ሞቅ ያለው ቀንም፡ ከራስጌው የማይለየውን የክትክታ በትር አንስቶ ይዠልጣታል ፡ ዳግምኛ እንዳይለምዳት እያስማላት ።

ለራዲዮው ባትሪ ድንጋይ የገዛበት ጊዜ ትዝ አይለ ውም። በአካባቢው የሚገኙ ባለሆቴሎችን በቋሚ ደምበኝነት ተጠግቶ ፡ አብቅቶላቸዋል የተባሉትንና ያገለገሉ ባትሪ ድንጋዮችን እየሰበሰበ በየጊዜው ለራዲዮው ያጐርሳል ።

ከአማርኛ ስርጭት ፡ የጀርመን ራዲዮ ጣቢያ ነፍሱ ነው ። የቢ·ቢ·ሲ·ንም የእንግሊዝኛ ፕሮግራም ይከታተላል ። ይህን እንኳ የሚያደርገው ሲቀብጥ እንጂ ፡ ቋንቋውን የማዳመጥ ችሎታ የለውም ፡ የከተሞችን ስሞች ለመያዝ ካልሆነ በቀር ። ዋናው ነገር ፡ ቤቱ ሞር አይልም ።

ባልቻ ስለአለም ፖለቲካ ጣጣ ዘወትር ይጨነቃል ። ያስባል ፡ ያሰላስላል ። ካልተባለ ነገር ተነስቶ እልህ እየተናነቀው የራሱን አስተያየት ይሰነዝራል ። የራሱን ውሳኔ ይሰጣል ። የአለም አስከፊና ዕልመታዊ ገፅታዎች እንጂ በጐና ብሩህ ጐኖች ፈጽሞ አይታዩትም ።

የድርቅ ኮሚሽን ኮሚሽነር ፡ ድርቁ በሰሜን ወሎ ስላስከተለው ችግር የሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫ ፡ ራሱ በሚያጠናቅረው ጥበብ አጣም የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ መንግስት እርዳታ ለመስጠት መዘጋጀቱን ፡ ነገር ግን የሩሲያ መንግስት ያን እደተቃወመና እህል በገፍ መጫን እንደጀመረ ከጀርመን ራዲዮ ጣቢያ የሰማ መሆኑን ያወራል ። ይተነትናል ። የታንዛኒያው መሪ ለጐብኘት ወደ ኢትዮጵያ የመምጣታቸውን ዜና ከሰማ ፡ ያን አስታኮ ስለሶሻሊዝምና ስለኢምፔሪያሊዝም ፍጥጫ በስፋት ይዘረዝራል ። ሶስተኛው የአለም ጦርነት የመቃረቡን መርዶ ያስከትልና ስለ 'ስምንተኛው ሺህ' መዳረስ አንድ አስደንጋጭ ስዕል ያስቀምጣል ። በህንድ አገር አደገኛ ጉርፍ በርካታ ሰዎችን ቢገድልና ንብረት ቢያወድም የአሜሪካ መንግስት የሚፈጽመው ደባ

መሆኑን አይኑን ሳያሽ ይናገራል ። ኢጣልያ ለኢትዮጵያ የምግብና የመድሀኒት እርዳታ መስጠቷን ቢሰማ ፡ የአደዋና የማይጨው ጦርነቶች ያስከተሉባትን ሽንፈት ለመበቀል በእርዳታ ሳቢያ ኢትዮጵያን ልታጠቃ እንደተዘጋጀች አድርጐ ያቀርበዋል ።···

እለቱ ዘመን መለወጫ ነው ። የከተማው ሰው እንደየአቅሙ በአሉን ለማክበር ተፍ ተፍ ይላል ። የዛኒጋባው አዋሳኝ አቶ ደርቤ በጠብደል ኩሊ አሸክመው ያመጡትን ሙክት ጥለው ብልት ያወራዳሉ ። አበባ የሚመስሉት ልጆቻቸው ባማሩ ልብሶት ተሽቆጥቁጠዋል ። በራሮ የሀገር ባህል ቀሚስ የተሸሞነሞኑት ሞንዳላ ባለበታቸው እመ· ኣበዘነችም በኩራት ተንጠርበው ገባ ወጣ ይላሉ ።

ባልቻም እንዳቅሙ መናኛ ብጤ ፡ ግን አዲስ ካኪ ሱሪ ፡ አጥፈዶል ። አንጓችም ብትሆን ፡ ወጉ አይቅርብኝ ነውና ፡ አቻምና ለጥምቀት ገዝታው ጭንቅ ካልሆነባት በቀር ከሰን ዴቅ የማታወጣውን የክት ባለአበባ ቀሚሷን ሳብሰብ አድርጋ ለብሳ ጓዳዋ ትርመጠመጣለች ።

ፊቷ በቅሬታ ስሜት ጠውልጓል ። በልጅነት ዕድሜዋ ፡ በዘመን መለወጫ በአል እለት የነበራት የገጠር ህይወት ድቅን እያለባት ትተከዛለች ።

''ገንዘብ ካለህ ስጠኝ'' አለችው ፡ ስትፈራ ስትቸር ።

''ለምን?'' አላት ባልቻ ።

''ጠላ መግዣ ።'' እፍ እፍ እየተባለ የሚሳብ ጉሽ ጠላ በአይኗ ይዞራል ።

''የለኝም ።''

በእርግጥም የዛንለት ገንዘብ አልነበረውም ። በሌለው እለት ደግሞ ኩርፊያ ኩርፊያ ይለዋል ። ስድብና ግልምጫ

ይቀናዋል ።

ትንሽ ቆያይታ ‘‘ቅቤው እማያሰማ ብጤ ነው ። ዘይት ጠብ እንዳደርግበት ሳንቲም ስጠኝ’’ አለችው ።

‘‘ከየት ላምጣ?’’ ሲል አፈጠጠባት ።

‘‘ትናንት ማታ ከምታጨበጭብበት ...’’ ብላ የጀመረችውን ባልቻ አላስጨረሳትም ።

‘‘በሽታ ይጨባብጥሽ! እንግዲህ ባመት ባል ቀን በጠዋት አትነትርኪኝ’’ ሲል ደንፍቶባት ብድግ አለ ። ማታ በእርግጥ ኪሱን አራግፎ ምቅ ብሎት ነበር የገባው ። ግን አንጓች አንድ ፡ ሁለት ብር አያጣም የሚል ተስፋ ነበራት።

ብድር እንዲፈልግም ጠይቃው ነበር ። ‘‘ብድር ለማንም አልበጀ ። ከተባበሩት መንግስታት የሚበደረውን እንኳ አማሪካን እያስጨነቀው ነው’’ በሚል ትምህርት አፍን እንድትዘጋ አደረጋት ።

‘‘በል ፡ ዶሮውን እረድልኝ’’ አለችው ፡ በታሰሩ እግሮቹ እንጣጥ እንጣጥ እያለ ጣሳ ውሀ ደፍቶ ፡ ጀበና ገልብጦ ፡ ስኒ ከተኮለኮለበት ረከቦት ላይ ሲያርፍ ቀልቧን የገፈፈውን አመለኛ አውራ ዶሮ እየረገመች ።

ባልቻ ዶሮውን በአሮጌ ቢላዋ እየገዘገዘ ‘‘በግ ቢሆን ኖሮ ቆዳው ተሸጦ ስንት ቀዳዳ በደፈነ’’ አለ ። የተናገረው ለራሱ ነበር ።

‘‘ለቆሌው ያህል ፡ ደም ካየን ይበቃናል’’ አለች አንጓች ። ባልቻ ያዳመጣት አይመስልም ። ራዲዮኑን ከራስጌያቸው አነሳና መጎራነር ጀመረ ።

ሁለት የሰፈር ልጆች የእንቁጣጣሽ ስዕሎችን ይዘው ገርበብ ያለውን የፀጉር ቤት ገፍተው ገቡ ፡ ‘‘አባ ባልቻ! አባ

ባልቻ!’’ እያሉ ።

ባልቻ ብርድ ልብሱን ተከናንቦ ተኛ ።

‘‘የእንኳን አደረሳችሁ ነው?’’ ስትል አንጓች ስሜቷን ደብቃ ሁለቱንም ሳመቻቸው ። እነርሱም እየተቅለሰለሱ በእርሳስ ከተሳሉ ወረቀቶቻቸው መሀል አንዳንዱን እየመዘዙ ዘረጉላት ።

‘‘ያሳድጋችሁ!’’ በማለት አንዱን ብቻ ተቀበለቻቸውና ‘‘ይህን ደግሞ ለሌላ ሰው ስጡ ። እንዳያልቅባችሁ ። ኋላ ብር መንዝሬ እሰጣችኋለሁ ፤ እሺ? ... ጐበዞች!’’ በማለት ሸነገለቻቸው ።

ልጆቹ ወንድምና እህት ስለሆኑ ፡ አንጓች አንዱን ወረቀት ብቻ መቀበሏን እንደሁነኛ አማራጭ ወስዳዋለች ። እነርሱም አልተሻሙም ።

‘‘ኋላ እንምጣ?’’ አላት ወንዱ ። የሚፈልጋትን አስር ሳንቲም እጅ በእጅ ባለማግኘቱ ቅር የተሰኘ ይመስላል ።

‘‘አዎ ፡ በኋላ ና!’’

ልጆቹ ከወጡለት በኋላ ባልቻ የተከናነበውን ብርድ ልብስ ወረወረና ተነሳ ። ‘‘ቁርስ የለም?’’ አላት ።

በገብስ እንጀራ ላይ ያደረ ሽሮ ወጥ ፈሰስ አድርጋ አቀረበችለት ።

‘‘እንቺስ አትበይም?’’

‘‘በላሁ!’’

‘‘እህል ሳትቀምሽ ይህን ገዶ ቡና መለጋት የልብ ህመም ያመጣብሻል ። ኋላ የለሁበትም! የልብ ህመም መድኃኒት እንኳን አገራችን እንግሊዝም አልሰራችም’’ አለና የጐረሰውን እስኪውጥ አቋረጠ ።

"ምናለ ይህን ንትርክህን ትተኸኝ ሳንቲም ብትሰ
ጠኝ?"

"ከየት ላምጣ ነው'ኮ እምልሽ! ሳንቲም የሚቀጠቅ
ጡት ጃፖኖች እንጂ እኔ መሰልኩሽ? ኑሮ እየተወደደ መጥ
ቷል ። የአለም ገበያ ይዋዥቃል ። ዳሩ አንቺ አለም ምን ሁኔታ
ላይ እንዳለች የት ታውቂና! ሽንኩርት ... ዘይት... ትያለሽ።
አረብ ሴራ ጀምሯል ። ዘይት ውስጥ ምናምን እየጨመረ
እንዳይጨርሰን!... አንቺ አይገባሽ መቼስ!" እያለ አላምጦ
ሲወጥ ትን አለው ። "እስቲ ውሀ" አላት : እየጎነረ ።

በጣሳ አቁረበችለት ። ያን ጉርጉጭ አደረገና ጉሮሮውን
ጠራርጉ የጠቀለለውን ከመጉረሱ በፊት ለወሬ ሲያቆበቁብ
አንጎች ቀድማው "ምነው ሴሎች ሰዎች እንዲህ አይሉ?
አንተ ብቻ ነህ መአት የምታወራው ። ይሽ ፖለቲካህ ...ዋ!"
አለችው ንዴት እየተናነቃት ።

"መአት ይፍላብሽ!" አለና የጠቀለለውን ጉረሰ ።
ተቻኩሎ ዋጠና "ሁሉም ያውቀዋል ። ያንቺ ማይምነት ነው
የበጠበጠኝ ። የአረብ ተንኮል ማን ጠፍቶት? ብቻ... እስራ
ኤል ነቅታበታለች ። የቀመመውን መርዝ መልሳ ትረጭበታ
ለች ። ያኔ አረብ የእጁን ያገኛል! እስራኤል ማርከሻውን
የፈለሰፈችው ከፈረንሳይ ጋር ነው ይባላል ። ይሽ የአይጥ
መግደያው ዱቄት እንዳይመስልሽ! አለምን በሃያ አራት
ሰዓት ፀጥ ጭጭ የሚያደርግ ፣ እንደጢስ የሚተን መርዝ
ነው" ብሏት ባልቻ በተረፈው የጣሳ ውሀ እጆቹን ተለቃል
ቆና ተጉሞጥሙጠ ራዲዮውን በማንጠልጠል ወደ 'ቢሮው'
ገባ ።

የፀጉር ቤቷን መስኮትና በር ወለል አድርጉ ከፍቶ
ወንበር ላይ ተቀመጠና መልኩን በመስተወቱ እየተመለከተ

ሄሙን ደባበሰ ። ...አንደኛውን የመቀምቀሚያ መኪኔታ
አንስቶ ከአፍንጫው ስር ችፍግ ብሎ የበቀለውን ሄሙን
መከርከም ያዘ ።

በግራ እጁ አራት ኮቶች ፣ በትክሻው ሁለት ሱሪዎች
ያንጠለጠለና በቀኝ ክንዱ ሶስት ሰአቶች አጥልቆ በጣቶቹ
ጫፍ ደማቅ አረንጓዴ ተካፋች ሹራብ የያዘ ሰው ወደ ፀጉር
ቤቷ ገባ ። የከተማይቱ እውቅ አዚሪ ነጋዴ ገበየሁ የተባለ
ወዳጁ ነው ። አምስት ሰአት ገደማ ሆኗል ።

"ባልቻ ፣ እንኳን አደረሰህ!" አለው በፈገግታ ።

"እንኳን አብሮ አደረሰን!"

"ብለሀ እንዴት ነው?"

"ጥሩ ነው!"

"ምን ዜና አለ?" አለው ባልቻ በመስተዋቱ ውስጥ
እየተመለከተው ።

"ምን አለ ብለህ ነው?" ሲል ገበየሁ በማቅማማት
ጀመረና "ቅድም ትሁኔ ቤት ጉራ ብዬ ሳለሁ 'የተባበሩት
መንግስታት ስብሰባ ጀምረዋል' ሲል ራዲዮው ጀሮዬ ጥልቅ
አለ ። ምን ጉዳይ እንዳላቸው እንጃ!" አለ ትክሻውን
እየሰበቀ።

"እውነትህን ነው?" አለ ባልቻ ቀልጠፍ ብሎ ወደ
እርሱው በመዞር ። "ምን እባክህ ከዚች ገልቱ ጋር ስንታረክ
ወሬ አመለጠኝ" በማለት በግምባሩ አንጓች ወዳለችበት ጓዳ
ጠቆመው ።

"በኋላ ይደግመው የለ!"

"እሱማ ነው ። ግን ወሬ እሚጣፍጠው በትኩሱ ሲሆን
ነው ። ከጀርመንም ፣ ከቢቢሲም አላጣውም ። ለመሆኑ የኛው
ራዲዮ ነው እንዴያ ያለው?" ሲል ጠየቀው ፣ ገበየሁን ።

ወሬያቸውን ለማራዘም እንጂ ፣ በዚያን ሰአት በአማርኛ የሚያስተላልፍ የውጭ ሀገር ራዲዮ ጣቢያ እንደሌለ ልቦናው ያውቀዋል ።

"የጀርመን ጣቢያ ሳይሆን ይቀራል?" አለ ገበየሁ ተቻኩሎ ። ባልቻ የልቡ ስለደረሰለት ከአንጀቱ ከትከት ብሎ ሳቀበትና "አዬ ሞኙ ! አሁን በዚህ ሰአት የጀርመን ራዲዮ አለ? አይ ማይምነት!" በማለት ተሳለቀበት ።

"ለምን አይኖርም?" አለው ገበየሁ ። ይህን ያህል የሚያስተቸው ጉዳይ አልመሰለውም ።

"አይኖርማ!" ሲል መለሰለት ባልቻ ። "እዚህ ቀን ሲሆን እዚያ ይመሻል ። እዚያ ሲመሽ ደግሞ ፣ እዚህ ቀን ይሆናል ። እናም ባልከኝ ሰአት የጀርመን ሰው እንቅልፉን ስለሚለጥጥ እንደማይሆን አውቀዋለሁ ።"

"በቃ ተወው! ያለመማሬን ጉድ ያወቅሁት አሁን ገና ነው" ሲል ገበየሁ ትምህርቱን ተቀበለው ።

ባልቻም በአዋቂነቱ ተኩራርቶ ፈገግ አለና "ጀርመን ጣቢያን እወደዋለሁ ። አይዋሽም'ኮ! ሃቁን ነው ፍርጥ የሚያደርገው" በማለት ወደ ተጨማሪ ማብራሪያ ተሸጋገረ ።

ገበየሁ ቁጥርጥር ፀጉሩን ደባበሰና በውኃ የተሞላውን ጠርሙስ አንስቶ አናቱ ላይ አርከፍክፎ አሸው ። ከዚያም ወደ መስተዋቱ ተጠግቶ እያበጠረ "ስብሰባውን የከፈተው የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ነው' ሲል የሰማሁ መሰለኝ ። ስለምን ይሆን የሚወያዩት?" የሚል ጥያቄ አቀረበ።

"ዘንድሮ አማሪካ አቅለብልቦታል ። ጥሉ ከአለም ጋር በኢኮኖሚ ነው ። ሁልጊዜ ። ቆይ ...ቆይ! ቻይና በስብሰባው ተገኝታለች አልተገኘችም?" ሲል የራሱን ጥያቄ ሰነዘረለት ።

"ይህን እንኳ እንጃ!" አለው ገበየሁ ። "የያዝኩት ልብስም ሆነ ሰአት ላይ አይኑን የሚጥል ስላጣሁ ከትሁኔ ቤት ወጣሁ ።"

"ቻይና ካልተገኘች ደግሞ ነገር አለማለት ነው ። አማሪካና ቻይና አይጥና ድመት ናቸው ። ቻይኖች የዋህ መስለው ልባቸው እማይገኝ ብልሆች ናቸው ። ደሞ ታያለህ ፣ ከአማሪካ ጋር ጦርነት ያነሳሉ" አለ ባልቻ ።

"ቻይኖች እኒህ የወልደያ–ደሴን መንገድ የሚሰሩት አይነ ጭፍኖቹ አይደሉም?"

"አዎ ፣ ዋዛ እንዳይመስሉህ! አይናቸው ቢጨፈን አእምሮዋቸው ክፍት ነው ። እንደ እስራኤል የጥበብ ሰዎች ናቸው ። በዚህ ላይ መንግስታቸው ሶሻሊዝም ስለሆነ ከመስኩብ ጋር ይገጥማሉ ። የህዝባቸው ቁጥርም የትየለሌ!"

"ጦርነት አይክፈቱ እንጂ ከከፈቱ አሜሪካስ ወዳጅ ያጣል ብለህ?" አለ ገበየሁ ፣ አበጣጥሮ ጨርሶ ሚዶውን ከሥፍራው እያኖረለት ።

"እስቲ በል ማ?" ባልቻ ክርክር ለመክፈት ቋመጠ ።

"ለምሳሌ ጥሊያን!" አለው ገበየሁ ።

"ወይድ! 'ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ' አሉ ። ጥሊያን ባስታውን ይጠቅልል እንጂ ፣ ደሞ እሱ ብሎ!" የሚል ተቃውሞውን ባልቻ ወረወረ ።

ገበየሁ "እንግሊዝስ? ፈረንሣይስ?..." እያለ በመቀጠል ክርክራቸውን ለማጧጧፍ በማሰላሰል ላይ እያለ ፣ በተንዠረገገ አዲስ ካኪ ሳሪያን ኮትና ባት ተግማሽ ሱሪ ያጌጠ ጐፈሪያም ዳንዴ ፣ መውዜር ጠመንጃውን እንዳነገተ ወደ ፀጉር ቤቱ ገብቶ ቆመ ። ሰላምታ አላቀረበም ። ሰው እንደሚፈልግ ሁሉ በድንገት ዘው ብሎ ገብቶ በመገተሩ

ሁለቱም ደነገጡ ።

"ምን ነበር?" አለው ባልቻ ፣ ሽቅብ ቁልቁል እየተመለከተው ።

"ፀጉሬን ልቆረጥ!" ሲል መለሰለት ሰውዬው ጐፈሬውን እየነካካ ።

"አንድ ብር ትከፍላለህ" ብሎት ባልቻ ወደሚቀመጥበት ወንበር በጣቱ ጠቆመው ።

ሰውዬው አቅማማና ጠመንጃውን ጭኑ ላይ እንዳጋደመ ቁጭ አለ ፣ በተሰነጣጠቀው መስተዋት መልኩን እየተመለካከተ ።

ባልቻ የሰቀለውን አንሶላ አንስቶ በሰውዬው ትከሻ ላይ ጣል አደረገና ፀጉሩ ላይ ውሃ ካርከፈከፈበት በኋላ አበጠረለት። ቀጥሎም ማበጠሪያውን ወደግራ እጁ አዛውሮ በቀኝ እጁ መቀሱን እያንቀጫቀጨ የሰውዬውን ፀጉር አሸተተው ። ብሽ ስላለው ፊቱን ቅጭም አደረገና "ቅቤ አለው እንዴ ፀጉርህ?" የሚል ጥያቄ ለሰውዬው አቀረበለት ።

"ቢኖርበትሳ?" ሲል መለሰለት ሰውዬው ቆጣ ብሎ ።

"መቀስ ይጐዳብኛል!"

"አላቅልህም! ብሬን ከፍዬ ነው'ኮ እምቆረጠው ።"

"ወንድሜ ቅቤያማ ፀጉር መቀስ ይጐዳል ። የያዝኩት መቀስ ደሞ የአረብ መቀስ ነው ። ጥንካሬ የለውም ። የጀርመን ቢሆን እንኳ እንዳሻው! በጥንካሬው ወደር አይገኝለትም ። ለማንኛውም ገንዘብ ትጨምራለህ" ሲል አቋሙን ገለጸለት ።

"ስንት?"

"ሃያ አምስት ሳንቲም ።"

"እጨምራለሁ ። ቁረጠኝ ።"

ባልቻ የሰውዬውን ፀጉር ከበስተኋላው ማሳጠር

ጀመረ።

"ወደ አዲሳባ ስለምወጣ ያማረ ከመከም አድርግልኝ" በማለት ሰውዬው የሚፈልገውንም የቁርጥ ዐይነት ጠቆመው።

"እሱን ለኔው ተወው!" አለውና ባልቻ ፡ "ለምን ጉዳይ ነው ወደ አዲሳባ የምትሄድ?" የሚል ጥያቄ አቀረበለት።

"ከታናሽ ወንድሜ ጋር አገር ለማየት ።"

"ወንድምህ ከዚያ ነዋሪ ነው?"

"አይ!" አለው ሰውዬው ፣ "የክልል ተመራጭ ስለሆነ ለሽንጐ ስብሰባ ነው የሚሄደው ።"

"ለባርላማ ስብሰባ ማለትህ ነው?" ሲል ገበየሁ ጣልቃ ገባ ።

"አንተ ደሞ!" አለው ባልቻ "ባርላማ ይባል ሽንጐ ፣ ያው ስብሰባ ነው ። እርግጥ ባርላማና ሽንጐ ልዩነት አላቸው ። ባርላማ የፊውዳሊዝም ስብሰባ ሲሆን ፣ ሽንጐ ደሞ የሶሻሊዝም ነው" የሚል ትምህርት አከለለት ።

"ሽቶስ አለህ?" የሰውዬው ጥያቄ ነበር ።

"አለኝ ። ግን ገንዘብ ያስጨምራል" አለው ባልቻ ።

"ስንት?"

"ሃያ አምስት ።"

"ይሁን ! ብቻ ሽጋ አርገህ ቁረጠኝ ።"

"ልብ በል! ብር ተሃምሳ መሆኑ ነው!"

"ሂሳቡ መች ጠፋኝ አልኩህ! ጣቴን እምጠባ ሀፃን መሰልኩህ ወይ ብላገርነቴን አይተህ ማሾፍህ ነው?" ሲል

ሰውዬው ቱግ አለ ።

ባልቻ ተርበተበተ ። "በል ተወው ወንድሜ! ባመት ባል ምድር ክፉ አንዳረስ ።"

ለገበየሁም የሰውየው ሁኔታ አላማረውም ። ልውጣ ወይስ ልቆይ እያለ ሲያወላውል ተላይነህ የሚባል ከሲታና ጐባጣ ሰው በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥሞ የሚቋጨውን ነጠላ እያፍተለተለ ዘው አለ ።

"እንኳን ላዲሱ ዓመት አደረሳችሁ" አለና ከመቸኮሉ የተነሳ ምላሻቸውን እንኳ ሳይጠብቅ "ባልቻ ፣ ዜና አዳመ ጥከ? አንድ የፈረንሳይ አሮብላን ተጠለፈከ!" የሚል ወሬውን አስቀደመ ።

"እንዴት ባክህ?" ሲል ባልቻ ከአፉ ቀልቦ መቀሱን በአየር ላይ እያንቀጫቀጨ ቆመ ።

"እንዴት እንደሆነ ምኑን አውቄው" በማለት ተላይነህ መለሰለት ።

"ጠላፈውስ ማን ነው?" የገበየሁ ጥያቄ ነበር ።

"ወዴት አገር ነበር እሚሄደው?" ሲል ባልቻም የበኩሉን ጥያቄ አቀረበ ።

"ተጠለፈ መባሉን እንጂ ሌላ ሌላው አልተያዘልኝም" በማለት ተላይነህ አጠቃሎ መለሰላቸው ።

"ይኸውልሃ !" አለ ባልቻ ገበየሁን በዓይኑ ጠቅሶ ። "በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ቻይና አልተገኘችም ማለት ነው ። ይኸ እንደሚሆን ታይቶኝ ነበር ። "

"ቻይናና ፈረንሳይ ጠበኞች ናቸው?" ሲል ተላይነህ ጠየቀው ።

"ቻይና እንደመስኰብ መንግስቷ ሶሻሊዝም ነው ። እነፈረንሳይ ፣ እነእግሊዝና እነአሜሪካ ደሞ መንግስታቸው ኢምፔሪያሊዝም ነው ። ታዲያ ..." እያለ ማብራራት እንደጀመረ ገበየሁ ጣልቃ ገባ ።

"ጀርመንስ?"

"ጀርመን እንኳ ቅይጥ ነው ። እንዲህ በፀሐይ መውጫ በኩል" በማለት እጆቹን ዘርግቶ "የሶሻሊዝም ፣ በወዲህ በፀሐይ መግቢያ በኩል ደሞ የኢምፔሪያሊዝም መንግሥት አለው ። ሁለቱ ግዛቶቹ በግምብ የተለዩ ቢሆኑም ፣ ህዝቡ በግምቡ ላይ እየተንጠላጠለ መፋጠጥ ከጀመረ ስንትና ስንት ዓመቱ!"

"ምናለ ይኸን ፖለቲካችሁን ብትተዉ!" አለ ሰውየው፡ በተቀመጠበት ቆርጠጥ ቆርጠጥ እያለ ። "ታወሩ እንደሁ ስለአገራችን ፣ ስለመንግሥታችን ፣ አውሩ ። እኛ ስለተቀረው ምን አግብቶን? ይህ ባህርማዶ እንጣጥ ብሎ ተሻግሮ በማያውቁት አገር መዳከር ምን ይባላል?"

ባልቻ ከድንጋጤው የተነሳ ከሰውዬው ማጅራት ወጣ ብሎ በመቀሱ ጭብጥ ሙሉ ፀጉር አነሳ ። ሳያስበው ያደረገው ጥፋት ነበር ። ፀጉሩን እንደጨበጠ አፉን ከፍቶ ሲንቀጠቀጥ ቆየና በሰውዬው ጀርባ ቁልቁል ለቆት ላቡን ጠራረገ ። መላጣውን ስፍራ ለመድፈን ከላይና ከታች ፡ ከግራና ከቀኝ ማበጣጠር ሞከረ ። ፈጽሞ የማይቻል ሆነበት ። እናም ከዚያ በመነሳት ፣ በሁለቱ ጀሮዎቹ አቅጣጫ ጥቂት ከፍ ብሎ በመቀሱ ቀጭን መሥመር አወጣና በቦጨቀው ልክ የሰውዬውን ፀጉር ዙሪያውን መደመደው ።

ይሄኔ ገበየሁ "ዞር ዞር ብዬ መጣሁ" ብሎ ውልቅ አለ ። ተላይነህም አፍታ ሳይቆይ መሰስ ብሎ ወጣ ። ባልቾና ሰውዬው ብቻ ቀሩ ።

ባልቾም ስራውን ወዲያው አቀላጥፎ ፣ የጥራቱን ውጤት ለመገምገም ያህል "እስቲ ወደቀኸህ ዞር በል" አለው ሰውዬውን ።

ሰውዬው ብድግ ሊልበት ሲል የበስተግጅራቱን ኮሌታ ጨምድዶ ያዘና መልሶ አስቀመጠው ።

"እስቲ ደግሞ አሁን ወደ ግራ ።"

ሰውዬው እንደተቀመጠ ፊቱን ወደ ጓዳ አዞረለት ።

"ጥሩ ነው!" ብሎት ባልቾ አንሶላውን ከትከሻው ላይ አወረደለት ። ከአሮጌዎቹ ፎጣዎችም አንዱን አንስቶ ፊቱን አበስ አበስ ሲያደርግለት የፀጉር ብናኝ ባፍንጫው ገብቶበት ኖሮ ሰውዬው ደጋግሞ አስነጠሰው ።

"ይግርህ!... ይግርህ!... ይግርህ!" እያለው ባልቾም ጐንበስ ቀና አለለት ።

ትንፋሹ ሲመለስለት ሰውዬው ወደ መስተዋቱ ጠጋ አለ ። የገዛ መልኩ አጠራጥሮት አይናቹን ከፈት ከደን አደረገ።

"ቆይማ! ከወደ ግምባርህ ትንሽ ይቀረዋል መሰል" በማለት ባልቾ መልሶ አስቀምጦት አፍንጫውን ካጠላው ጐፈሬው በመጠኑ ከርከሞለት ፀጉሩን ከግምባሩና ከአናቱ በሚገባ ተመተመለት ።

"እሽ!" አለ ሰውዬው መልኩን በመስተዋቱ እያየ ፣ "ከመከም አለነበረ ያልኩህ?"

"አዬ የእኛ ሰው!" የሚል ምላሽ አመጣ ባልቾ ቀልጠፍ ብሎ ፣ "ያለ ከመከም ሌላ ቁርጥ አያውቅ ። ወደ አዲሳባ አይደል የምትሄድ?"

"ቢሆንስ ?"

"ያዲሳባን ተወውና ፣ ገና ደሴ ስትገባ የምታየው የፀጉር ቁርጥ አይነት ያይን አዋጅ ይሆንብሃል ። ጀንትራ እሚሉት አለ ፤ ከወደማጅራት እንደ አህያ ጅራት ቁልቁል ሾሎ እሚወርድ ፣ ወይ እንደፍየል ጭራ ሽቅብ እሚቀሰር ፣ ካሊፎርኒያ እሚሉት አይነትም አለ ። ያ እንኳ ላንተ አይሆንም ። የአሜሪካ ነው" የሚል ሰፊ ማብራሪያ ሰጠው ።

"ይኸስ ምን እሚሉት ነው?" ሲል ጠየቀው ሰውዬው በጉጉት ።

"ሙኒክ ይባላል ። የጀርመን ነው" አለው ባልቾ አፉ እንዳመጣለት ።

ገና ያልሰማውና ያላየው ሆኖበት እንጂ ፣ በአጋጣሚ የደረሰበት ቁርጥ እንኳ 'ፓንክ' የሚባለው ዝርያ ነበር ።

ሰውዬው ሳቅ ብሎ ከወንበሩ ተነሳ ። ጠመንጃውን ጉልበቶቹ መሀል አቁሞ ፣ ኩራት ኩራት እያለው ክሳሪያን ኮቱ ደረት ኪስ ሁለት አሮጌ ብሮች መዝዞ ፣ እላፊ ሂሳብ እንዳያመልጠው እያንዳንዳቸውን አራገፈና አስጨብጦት "መልሱን ፣ ቶሎ በል" አለው ።

"ቆየኝማ ። እዚችው አረፍ በል ። ከሃጂ ኡስማን ሱቅ መንዝሬልህ ልምጣ" ብሎት ባልቾ እየሮጠ ወጣ ።

ሰውዬው ወደ መስተዋቱ ተጠግቶ እየተዟዟረ መልኩን ደጋግሞ አየ ። አልመጣልህ ብሎት ግራ በተጋባ መንፈስ

ራቅ አለና እንደገና ተመለከተው ። ጥቁር ቆብ የደፋ መሰለውና አማተበ ።

እንዲህ በመቅበጥበጥ ላይ ሳለ ባልቻ ተመልሶ መልሱን ሰጠው ።

"በዚህ ቁመናህና በዚህ ቁርጥህ ሎቲ ብታንጠለጥል!..." በሚሉ ቃላት እየሸነገለው እበር አደረሰው ።

"አዬዬዬ!" አለው ሰውዬው ፣ "ደን ጥበቃ እየተባለ ዝሆንና አውራሪስ መጣል ከቀረ በስንት ዘበኑ!"

"በል ፣ በደህና ያግባህ!" አለው ባልቻ ፣ በፈለሰፈው የፀጉር ቁርጥ እየተገረመ ።

"አሜን!"

ባልቻ አንገቱን ወደ ጓዳ ገባ አድርጐ "በይ ፣ በዚህ እንደሚሆን አድርጊ" ሲል ለአንጓች ብሩን ወርውሮላት ፣ በሃምሳዋ ሳንቲም አንድ ሁለት ሊል ወደ ትሁኔ ቤት ተፈተለከ ።

ባለ ጉዳይ

ተባይ የወረሣትና የተቦጫጨቀች ቡናማ ሽሚዛቸውን ገልብጠው ለፀሐይ ዘርግተዋታል ። አጠገቧ ቁጢጥ ብለው ፣ የፀሐዩ ግለት ሲያይልባቸው እየተንፈራፈሩ ብቅ የሚሉትን ተባዮች እየለቀሙ በአውራጣታቸው ቀጭ ያደርጓቸዋል ፣ አባ እንቀርሻው ።

ቀዬው ጭር ያለ ነው ፣ የሠፈሩ ቆሻሻ የሚከመርበት ። አልፎ አልፎ ብቻ አንዳንድ ሰዎች ውልብ ሲሉ ይታያሉ ።

ሊፀዳዱ ። የሠፈሩ ህፃናት መጫወቻ ለማግኘት የቆሻሻውን ቁልል ያተራምሳሉ ። ቁልሉ ቆሻሻ—የፀሐይዋን ግለት ሲኖበል አካባቢውን የሚያጥነው ግማት ለጉድ ነው ።

ረሃብና እርጅና ጓዛቸውን ጠቅልለው የሠፈሩባቸው አንድ አይናው አዛውንት አባ እንቀርሻው ፣ ለፀሃይ የዘረጓትን የተበሳሳች ሽሚዛቸውን አንስተው አራግፈው ለበሷት ። የነተበ ዐመድማ ጋቢያቸውን ከደረቡ በኋላ ቢሲ ጠጥታ የቀላች ዘንጋቸውን ወደላይ ቀስረው ፣ ትልቁን ዋርካ ሽቅብ አያዩ የራስ—በራስ ሙግታቸውን ተያያዙተ ፣ በንዴት እየተርገፈገፉ ።

"አዳፋ ብለብስ ፣ አፈ—ዶማ ብሆን ማንን ጐዳሁ ? ግራ ቀኝ አሟግተው ተረትተሃል ቢሉኝ ምናለ ? ሰባት ዓመታት ሙሉ ከራቦር—ጠሐፊ ራቦር ጠሐፊ ስዞር ጅስሜ አልቆ ፣ የሰው ውራጅ ሆኜ ብቀር ምን ሊጠቀሙ !?" ንግግራቸውን ገታ አደረጉና ዘንጋቸውን ወደ ትልቁ ዋርካ እንደቀሰሩ አፍጠው ተመለከቱት ።

ዋርካው አባ እንቀርሻው ለተናገሩት መልስ የሚሰጣቸው አልሆነም ። በሞገሱ ተኩራርቶ ቁልቁል በንቀት የሚመለከታቸው መስሏቸው እሮሮአቸው ገነፈለ ። "ጥንት ጉንዶ ማር ፣ አሥራት ፣ የቆሎ ፣ የሣርና የውሃ ፣ የስልከኛ ፣ የምልምል ፣ የመስቀል ፣ የቋሳ ... ምን ሥፍር ቁጥር አለው ! ... በሚሉት የግብር አይነት ወሎ—ወሎዬ ምን ያላየው አበሳ አለ ? ዛሬም አሳሩ ብዙ ነው ። ሙግት ቢመጣ በሱ ... እህል ቢያር የሱ ... ለጦርነት ቢመለመል እሱ ... የነፍጥ መራኮቻና መረጯመጃ ቀየ የሱ ... ዳኛ ከነሱ ... አየ ጉድ !

ጥራሪ ፍረደኝ ! የወለህ—ማርያም አውድማ ይታዘባቸው ! ጡረኞች !" አሉና አፈር የጠጣ ጋቢያቸውን አራግፈው ዘንጋቸውን እየተደገፉ ራፖር_ፀሐፊ ፍለጋ ፣ ጀርባቸውን ለዋርካው ሰጥተው ወደ መሀል ከተማው ማዝገም ጀመሩ ። ...

ላሰባት ዓመት ያክል ፍትህ ያጡበት ጉዳይ አላቸው ። ፍትህ ፍለጋ ያልዞሩበት ቦታ የለም ። በየአጋጣሚው የገኙትን ፖሊስ ሁሉ እያስቆሙ ጉዳያቸውን በዝርዝር ለማሳወቅ ቢሞክሩም ንግግራቸውን አስኪጨርሱ እንኳ ያደመጣቸው አንድም የለም ። ፋይላቸውን ታቅፈው ገና ጠጋ ሲሉት ለልመና የመጡ እየመሰለው 'እግዜር ይስጥዎ !' እያለ የሚርቃቸው ብዙ ነው ።

ለዚህ ጉዳያቸው የነበራቸውን ገንዘብ ሁሉ ጨርሰዋል ። በተለያዩ የራፖር ፀሐፊዎች የተለያየ ማመልከቻ አፅፈዋል ። ለክላሰር ፣ ለቴምብር ፣ ለፍርድ ቤት አንጋቾች ጉቦ ... ያወጡት ወጪ ቀላል አልነበረም ።

የዚህ ሁሉ ውጣ—ውረድ የከፋ ድህነት ውስጥ ክቶአቸዋል ። ንዴትና እልህ አስከትሎባቸዋል ። ብቻቸውንም ያወራሉ አድማጭ ባይኖራቸውም ለራሳቸው ሲያወሩ የፍትህ ጭላንጭል ያገኙ ያክል ቀለል ይላቸዋል ። ተስፋ እየታያቸው ይፅናኑባታል ።

ሁነኛ የራፖር ፀሐፊ ማግኘት ቀላል አልሆነላቸውም ። አብዛኞቹን የወልዲያ ካተማን ራፖር ፀሐፊዎች አዳርሰዋል ። የሁሉም አልጣማቸውም ። እስከአሁን ያልሞከሩትን ማፈላለግ ጀምረዋል ፣ እያጠያየቁ በቅርቡ ከውጭ ወደ ወልዲያ

የመጣ እውቅ ሰው መኖሩን ሰምተው ወደሱ ለመሄድ ልባቸው ቆመ ።

* * *

ሰውየው በእርግጥም ወልዲያ ከገባ ገና መንፈቅ ቢሆነው ነው ።

የተለያዩ ዶሴዎችን ፣ የተጨረማመቱ ካርቦኖችንና ሉክ ወረቀቶችን ከተሸካመው አሮጌ ጠረጴዛ ጀርባ የቆሸሸ አንሶላ አገልድሞ ፣ እንደ ትላንት የገዛው ነብስ ይማር ሱፍ ሱሪው ረዝሞበት ኖሮ አጥፎ እየቀመቀመ አጠገቡ ካለ አንድ ባለ ጉዳይ ጋር ያወጋል ። ባለአንዲት ክፍሏ ደሳሳ ጉጀው መኖሪያውም ፣ ቢሮውም ናት ።

"የሰማንያ ፊርማ ሳይኖረን ፣ በወደድኩሽ—ወደድኩህ በአንድ ጣራ ስር መንፈቅ ለማይሞላ ግዜ አብረን በኖርን ፣ ስንቋን ደባልቀን አንድ ማዕድ ላይ በቀረብን ብቻ ... ወደኋላው ባንስማማና ልባችን እየቅል ሆኖ ብንላቀቅ 'ንብረት እኩል ይገባኛል' ብላ ብትከሰኝ ሕጉ ይደግፋታል ?" ሲል ራፖር ፀሐፊውን ጠየቀ ።

"ይኸንን ሀሳብህን ለፍርድ ቤቱ አልፃፍክም ኖሯል ?" አለው ራፖር ፀሐፊው ቀና ብሎ ሌላ ዶቃ ክር በመርፌው ቀዳዳ እየከተተ ።

"ምን ዋጋ አለው ?" አለና ሰውየው ከንፈሩን ነከሰ ። "በማይረባ ፀሐፊ አፅፌ ለዳኛው ብሰጣቸው 'ጭብጥ የለውም !' አሉኝ ። ሁለት ብር እኮ ነው የከፈልኩት ። ጉድ ሠራኝ !" በቁጭት ተወራጨ ።

"የህግ ነገር ዋዛ አይደለማ !" ፀሐፊው በኩራት ተኮፈሰ ፤ 'ከእኔ ወዲያ ፀሐፊ !' በሚል ስሜት ። ቀጠለና "የህግ ፅሁፍ ማንም የሚፅፈው ነገር አይደለም ። ለመፃፍማ ዛሬ ማን የማይፅፍ አለ ? ቁም ነገሩ ግን ባለጋራውን ሊረታ የፈለገ ነገረኛ ዳኛውን የሚያዋዛ ፣ ዳኛውን እያከበረ የሚያግባባ ፣ በተለይ ቁልጭ ያለች የህግ አንቀጽ ጠቅሶ ሲያቀርብ ነው እንጂ አለዚያማ ... በዋል ፈሰስ ነው" አለው የቋጠረውን ክር በጥርሱ እየቆረጠ ።

ራፖር ፀሐፊው ከሌሎቹ ፀሐፊዎች የሚሻልበት ሁኔታ ስላለው ገና ከመምጣቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂነትን አትርፏል ። ፍርድ ቤቶች አካባቢ እየተዘዋወረ በየአጋጣሚው የሚያደምጠውን የህግ ቁጥር ሁሉ ለአንድ ወቅት ያገለግላል በሚል መንፈስ ሲመዘግብና ሲያጠና የኖረ ነው ። ደሴና አዲስ አበባ በሚመላለሱ ነጋዴዎች የንጋሪት ጋዜጣ ያስመጣል ። ጊዜ ያለፈባቸው ቢሆኑም የተለያዩ ጋዜጦችን ይሰበስባል ፣ በተለይ ለህግ አምድ ልዩ ሱስ አለው ።

በአንጋገሩ ጥራዝ—ነጠቅ በመሆኑ የፈረንጅኛ ቃላትን በመደባለቅ የመጠቀ የህግ አዋቂ መስሎ ይቀርባል ። የሌሎችን ራፖር ፀሐፊዎች ስም ያጠፋል ፣ ችሎታ እንደሌላቸው በግልጽ በመናገር ። በባለጉዳዮችና በዳኞች መካከል ጉቦ ሰለሚያቀባብል እና በመካከሉም ስለሚጎርስ እሱም በሌሎቹ ፀሐፊዎች ይጠላል ። ቢሆንም የደምበኛው ብዛት በሽ—በሽ ነው ። በአጠቃላይ በከተማው ከሱ ወዲያ ራፖር ፀሐፊ ያለ አይመስልም ።

"ታዲያ እንዴት ላድርግ ? የማንም ጋለሞታ መጥሪያ እያስወጣች ፍርድ ቤት ስታንከራትተኝ ትልቅ ውርደት አይደለም ?" አለ ሰውዬው ቀኝ እጁን ጨብጦ ሞኑን መታ መታ እያደረገ ።

"ላንተ ጉዳይ መጠቀስ ያለበት የህግ አንቀጽ ..." አለና ራፖር ፀሐፊው ጠረጴዛው ላይ ያለውን 'የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ' የሚለውን ጥራዝ ሲያገላብጥ "እንደምንዋላችሁ ቤቶች !?" አሉ አንድ አዛውንት አንገታቸውን ብቅ አድርገው ።

"እግዜር ይመስገን ! ይግቡ" አለና ፀሐፊው ተጣድፎ መለሰ ፣ ካርቶኖች የተነጠፉባትን መደብ እያመለከታቸው ።

ራፖር—ፀሐፊው ቀደም ሲል ችግሩን ሲያዋየው ለቆየው ባለ—ጉዳይ ቀጠሮ ሰጥቶ ፣ የቀመቀመውን ሹሪ አጠገቡ ወደሚገኝ የጠፍር አልጋው ላይ ወረወረና ያገለደመውን አንሶላ አጠበቀ ። መርፌዋንም ግድግዳ ላይ ሰካት ።

"ምን ነበር አባት ?" አለ እየተንጠራራ ። ሲንጠራራ የተቀመጠባት ወንበር ተንሳጠጠች ።

"ነገሬ ብርቱ ነው !" አሉና በረዥሙ ተነፈሱ አባ እንቀርሻው ፣ ያመለከታቸው መደብ ላይ እየተቀመጡ ።

በራ በሆነው ሞንቅላታቸው ላይ አንድ ወፈር ያለ አረንጓዴ ክር አዙረዋል ። ከዚሁ ጋር በተያያዘች አዳፋ እራፊ ጨርቅ ግራ ኤዲናቸውን ሸፍነዋል ። የተጎሳቆለውና እንደ መነኩሴ ቆብ የተጣጠፈው ፊታቸው በእርጅና ላይ መከራ

የተደራረበባቸው መሆኑን ይመሰክራል ። ባጠለቁት ሰፊ ቁምጣ ግራ ጭናቸው በኩል ብልታቸው ብቅ ብሎ ይታያል ። እንደ ዋልካ መሬት የተሰነጣጠቁት የእግሮቻቸው ተረከዞች የሌት ቁርና የቀን ሃሩር እንደተፈራረቀባቸው ያስታውቃሉ ።

"አ ሪዴጥ ነው ነገሩ ፣ ክስ ነው ወይስ መልስ ?"

"አትችኩል ልጄ ! 'እሀ !' ብለህ አድምጠኝ ። ሁነኛ ጠሃፊ ነገርን ያደምጣል ። ነገሬ ብርቱ ነው ያልኩህ ያለምህኛት አይደለም ። ሰባት ዓመት ሙሉ ያንከራተተን ፣ አለጪሪ አለቀባሪ ያስቀረኝ ፣ የከተሚ ምጥዋተኛ ፣ የደጀ—ሰላም ቤተኛ ያደረገኝ ነገር ነው ። በይህ ነገር ከጠሐፊ—ጠሐፊ ሰዞር የፈጀሁት ገንዘብ አይወጋም" አሉና በዘንጋቸው ጀርባቸውን አከክ—አከክ አደረጉ ።

"ቢሆንልኝ ብዬ ሙግት ከገባሁ ዘመን የለኝም ። ምን ዋጋ አለው ! በዚህ ላይ የዛሬ ዓመት ገደማ የከገማ ቀጣፊ አራት ባውንድ ቀማኝ !"

"የት አባቱንስ ! የሔማኖውን ስም ያውቁታል ?" አለና ራፖር ፀሐፊው አጃረጣትው ።

"ኤዲያ ! ምናለ ብታደምጠኝ !" በብስጭት እጆቻቸውን አወናጨፉ ። ተስፋ መቁረጣቸው ከፊታቸው ይነበባል ።

"ልብ ብለህ አድምጠኝ ! ከአፌ አትቀማኝ !" አሉና በቁጭት ዘንጋቸውን አጥብቀው ጨብጠው ወለሉን ወጋ ወጋ አደረጉት ። "በተወለደች በዓመቷ በምች እመም እናቷ ስትሞት እንደ እናት ፣ እንደ አባት ሆኜ አንዲት ልጄን ያሳደኳት እኔው ራሴ ነበርኩ ። በጀርባዬ አዝዬ ፣ የፍየል

ወተት እያጠባሁ ከስንት መዓት ያተረፍኳት መከራየን በልቸ ነው ። ምስለኔ የተወልኝ የወውድማ ጥራጊ ለዕለት ጉርሳችን ባይበቃ ፣ ጥራሪ ወርጄ እንጨት ተሸክሜ ጉልት እያወጣሁ በማገኛት ቁጣሪ ለወግ ለማዕረግ አበቃኋት በምልበት ወቅት ... ወይኔ እንቀርሻው ! የዘራነውን ሁሉ ተባይ ቢያጠፋብን ፣ ቀን እስኪያልፍ ያችኑ አንዲት ፍሬየን አስከትዬ እዚሁ ወልዲያ ገባሁ ። እንደ ባልንጀሮቿ ተላውሳ ጥቂት ቁጣሪ ብታገኝ ብየ ግራዝማች አበጋዝ ቤት አስቀጠርኳት ባግር ድና ።

"በተቀጠረች በአራት ወሯ የጌታየ የግራዝማች ልጅ ካሣሁን ድንግልናዋን ቢገሳት ፣ የፀነሰችውን እንኳ ቦሰላም እንዳትገላገልበት ፣ ቤተክስያን እንደገባች ውሻ ብጣሏን ብቻ አስይዘው አባረሯትና መግቢያ ቢጠፋት ተመልሳ እጄ ላይ ወደቀች ። ለማን አቤት ይሉታል ?"

"ለዕለት ስንቃችን ከተማ እየዞርን ውለን ፣ ማደሪያችን ደጀ ሰላም ሆኖ እያለ አንድ ሌሊት ውጋት ጡት ስሯን ቀስፎ ያዛትና እጄ ላይ አረፈች ። ዘመድ ወገን ስለሌለኝ እንበለ ፍታት ፣ እንበለ ፀሎት ቀን ተሌት ራሴ ጭሬ ታች መሬት አዋልኳት ። ይኸን በደሌን ደጋግሜ ባመለክት ማን ያስማኝ ? የከሰስኩት ግራዝማች አበጋዝን ... ዲታ! የገባ ላፍቶ ተወላጅ ባላባት ! ልጄን ለሞት የዳረገ የጌታዬ የግራዝማች የበኩር ልጅ ! ህጉ ለሳቸው ... የንጣቱ የማጣቱ ነገር የኔ ! ቆይማ ..." አሉና, ከውስጥ ኪሳቸው አንድ የተጣጠፈ ዶሴ አሙጥተው ፅጡት ።

ራፖር ፀሐፊው ዶሴአቸውን ተቀብሎ ሲያገላብጥ አባ እንቀርሻው አንገታቸውን ደፍተው ጥቂት ከተከዙ በኋላ "አስተውለህ እየው ! ሃያ አንድ ወረቀት ነው ። ሰሚ ባገኝ ብየ ደጋግሜ ያጣፍኩት" አሉ ባሞጨሞጨችው ቀኝ አይናቸው ትክ ብለው እየተመለከቱት ።

ራፖር ፀሐፊው በባለ—ጉዳዮች ዘንድ ልዩ ግምት ከሚያሰጡት ነገሮች ዋነኛው የሆነውንና በተለያዩ ክሮች የተተበተበውን ሰባራ መነፅሩን ዓይኖቹ ላይ ሰክቶ ዶሴአቸውን እያገላበጠ ማንበቡን ቀጠለ ። ሜንቅላቱን ግራ ቀኝ እያወዛወዘ ያልጮመጉማል ። አልፎ አልፎ ከንፈሩን ይመጣል ።

"ጥሩ አድርገህ ጣፍልኝ ! እጅህ ርጥብ ቢሆን ዕድሌን ልሞክር !" አሉት በረዥሙ እየተነፈሱ ።

ራፖር ፀሐፊው መልስ ሳይሰጣቸው ከአንድ ፋይል ወረቀት አወጣና ካርቦን ከተተበት ። ወደ አፍንጫው ጫፍ የወረደውን ሰባራ መነፅሩን ከፍ አድርጎ ዕለቱን መግፋ ጀመረ ።

"አ ! አ !" አሉና አባ እንቀርሻው ራቦር ፀሐፊው ቀና ብሎ እንዲያያቸው አደረጉት ። "የጅህ ዋጋ ስንት እንደሆነ አንነጋገር ። በአራት ኮቢ አድርገህ ጣፍልኝ ። እንበለ ቀሪና እንበለ ቅጂ ሙግት ምን ዋጋ አለው ? አንድ ለአውራጃው ግዛት ፍርድ ቤት ... አንድ ለቦሊስ ... አንድ ደግሞ ለአውራጃው ገዢ ... አንዱ የኔ ቀሪ ይሆናል ።" በግራቸው በኩል የነበረችውን ዘንጋቸውን ወደ ቀኛቸው አዞሩ ።

"ጥሩ ! እንግዲህ ... እኔ የምፅፈው አንቀጽ ጠቅሽ

ነው ። ለአራት ኮፒ አሉኝ ? እስክሪፒቶ ፣ ወረቀትና ካርቦን ተወዷል ። በተለይ የእስክሪፒቶ ነገር ! የዛሬ እስኪሪፒቶ ገና አንድ ሳይሉበት ያልቃል ። አሁን ይቺ ..." አለና ቀለሟ ታች የደረሰውን እስክሪፒቶ ከፍ አድርጎ አሳያቸው ። "ትላንት ገዝቻት ገና አራት ወረቀት ሳልፅፍባት ነው እንዲህ ያለቀችው ! ጉዳይዎ ደግሞ የዋዛ አይደለም ። ብዙ አንቀጽ መጥቀስ አለብኝ ። ስለዚህ አራት ብር ይከፍላሉ !" አለና ደፍጠጥ ባለው አፍንጫው ላይ የተፈናጠጠውን ሰባራ መነፅሩን ወደ ላይ ገፋ አድርጉ በእስክሪፒቶው ጠረጴዛውን መቆርቆር ጀመረ ።

"ይበዛብሃል ማለቴም አይደል ! ባይሆን ጥቂት ቀንስልኝ ... ራብ አንጀቴን አጥፎታል ። የለምለም እንጀራ ሽታ በአይኔ እየዞረ ነው ። በደጀ—ሰላም ፍርፋሪ ትንፋሼ አለች ። እንደሚሆን አድርግልኝ ። ከልጆችህ ታገኘዋለህ ። የተማረ ሰው አይጨክንም ። ..." ልመናቸውን አቋጮደጮዱት ።

"ይበሉ ሦስት ብር ይክፈሉ ! ምን ይደረግ ?" ወረቀቱንና ካርቦኑን ካስተካከለ በኋላ አስክሪፒቶውን ወጋ ።

አባ እንቀርሻው ከፍየል ቆለጥ ቆዳ የሠሯትን የገንዘብ ማስቀመጫ ከረጢታቸውን ከጉያቸው አካባቢ አወጡና የተጠፈረችበትን ጅማት ፈትተው ከውስጧ የተጣጠፉ ብሮችንና ሣንቲሞችን አወጡ ። አንዷ ብር ሌላ እንዳልደረበች ደጋግመው በማሸት እያረጋገጡ ፣ ሣንቲሞቹንም ጥርሳቸው ላይ እየከረከሩ ከለዩ በኋላ ሶስት ብር ሰጡት ። ሁለት ብሮችና የአንድ ብር ሣንቲሞች ።

ራፖር ፀሐፈው የተቀባላቸውን ሦስት ብር ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ አቀርቅሮ መፃፍ ጀምሯል ። የሚፅፋቸውን ቃላት ዝቅ ባለ ድምጽ ይናገራቸዋል ። የተጠጋገኑ የህግ መፃህፍትና የወየቡ ነጋሪት ጋዜጣዎችን ያገላብጣል ። ያልጮመጉማል ። የመደነቅ ፣ የመጨነቅ ፣ የመመራመር ስሜት ፊቱ ላይ እየተነበበበት ይፅፋል ።

"ለመንግሥቴ ታማኝ ... ለህግ ተገዥ .. የታዘዝኩትን የማላጐድል' በልበት !" አሉት አባ እንቀርሻው አንገታቸውን አስገው ።

ራፖር ፀሐፈው ያደመጣቸው አይመስልም ። ዝም ብሎ ይፅፋል ። ያልጮመጉማል ። ጣራው ላይ አፍጦ ያስባል ። ያሰላስላል ። ያረጀ የቀሚስ ትልታይ ከሸሚዙ ኪስ እያወጣ የአፍንጫውን ጫፍ ይጠርጋል ። አሥር ግዜ ሰባራ መነፅሩን ከፍ ያደርጋል ።

"'ለባንዲራዬ ሟች ... ጪሪ የሌለኝ ... የሰባ አራት ዓመት ሽማግሌ ... አቅመ ደካማ' በልልኝ ! ዋናው ይኸ ነው !"

"ዝም ይበሉ አባት !" አላቸው ካቀረቀረበት ቀናብሎ ። "አይገባም ! ለኔ ይተዉት ... ስጨርስ አነብልዎታለሁ ። እያደናቀፉኝ !" አለና አቀረቀረ ።

ዝምታ ሰፈነ ።

ወዲያውኑ አንዲት ወፍራም ሴትዮ እያለቀሱና እየተናፈጡ ገቡና "ጋሼ መርጊያው ! ቦሊሱ ማመልከቻ አስጥፌ አንድመጣ መክሮኛል ። ወይኔ ! እሱ ጉልበተኛ ሆኖ እኔን ሊጫወትብኝ !? ... ሴተኛ አዳሪ የሆንኩት ወድጀ መሠ

ለው እንዴ? ... እኔን አታሎ ቤት ካዘጋኝ በኋላ ሂሳቤን ክፈለኝ ብለው አፍንጫዬን መታኝ ። አንድ ጫማውን ላስቀርበት ብሞክር አልቻልኩም !" ሴትዮዋ ያለቅሳሉ ። አንድ ወረቀት ይዘዋል ።

"እረ ይቆዩማ ! ሊበላሽብኝ ነውኮ ! ረጋ ይበሉ .. የኔ ይለቅ !" አሉ አባ እንቀርሻው ሁለት እጆቻቸውን ወደ ሴትዬዋ ዘርግተው ፣ የሴትዬዋ ስሞታ የራፖር ፀሐፈውን ሃሳብ እንዳያደናቀፍባቸው እየሰጉ ።

ሴትየዋ እምባቸውን እየጠራረጉ ጥግ ተቀመጡ ። ... አባ እንቀርሻው ፈራ ተባ እያሉ "'ከእግርዎ ሥር ወድቄ እኔ ባርያዎ የምለምነዎና በእግዜር ስም የምማጠንዎ ... የሚል ጨምርበት ! አትርሳኝማ ልጄ !" አሉት ።

"ምን ያሉ ሰው ናትው !! ዝም ቢሉ ምናለበት ?" ራፖር ፀሐፈው ቱግ አለ ።

አባ እንቀርሻው አቀረቀሩና በትካዜ አንዲት ስንጥር አንስተው ወንከርከር ያለው ጥርሳቸውን እየወጉ በሀሳብ ጢብሰለሰሉ "ሳነብልዎት ፣ ያድምጡኝ !" አላቸው ሰባራ መነፅሩን ወደ ላይ ገፋ እያደረገ ።

አባ እንቀርሻው ከተቀመጡበተ ብድግ ብለው አጠገቡ ቁጢጥ አሉና በተንቀሳቀሰ ቁጥር በምትንሳጠጠው ወንበር ላይ ወደተቀመጠው ፀሐፊ አንጋጠጡ ።

ፀሐፈው አፉንና አፍንጫውን አሁንም አሁንም ከኪሱ በሚጐትታት ብጣሽ ጨርቅ እየጠራረገ ፣ ገሮሮውን ስሎ ማንበብ ጀመረ ። ቀኑንና ዓመተ ምህረቱን በዝቀተኛ ድምፅ ኩሽካሽከ በኋላ ፣

"ለክቡር የየጁ አውራጃ ግዛት ፍርድ ቤት ።
ወልዲያ ።

ከሳሽ እኔ ... ከማለቱ "ተበላሽቷል ልጄ ! እንዲህም አይደል የሚጣፈው !" አሉት አባ እንቀርሻው ተመልሰው መደቧ ላይ እየተቀመጡ ። ራፖር ፀሐፊውን በተስፋ መቁረጥና በብስጭት ተመለከቱት ። የሚናገሩት ነገር የጠፋባቸው ይመስላል ፣ በሁለት እጆቻቸው ጭንቅላታቸውን ደግፈው ያዩታል ።

"ምናለ ቢያስጨርሱኝ ?" የተሟረረው ራፖር ፀሐፊ የጉሪጥ ተመለከታቸው ። አመለካከቱ የትዕግስቱን ማለቅ የሚያመለክት ነበር ።

"ምኑን ጨረስከው? 'ለክቡር የየጁ አውራጃ ግዛት ፍርድ ቤት መሃል ዳኛ የተከበሩ ፊታውራሪ ገበየሁ' ማለት ሲገባህ ጉረድከው! ቀጠልክና ደግሞ 'ከሣሽ!' --እንዴት ይቀበሉኛል? 'እኔ ባሪያዎ' ማለት ነበረብህ ። ማን አይዞህ ቢለኝ! ማን ቢከተለኝ? እግዜር ቢጣላኝ ነው እንተው!..."

ራፖር ፀሐፊው ፊቱን አኮሳትሮ ጠረጴዛውን በቡጢ 'ዲ! ዲ!' አደረገውና "ሌላ ፀሐፊ ይፈልጉ! ምን ያሉ ሰው ናቸው?" አለ ።

"አንተ ምናለብህ ? ድፍረት የተመላበት ጥሁፍ ይዠ ብቀርብ የምቀጣው እኔ! ካልሆነልህ ምን ይደረግ? እንደለመ ደብኝ ልንከራተተው እንጂ!" አሉና ብድግ አሉ ።

"ከኔ የተሻለ ካገኙ ይሞክሩ !" አለና ራፖር ፀሐፊው ፈገግ አለ ፤ ሊያባጫቸው ። ቀጠለና "የከሰርኩትን ወረቀትና ካርቦን ሂሣብ እቆርጣለሁ ። በዛሬ የገበያ ውድነት ቀልድ

የለም ! አንድ ብር ቆርጫለሁ!" አለ ሁለቱን ላሮች የያዘው ቀኝ እጁን እየዘረጋላቸው ።

"በምን ምህኖት? ያበላሸኸው ራስህ! መልሰህ እኔኑ ለምን ትቆርጥብኛለህ? በህግ አምላክ!...በባንዲራው! ...በመንግሥት! ...በኋላ በምን ተከሰስኩ እንዳትል..."

ራፖር ፀሐፊው ከተቀመጠበት ወንበር ብድግ አለና "አሁን ከቤቴ ይውጡ! ካለበለዚያ ግን ሆን ብለው ስራየን በማንቋሸሽና እንዲሁም አለአግባብ የግራዝማች አበጋዝን ስም ለማጥፋት በማን አለብኝነት ተነሳስተው ለፈፀሙት ወንጀል አንቀጽ ጠቅሼ ፡ እዝባር አድርጌ የአስቸኳይ ክስ ማመልከቻየን ለአውራጃው ዐቃቢ ህግ አቀርባለሁ!

"እንዲያውም ከማን እንደተላኩ ሳይታወቅ 'ተንገላታሁ...ተረገጥኩ...' እያሉ ለድሃ የቆመውን መንግሥት ፍትህ እንደማይሰጥ አድርገው የሚያማርሩ በመሆንዎ በጥብቅ እንዲመረመሩ ለአውራጃው ፖሊስ ህግ አስከባሪና የፀጥታ ሹም በአስቸኳይ አስታውቃለሁ ። ይሄን ይወዳል መርጊያው!... እማኞች መቁጠር አለብኝ ። አንዲ አንቺ ትሆኛለሽ!" አለና ጣቱን ወደ ሴትዬዋ ቀሰረ ። "ሌላ... ሌላ ..." ብሎ ወደበሩ ወጣ ሲል በአስፈሪው አነጋገሩ ስጋት የገባቸው አባ እንቀርሻው ጠረጴዛው ላይ የነበረውን ሁለት ብርና ዶሴአቸውን ይዘው ሹልክ ብለው ወጡ ። በጥድፊያ ...

በርቱዕ አንደበቱ ተጠቅሞና በጥራዝ—ነጠቅ ቃላት ባለጉዳዩን ከቤቱ አስደንብሮ ለማባረር የቻለው ራፖር ፀሐፊ እየፈገገ ሰባራ መነፅሩን አወለቀና ወንበሩን ያዘ ፣ ወደ አዲሷ

ባለጉዳይ ፊቱን አዙሮ ።

* * *

ጥልቅ ሃሳብ የገባቸው አባ እንቀርሻው አለ አግባብ የሄደባቸው አንድ ብር በቁጭት አብሰለሰላቸው ። ቂጥለው ምን ማድረግ እንዳለባቸው እያሰላሰሉ ሾየጁ አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ቢሮ ወደሚገኝበት ግቢ አዘገሙ ።

"ይሽን ሁሉ ወረቀት ይዤ ወደ እዛጮ ቀርቢ፣ በቃሌ ጭምር ባስረዳ አይቀበሉኝ ይሆን? መከራ በልቼ ያላደግኳት አንዲቅ ምርኩዜ ክብሯ ተደፍሮ ስትሞትና ያለቀባሪ ስቅቅር! እኔም ደሀ ጧሪ ስዋትት ዳኛ የለም ባገሩ?" እያሉ ራሳቸውን አጥብቀው ይጠይቃሉ ።

ወዶ ፖሊስ አዛዥ ቢሮ ሲያመሩ ሽንጡ ላይ ሽጉጥ ያገነደረ ረዥም ደረቱ—ሰፊ ፖሊስ ገላመጣቸው ። ችግራቸውን ሊያስረዱት ቢሞክሩም ሊያደምጣቸው ፈቃደኛ አልሆነም ። ከልክለው ደግሞ አልከለከላቸውም ። እጅ እጃቸውን ያያል ። ምንም የማይወጣቸው መናጢ ድሃ መሆኛቸውን ሲያውቅ ግን ተጠይፏቸው ከአጠገባቸው ዘወር አለ ።

አባ እንቀርሻው ጠደፍ—ጠደፍ እያሉ ወደ ፖሊስ አዛዥ ቢሮ ተጠጉ ። ዘንጋቸውን አስቀመጡ ። የነተበ ጋቢያቸውን በባለ —ጉዳይ ደንብ አጣፍተው በልበናቸው ፈጣሪያቸውን ተማፀኑ ። የቢሮውን በር ገፋ አድርገው ገቡና ሰጥ ብለው ወለሉን ሳሙት ። በፍርሃት የሚብረከረከው ጉልበታቸው ሊከዳቸው ተቃረበ ።

ከፊት ለፊታቸው ፊቱን የሐምሌ ደመና አስመስሎ የሚመለከታቸው የፖሊስ አዛዥ ሻለቃ ደግሞ በአግራሞት

አስተዋላቸው ። ከአባ እንቀርሻው ዓይነት ጐስቋላ ሰው ጋር በቢሮው ሲገናኝ የመጀመሪያ የሆነበት ይመስላል ። ከላይ እስከ ታች መዘናቸው ። ያላበውን ማጅራቱን በመሃረቡ እየጠራረገ ሲቃኛቸው — አባ እንቀርሻው እጆቻቸውን የኋሊት አጣምረው አቀረቀሩ ።

"ምን ነበር?" አለ ሻለቃው ግራ እጁን አገጩ ላይ አስደግፎ ። ግራ እጁ ጣቶች ላይ የተሰኩት የወርቅ ቀለበቶች ዓይን ይስባሉ ።

በአክብሮትና በፍርሃት መላ ሰውነታቸው የታመሰባቸው ባለ—ጉዳይ አሮጌ ጋቢያቸውን ገለጥለጥ አድርገው ከብብታቸው ሥር ዶሴአቸውን መዘው አቀበሉት ። ክላሩ አዲስ ነው ። ወረቀቶቹ ግን በላቦት ጠቁረዋል ። ከመላሸቃቸው የተነሳም ሶስት — አራቱ እንደ አነባብሮ የተጣበቁ በመሆናቸው ማላቀቁ ፈተና ነው ።

ፖሊስ አዛዥ የተቀበለውን ዶሴ ገለጥ ሲያደርግ ፣ የሆነ ጠረን አፍንጫውን ሳይወጋው አልቀረም ፣ ከፉኛ አነጠሰው። መሃረቡን አውጥቶ ፊቱ ላይ እያራገበና እየተጠየፈ በሁለት ጣቶቹ ገለጥለጥ አደረገው ፣ የሚያነብ ለመምሰል ያክል። ከዚያም ቀናብሎአያቸውና "ምንነበር?" አላቸው—እንደገና።

"አዩ ጌታየ ! ምኑ ተነግሮ ! ...ነገሬ ብርቱ ነው" አሉትና ዝም አሉ ።

ከላሰሩን አጥፎ ከፊት ለፊቱ ገፋ በማድረግ "ግዜ የለኝም ። ጉዳይዎን ባጭሩ ይግለፁልኝ!" አላቸው ።

"ክስ ነው ።"

"ማንን ነው የከሰሱ? ለምን?"

"እየ ጌታየ! ዶሴየ ይናገረው ! እኔ ላወራዎ ውዬ ፣ ላወራዎ ባድር የሚያልቅ አይደለም" አሉት አባ እንቀርሻው — በደፈናው ። ያ ራፖር ፀሐፊ ያነሳባቸውን የአፍ—እልፊት እንዳይደግሙ ፈርተዋል ። "ተበደልሁ ፣ ፍትህ አጣሁ ፣ የድሃ ብሶትና እንባ ለባለ አዱኛና ለሹም የገለባ ያህል እንኳ የሚከብድ አልሆነም ..." እያሉ የልባቸውን ያህል ካልተና ገሩ ክሳቸው ሰሚ እንደማያገኝ ቢያውቁም ፣ ሊያፈልቁት አልቻሉም ።

"ይህን ዶሴ ገና አንብቤ..." አላቸው ሻለቃው ዶሴአቸውን በጥላቻ ዓይን እየተመለከተው ፣ "ጉዳይዎን እንድረዳልዎ ካሰቡ የማይሆን ነው ። ግዜ የለኝም ብየዎታለሁ' እኮ !"

"ረጋ ብለው ያንብቡታ! እኔ ከታዛ ሆኜ እጠብቃለሁ።"

"እንዲያማ አይሆንም! ሌላ ቀን ይዘውት ብቅ ይበሉ !" ብሎ ክላሰሩን ገፋላቸው ።

አባ እንቀርሻው ለጥ ብለው እጅ ነሱና "መቼ ልምጣ?" አሉት ።

ነገ...ከነገወዲያ...ሳምንት...የዛሬ ወር...ማለቂያ የሌለው ቀጠሮ ።

* * *

አባ እንቀርሻው የፖሊስ ጣቢያውን የውጭ በር አንቀው ቀሩ ። ወደ ውስጥ እንኳ የሚያስገብቸው ሳያገኙ ውሎአቸውም ሆነ አዳራቸው እዚያው ሆነ ።

ሲጀምራቸው አላወቁትም ። እንኳን እሳቸው ሌላውም ልብ ያለው ከብዙ ግዜ በኋላ ነበር ። አባ እንቀርሻው ወፈፍ

አደረጋቸው ። ከጋቢያቸው በቀር ልብሳቸውን ጣሉ ። ዶሴያቸውን ግን ከደረታቸው አይለዩም ።

"አባቴ...ስምዎ ማነው?" ይሏቸዋል የሚያውቋቸው ፣ ሳቅ ሲያምራቸው ።

"ስሜ?" ይሉና አባ እንቀርሻው "አምና !" በማለት ግንኙታቸውን ይገልፃሉ ።

"ያባትዎስ ስም?"

"አቻምና!"

ክፉ ቃል አይወጣቸውም ። በአጫዋችነታቸው ትልቅ—ትንሹ ወደዳቸው ። ሳንቲም ሆነ ፍርፋሪ በአሮጌ ጋቢያቸው እየተቀበሉ የመንገድ ዳር ዚቀኛ ሆኑ ።

"ጎጆ አለዎ አባቴ?"

"እንዴታ! ሰማይ ጣራዬ ፣ ፈረስ መግሪያ ግድግዳዬ!"

"ሚስትዎ ማን ትባላለች ?"

"ዘለቀች ፣ ገበያ ሂዳብኝ ሳትመለስ ቀረች ።"

"ልጅዎስ?"

"ፈጠነች!...ፈጠነች!" ሲሉ ይጠሩና "አረፍ በሉዋ...ቡና ታፈላለች" በማለት የከበቡዋቸውን ያስቃሉ ። መልሶቻቸው ምንጊዜም አጫጭሮች ናቸው ።

"አባት ምን ይበላሉ?"

"አንጀት!"

"ምን ይጠጣሉ?"

"ሀሞት!"

"እስቲ ያንጉራጉሩልን!..."

"ምን ከፋኝ!" ይሉና በሽካራ ድምፃቸው

“አቻምና አምናን ወልዶ
አምና ሚስት አገባ
ዘለቀች...ዘለቀች...ዘለቀች
ዋይ! ...ዋይ! ...ዋይ!...
ፈጠነች...ፈጠነች...ፈጠነች

እህህ...አሸሸ ገዳሜ!” እያሉ እንደ እስክስታ ይሞክራቸ
ዋል ። ዜማቸው ሁልጊዜም አንዲት ናት — ሙሾ ብጤ ።
ከዚያች በቀርም ሌላ ግጥም የላቸውም ።

“እህህ! እ! ...እ! እ...” ይላሉ አልፎ ።

“አባቴ ለምን ያቃስታሉ?”

“ተወግቼ ።”

“በምን?”

“በእንካሴ! ...አንካሴ ፡ ውላሴ ... አንካሴ ፡ ውላሴ ...
አንካሴ ፡ ውላሴ...” ይላሉ ለብዙ ደቂቃዎች ያለማቋረጥ ።

ይህኔ የከበቧቸው ህፃናት በአባ እንቀርሻው ዙሪያ ጡብ.
..ጡብ እያሉ ይቀበሏቸዋል ። “አንካሴ ፡ ውላሴ...አንካሴ ፡
ውላሴ...አንካሴ ፡ ውላሴ...” ከመሀላቸው አንደኛው በአንካ
ላው እግሩ መሬት ቢነካ ወይ ቢወድቅ “እስክትወጣ ነብሴ!”
ሲሉ ያጨበጭቡና “አንካሴ ፡ ውላሴ...አንካሴ ፡ ውላሴ...”
ይቀጥላሉ ።

አባ እንቀርሻው እንዲህ እንዲህ እያሉ የመንደር ልጆች
አጫዋች ሆነው ኖረው አንድ ቀን ማለዳ ላይ ጋቢያቸውን
አስተተው ከሚቀምሉበት ቆሻሻ መጣያ አጠገብ ዶሴአቸውን
እንደተንተራሱ አሸለቡ ፡ እስከወዲያኛው ።

ለተስፋሁን አበራ (መምህ

1982—ወልዲያ

የማከያው ጥያቄ

ማከያው የእድር ለፋሪ ነው ። በወልዲያ ከተማ እሱን የማያውቅ ማንም የለም። መሬት ሊነካ ጥቂት የቀረው ረዥም የፖሊስ ካፖርት ለብሶ አጭር ወፍራም የብሳና ብትር ይይዛል። ጡሩንባውንም ከእጁ አይለያትም። ከአባቱ የወረሳት ይቺው ጡሩንባ ለረዥም ዘመን አብራው ኖራለች።

የእለት ጉርሱን የአመት ልብሱን የሚችለው የእድሩ አባል ወይም ታገሬው ሰው አንዱ ወይ ሲሞት ወይ የዘመድ ሞት ሲረዳ ወፍ ውሀ ሳይቀምስ ከመኝታው ተነስቶ አንዲትም የከተማዋ መንገድ ሳትቀረው እየተዟዟረ ከሷፈፈ በኋላ በሚያገኛት ሁለት ብርና በሽቀላ ነው። ሽክም ያነሳል፣ እንጨት ይፈልጣል፣ ይላላካል፣ ስራው ብዙ ነው።

በለስ ሲቀናው በተከታታይ ስራ ያገኛል። አመዳም እድሉ የባሰውን ስትገረጣ ደግሞ ወሩን በሙሉ ድፍን ብሎበት ይከርማል። ሚስት አለችው፣ አረጋሽ የሚሳት። ከአረጋሽ የወለዳት አንዲት የአራት አመት ልጅም አለችው። ከለመኗት የቆነጠሩላት የምታክል ይቺው ልጁን ‘ሆዲ!’ ይላታል። መንደርተኛውም ለምዶለት በዚያው ነው የሚጠራት።

የሚያገኛት ገቢ የጎጇውን ቀዳዳ አልደፍንለት ተላው መከራውን ያያል። አረጋሽም ታግዘዋለች፣ የሰፈሩን ጠላ ኮማሪዎች ቂጣ በመጋገር። ገቢዎ ግን የሚያወላዳ አይደለም። ከወረቱ ስንቁ የላቀ አይነኑ ነው። ሌሊቱን ቀኑንም ባጉታ

የምታገኛት ሶስት ብርና ሁለት ቁራሽ የአይንሽ ይፍሰስ መጠቃ ነው። ለዚያውም ስንት ደጅ ጠንታ!

ማከያው ግን የሱን ለሱ ትቶ፣ የወለደ ይፍረደኝ ሆኖበት የሆዱ አሳብ ይጠናበታል ። ሆዱ አንጀቷ ታጥፎ ፣ ላይዋ ላይ ያለቀ ዝተት የመሰለ ጥብቆዋን ለብሳ፣ አይን አሯም፣ ንፍጧም፣ ለሀጯም የዝንብ ነፍጠኛ እያጋፈረ ፍዝዝ ድንግዝ ብላ ሲመለከታት ሆዱ ይላወሳል።

ንፍጧን ጠርጎ፣ ፊቷንና እግሮቿን አባብሶ አጥቦ ደጋግሞ ይስማታል። ግንባሯን፣ ጉንጯን የእጆቿን መዳፍ ሁሉ እያገላበጠ ይስማል። ጥብቅ አድርጎ ያቅፋታል። ጭኑ ላይ አስቀምጦ ሆዷን እየከለከለ ሊያሳስታት ይሞክራል። ለቅፅበት ፈገግታዋ እንደ ትል እሳት ቦግ ብሎ እልም ይላል። በስጋትና በፍርሀት ትዋጣለች። ያኔ እንባው ይመጣል።...

እና ኑሮአቸው ይኸው ነው፣ ምንጊዜም። ማከያውም ሆነ አረጋሽ አፋቸውን ሳይሽሩ ከቤት ይወጣሉ። የቀንኛውም ቢሆን የማታው እንደተገኘ የሚጐርስ እንጂ ስሙ አለ ብር አድሩስ አይጠራም።

ጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ወታደር የነበረ የአቶ ሺበሺ ትልቅ ልጅ ጦር ግንባር ወድቆ ለእድርተኞች በመለ ፈፍ ሁለት ብር ካገኘ ወዲህ ሌላ አላጋጠመውም። ድፍን ሳምንቱ። በወልዲያ ከተማ የጥቅምት ወር ብርድ የዋዛ አይደለምና አረጋሽም ስራ ፈታለች። ወሩ ከገባ ጀምሮ የጎጀአቸው ውሎና አዳር ትልቅ ፈተና ሆኖባቸዋል። ከመቸውም የከፋ።

አዳጎ አካባቢ አንድ የዝሀ ነጋዴ እህት ሞታለች ተብሎ

ቤተሰቦቹ በሀዘን ላይ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ወደዚያው አዘገመ፣ እድርተኛው ወደ ሀዘን ቤቱ ከሚወስደው ምጣፍ ትርፍራፊ ለማግኘት።....

እንደደረሰም ጎንበስ ብሎ ድንኳኑ ውስጥ ገብቶ ጥግ ላይ ከሚገኘው አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጠ። አጠገቡ የነበሩ ሰዎች የሙፈ ክርክር ይዘዋል። የሚቹ ቤተሰቦች በተነጠፈው ፍራሽ ላይ ተቀምጠው በሀዘን ይወዛወዛሉ።

ማከያው በሁለት እጆቹ አገጩን ደግፎ ዙሪያ ገባውን ይማትራል። ጠላ የሞላ ማንቆርቆሪያ ይዘው በድንኳኑ ውስጥ የሚዘዋወሩት አስተናጋጆች አላዩትም። ቢያዩትም ቁብ አላሉትም። አንዲት ስንጥር ከወለሉ አንስቶ አፈሩን መጫር ጀመረ።

በአንድ እጁ ማንቆርቆሪያ፣ በሌላ እጁ መጠጫ ብርጭቆዎች የያዘው የሰፈሩ የሳር ፍራሽ ሰፊ፣ አብጤ፣ ወደ ማከያው ተጠጋና "ይቺን ዥው አድርግና ውልቅ!" አለው የጉሽ ጠላ በብርጭቆ እየቀዳላት።

ማከያው ቀና ብሎ ተመለከተውና አቀረቀረ። የፍራሽ ሰፊው አነጋገር ትርጉም አልገባ አለው።...

በርካታ እድርተኞች እንጀራ በሰፌድና በትሪ፣ ወጥ በድስትና በስክ ሰሀን ይዘው ወደ ደንኳኑ መግባት እንደጀመሩና የሰው መበራከትን እንደተመለከቱ የነጋዴው ባለቤት ለቅሶ ጀመሩ፣ ደፋ ቀና እያሉ።

"የኔ ቀብራራ

...ቀብራራዬ!

የኔ ቅምጥል

…ቅምጥሌ!
ገንዘብ አፈሩ!
እስከነ ክብሩ!
ተነ ማእረጉ!
ዋይ!…ዋይ!…ዋይ!''

በሰለለ ድምፃቸው አጠገባቸው የተቀመጡት ሀዘንተኞችም ያልነመጉማሉ። በጋቢያቸው ጫፍ የጨመቋቸው አይኖቻቸውን ይጠርጋሉ። አብዛኞቹ ደጋግመው ይናፈጣሉ።

የሚቹ ባለቤት የሀዘን እንጉርጉሮአቸውን ሲቀጥሉ ማከያው አላስቻለውም ። ''እንዴ ! 'አይገባም!… ተዉ! የሚላቸው ሰው የለም?'' በሚል ስሜት ተቁነጠነጠ። ወደ ሚቹ ቤተሰቦች ጠጋ ብሎ ለቅሶአቸውን እንዲያቆሙ፣ በባህል የተለመደውን ግሳጼ ሊያስተላልፍ ፈልጎ ከመቀመጫው ብድግ ከማለቱ ፍራሽ ሰፊው ''ጥጋበኛ! ጠላህን ጨልጥ! ብርጭቆውን ልወስደው ነው። በአንድ ትንፋሽ! ከዚያም ወደ ቤትህ!'' አለው አመልካች ጣቱን ወደ ማከያውና ወደ ጠላ ብርጭቆው እየቀሰረ።

ደንገጥ ብሎ ''እረእኔ ላስተዛዝናቸው ብዬ እንጂ ሌላም አይደለም!'' ሲል ማከያው ለስለስ ባለ አነጋገር መለሰለት።

''እንግዲህ አርፈህ ቁጭ በል! አንተ መለፈፍ እንጂ ማስተዛዘን ላይ ምን አገባህ! እረፍ!''

ማከያው ሀፍረት እያሸማቀቀው ተመልሶ ተቀመጠ። የፍራሽ ሰፊው አባባል ይበልጥ ከነከነው። በተለይም አጠገቡ ያሉት ሰዎች ምልልሳቸውን ስላደመጡበት ተሸማቋል። ''ምን በደልኩት የሚያዋርደኝ!?'' አለ ለራሱ። በድህነቱ፣በእርዛቱ

ተማረረ ። ማሰብ ጀመረ ፡ ውል ያለው ሀሳብ ባይሆንም ።…

በሀሳብ ሲብሰለሰል በግራው በኩል የሚያናግሩትን አዛውንት እንኳ ልብ አላላቸውም ። ምሰሶው ላይ ተሰቅሎ ብርሀን ከሚፈነጥቀው ፋኖስ ላይ አይኖቹን ተክሎ ያሰላስላል።

''እስቲ አሁን ምን አገባው? እሱስ እንደኔ ለቅልውጥ አይደል የመጣው! ቅልውጥ ፀያፍ የሚሆነው አመል ሲሆን ነው እንጂ ፡ ለድህ ምን ያስነውርበታል ? ምንስ በደልኩት?

ብቻውን ማውራቱን ቀጠለ። ግንባሩ ላይ ላብ ችፍፍ ብሏል ። በአደባባይ የተዋረደ ያክል ተሰምቶታል ፡

''እኔም ቆሎ ቢያርብኝ፣ እሱም ቢያርበት እንጂ የሞቀ ጎጆ ቢኖረንማ ሁላችንስ መች እዚህ እንደርስ ነበር? የደንቡን አዝነን በተመለስን! ለመሆኑ ምን በደልሁት?…. እስራ ዘጠኝ አመት ለእድሬ አላገለገልኩም?…''

የመጣበትን እንባ ለመመለስ አንዲት የተጣጣፈችና የቆሸሸች የቀሚስ ቁራጭ ከካፖርቱ የውስጥ ኪስ አውጥቶ አይናቹን ጠራረገ። የጠላ ብርጭቆውን አነሳና ተነነጨ። መልሶ አስቀመጣት።

ፍራሽ ሰፊው ከንፈሩን እየነከሰበት ማከያው እግር ስር የነበረችውን ብርጭቆ አነሳና የነበራትን ጠላ ደፍቶ ''ጠላ ቤት አደረግከው?'' አለው በግልምጫ።

ማከያው የባሰውኑ ሀሳብ ገባው። በፍራሽ ሰፊው አያያዝ ለአረጋሽና ለሆዴ ይዞላቸው ሊሄድ ያሰበውን ትራፊ ፍርፋሪ ሊከለክለው እንደሚችል ታየው። ጭንቀት አደረበት። አብዛኛውን ጊዜ ከሀዘን ቤት፣ ከሰርግ ቤት፣ ከድግስ…የ

ትርፍራፊ አለቆችን እያስፈቀደ በትልቅ ፕላስቲክ ከረጢት ሞልቶ ይሄዳል ። ያንን ትራፊ ትርፍራፊ በልተው ፡ አረጋሽ የትራፊውን ትርፍራፊ በጥንቃቄ ካስቀመጠች በኋላ ቡና ታፈላለች ። የጠላ ቂጣ ቁርስ ታቀርባለች ። በእንዲህ አይነቱ ምሽት በዚያች ደሳሳ ጎጆአቸው ደስታ ይሰፍናል ። ባልና ሚስቱ ''ተመስጌን!'' በማለት ዘና ይላሉ ፡ እንቅልፍ እስኪወስዳቸው ወይም የአንድ አምሳል አንድ አካል ተፈጥሮ አዊ ግዴታቸውን መፈፀም እስኪጀምሩ ድረስ ።

የፍራሽ ሰፊው ሁኔታ ግን በጣም አስግቶታል ። ሆን ብሎ በሚፈጥርበት መሰናክል ከዚህ የሀዘን ድንኳን ተስፋ የጣለበትን ትርፍራፊ ካጣ የአረጋሽና የሆዴ ሁኔታ ታየው። ረሀብ አንጀታቸውን አጥፎ፣ አፋቸውን ሸብቦ በጎጆአቸው የሚያንጎራብበውን የሀዘን ድባብ ላለማየት ወሰነ። ከፍራሽ ሰፊው ቅይታ ተሰውሮ ፡ ትልቅ ሳፋ ታቅፈው ትርፍራፊ ወደሚሰበስቡት አሮጊት የሚደርስበትን መንገድ ቀየሰ ።

ከመቀመጫው ተነስቶ ጥግ ጥጉን አድርጎ ወደ አሮጊቷ ተጠጋና ''እማማ እርጎየ! ለሆዴ የሚሆን እስቲ ...ጉንሽ ትርፍራፊ ብጤ፣...'' በብትሩ መሬቱን እየጫረ ጠየቃቸው።

''ማነህ? ማከያው! አየ ግዜ!...ዋ! ድሮ አባትህ የናጠጠ ነጋዴ ነበር ። ምን እንደነካው ሳይታወቅ አይምሮው ውሉን ሳተ። ከስንት እመም በኋላ ተሸሎት የእድር ለፋፊ ሆነ፤ እዚችው ወልዲያ፣ እዚችው አዳጎ። ታዲያ በጥጋቡ ግዜ አንገት አልፈጠረለቱም ነበር አሉ። የአባት ሀጢያት ለልጅ አልፎ ይኸው አንተኑ ይቀጣህል ጌታ!...'' ብለው ከንፈራቸ

ውን መጠጡ ። አሮጊቷ ጉልበታቸው እየተንቀጠቀጠ ተነሱና አጠገባቸው ካለው የእንጀራ ቁልል ሁለቱን አጣጥፈው ፕላስቲክ ከረጢቱ ውስጥ አደረጉለት ። ሳፋው ላይ ከተቆለለው ትርፍራፊም በሁለት እጆቻቸው እያፈሱ ጨመሩለት ።

በፕላስቲክ የተጠቀለለውን ምግብ በግራ እጁ አቅፎ፣ አጭር ወፍራም ብትሩን በቀኝ እጁ ጨብጦ ፍራሽ ሰፊውን በአይኖቹ እየማተረ እየተጣደፈ ሹልክ አለ ። ከድንኳኑ መግቢያ በግራ በኩል የተከለኩትን በርካታ ጎስቋሎች በፍጥነት አለፋቸው ፡ መሀል ለመሀል አቋርጦ ።

''ቁም!..ሌባ!'' የሚል ድምፅ ጆሮው ላይ ጥልቅ ሲል በድንጋጤ ዞሮ አጭር ወፍራም ብትሩን አቀና። ፊት ለፊቱ የተገተረው ፍራሽ ሰፊው ነበር።

''አንተ ባለጌ! እንጀራ ሰረቅህ አይደል?'' አለና ፍራሽ ሰፊው አፈጠጠበት የብረት ከዘራውን እየነቀነቀ ።

''ወንድሜዋ...ምን በድየህ! ምን የሚሉት ቂም ነበረ ብህ?'' አለ ማከያው፣ በማሳዘን ቅላፄ። ብዙ ቢያስብና ቢብሰለሰልም ፍራሽ ሰፊው እሱን ለመጥላት ያለውን መንስኤ ለማወቅ አልቻለም። የፍራሽ ሰፊው አማት ከሁለት ወር በፊት ሞተዋል። ይህን ሞታቸውን ለእድርተኞች ለፍፎለት የደንቡም ተከፍሎታል። እሱ ራሱ እንኳ ከዚያች ከተከፈለችው ሁለት ብር ፣ የሀምሳ ሳንቲም ጠላ ገዝቶ አስተዛዝኖታል። ከአረጋሽና ከሆዴ ተለይቶ አንድ ሌሊት አብሮት አድሯል። በሶስተኛው ቀንም የሀዘን ድንኳን ሲፈርስ ፡ ምንም ግዴታ ሳይኖርበት ፡ ከተለያዩ ቤቶች በትውስት የመጡ እቃዎችን አጓጉዘለታል ።

"ደግሞ ምን በደልኩህ ትላለህ? የሰው መሳቂያ አላደረ ግኸኝም?" አለው አብጤ ፡ ፍራሽ ሰፊው ።

"እንዴት አድርጌ?"

"አግቴ የሞቱ ጊዜ መላ ከተማዋን እየተዘዋወርክ መለፈፍ ሲገባህ በነግራዝማች አበራና በቆሻሻ መጣያው ግድም ዞር ዞር ብለህ በመመለስህ እድርተኞቹ ሁሉ ሳይሰሙ ቀሩ ። የመጣው ሰው በጣም ጥቂት ነበር! እ?...ይህ በደል አይደለም ?"

"እረ ተው፣ አለ ስራዬ ስራ አተስጠኝ!?"

"ዝም በል!" አለና ፍራሽ ሰፊው የብረት ከዘራውን ሜፍ ግከያው አይናች ላይ አድርሶ መለሰው። ቀጠለና "ሰው ጋር እንደግልወዳጅ፣ አገር እንደግይወደኝ፣ ለሰው መጥፎ እንደሆንኩ ተደርጌ የተቆጠርኩት ባንተ ምክንያት ነው። እድ የሰጠኝ ደበስም ትንሽ ነው። ምን ይህ ብቻ!? ሶስት ቀን ሙሉ በሀዘን መኮራመቴ እንዳይበቃኝ 'አልሰማንም! ማን ነግሮን?' እያለ በየቀኑ የሚመጣውን እድርተኛ ስቀበል ስራ አሞስፈታኸኝም! እ? ከዚህ በላይ ምን ልታደርገኝ ትፈልጋለህ! አህያ ካላረድክብኝ ነው!"

ፍራሽ ሰፊው የብረት ከዘራውን ደጋግሞ ነቀነቀ ግከያውን ላይና ታች እየገላመጠው። "ስራየም አይደል ወንድሜ! በሀግ አምላክ!..." አለና ግከያው ራመድ ሲል ፍራሽ ሰፊው የካፖርቱን ክላድ ጨምድዶ አስቆመው።

"ልብ አድርግ! ዋ! ሌላም የሰግሁብህ ጉድ አለ። መቃብርህን እየማስክ ነው። ተጠንቀቅ!!" አለና ፍራሽ ሰፊው ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው ።

የፍራሽ ሰፊው ዛቻ ግከያውን ጤና ነሳው። ይህን ያህል ያስፎከረውና ተፈፀመብኝ የሚለው በደል እስከዚህ የሚያናክስ ሆኖ አላገኘውም ። ሌላ ምስጢር ቢኖር ነው እያለ የሆዱን በሆዱ ይዞ ጥቂት ቀናት አላለፈ።

አንድ ቀን ከቀትር በኋላ ፡ ግከያው በለስ ቀንጭት እንጨት ፈለጣ አገኘ ። በፊቱና በግጅራቱ የሚንቆረቆረውን ላቡን እየጠረገ የቀረበለትን ግንድ ሲሸነሽን ውሎ ግታ ገደግ ሳንቲሙን በእጁ ሲያስገባ ውሻ በቁልቁለት የግይጎትተው ገብስ እንጀራ ከወፍራም ሽሮ ጋር ተጨግሪ ተሰጥቶት ያን በጣሳ ውሀ ካወራረደ በኋላ ፈጣሪውንና አሰሪውን አመስግኖ ወጣ።

ምሽት ላይ ከአረቄ ኮግራቷ ከየዋግነሽ ቤት ጎራ ብሎ በመዝናናት ላይ ሳለ የልብ ወዳጁ አባ ምትኩ ሪዛቸውን እያፍተለተሉ ገብተው ከጎኑ አረፍ አሉ። እውቅ ሽግኔ ናቸው። ጥሩ ገቢም አላቸው። ታዲያ እግራቸውን ከሽግኔ ጉድጓዳቸው አያውጡ እንጂ ካወጡ እግር ተወርች አስሮ የሚመልሳቸው ጎበዝ ይፈልጋሉ። አላፊ አግዳሚውን ይጎትታሉ፤ ይጋብዛሉ። ጠላው፣ ጠጁ፣ ካቲከላው፣...ምኑም አይቀራቸው። ያገኙትን ሁሉ ሲጨልጡና ገንዘባቸውን ሲረጩ አምሽተው ከቤታቸው የሚገቡት ሰአት እላፊ በሽክም ነው። በእጃቸው ያልጠጣ የለምና ሁሉም ይወዳቸዋል።

አባ ምትኩ ሌላም መስህብ አላቸው። ውሎዋቸው ከመንደር ሴቶች ጋር በመሆኑ ይመስላል፣ ወሬ አያመልጣቸውም። በወልዲያ ከተማ ተደረገ፣ ተወራ የተባለው ቀርቶ መንዝና ገመገም ተሻግሮ የሚመጣላቸውን ትኩስ ዜና ለመስ

ግት የሚከባቸው ሰው ብዙ ነው።

"እህሳ፣ ማከያው ደህና አመሸህ?" አሉት፣ ዘንጋቸውን ከጎናቸው እያስደገፉ። ግሳት ግሳት ይላቸዋል።

"ይከበር ይመስገን፣ አባ ምትኩ" አላቸው ማከያው ብድግ ብሎ እጅ በመንሳት።

"የዋግነሽ!" ድምፃቸው ከጣራ በላይ ነው።

"አቤት አባ ምትኩ" ስትል ከጓዳ ብቅ አለች።" ደህና አመሹ?"

"ካቴሽ እንዴት ነው? ሆዴን ነፍቶኛል" እያሏት እጃቸውን በጋቢያቸው ስር ልከው ሆዳቸውን ቸብ ቸብ አደረጉ ። ተቆዝሯል ።

"ትኩስ ነው" አለቻቸው የዋግነሽ ፣ ክፍሉ መሀል በተገተረች አንዲት አንካሳ ጠረጴዛ ላይ ተደፍተው ከተኮለኮሉት መለኪያዎች አንዱን እያነሳች ።

"የአበዛሽ ጠጅ በተሃ ሆነብኝ ። ቀደም ሲል ደግሞ ጉሽ ጠላ ቀምሼ ነበር ቀብትቶኝ ጎንበስ ቀና ማለት እንኳ አቃተኝ" አሉ አባ ምትኩ ። ጋን ጋን ይሽታሉ ። ምላሳቸውም እንደመኮላተፍ ብሏል ። "በብርሌ አድርጊው ።"

የዋግነሽ ብርላዊን ሞልታ ገሙ አደረገችላቸው ።

"ለማከያውም ቅጂ ። አንቺም ያዥ" አሏት አባ ምትኩ፡ የተሞላላቸውን በአንድ ትንፋሽ አጋብተው ድጋሚ እያስቀዱ ።

"አዬ አባ መስጠት!" ሲል አሞካሻቸው ማከያው ።

"አባ ዝናብ በላቸው እንጂ!" አለች ኮማሪትዋም ።

"በየገቡበት ሳያርከፈክፉ አይወጡ ።"

አባ ምትኩ ኩራት ኩራት አላቸው ። ደጋግሙ ። የተጋባዦቻቸውም መለኪያዎች የሚጋቡት በቅልጥፍና ነበር ና ሌላ ቀረበላቸው ።

"ምናባቱ!" አሉ አባ ምትኩ ፣ "ድህነት ውሉን አይስትም ። ሲያገኙ አብሮ መብላትን ፣ መጠጣትን ፣ መደሰትን ፣ ሲያጡም አንጀት አስሮ ማደርን ለምደነዋል ።"

"ብቻ ጤና እንሁን!" አለች የዋግነሽ ፣ ምላሷን እየመጠጠች ።

"አዎ ፣ ዋናው ጤንነት ነው" አለ ማከያውም የበኩሉን ሀሳብ ሲዘንዝር ። "አዱኛ ጤዛ ነው ። ባለው ጊዜ ያላካፈለ ፣ ባጣ ጊዜ ማ ሊደርስለት?"

"አዬ ተወኝ ባክህ! በዛሬ ዘመን ሁሉም በልቼ ልሙት ብሏል ። እንዲህ በጉ በጉውን የሚያስብ የታል ብለህ?" የአባ ምትኩ ቅሬታ ነበር ። "ሰው ለሆዱ ተገዥ ሆኗል ። ጆሮ አይሰማው ፣ አይን አያየው የለ ፣ ብዙ ጉድ እየታዘብኩ ነው" በማለት አባ ምትኩ ለወሬ ምላሳቸውን ሲገሩ ማከያውና የዋግነሽ ጆሮዎቻቸውን ቀሰሩ ።

"በጉድ ዘመን ተፈጥረን…" በማለት ማከያው ለማሚ ሚቅ የጀመረውን ሀሳብ ሆን ብሎ አንጠልጥሎ አስቀረው ።

አባ ምትኩ በልባቸው ያመቁትን ለመዘርገፍ ቸኩለ ዋል ። "መቼስ" አሉ ወገባ ያደረሰ ጉን መለኪያ እንደጨለጡ "ጉድና ጅራት ከወደኋላ እንዲሉ ፣ ፈጣሪ እድሜ ከሰጠን ብዙ ጉድ ወደፊት እንሰማለን ፣ እናያለን ።"

መለኪአቸውን አጋብተው አስቀመጡ። ማከያው ሞላላ ቸው። የራሱንም አንጠፍጥፎ ከሞላ በኋላ "በእኔ ሂሳብ ደግሞ አንድ ብርሌ አምጪ!"አላት የዋግነሽን ። እሷም ወሬው እንዳያመልጣት ተጣድፋ ከመቅፅበት አቀረበች ።

"ሰው ተበላሽቷል" በማለት ጀመሩ አባ ምትኩ ። "በያ ሰሞን አንዲት የወረኢሉ ሴት እየሀ መጥተው እህታቸው ዘንድ አርፈው ነበር ። እና በጨዋታ አንዱን ስንጥል አንዱን ስናንጠለጥል የእድር ነገር ተነሳ ።"

ማከያው ቀና አለ ። የዋግነሽም አሰገገች ።

"ታዲያ እኒያ ሴት ምን አሉኝ መሰላችሁ? 'በቀያችን ነጋ ጠባ ፣ እዚያም እዚህም መርዶ በዛና በመዋጮ ጓዳችን ተራቆተ ፣ የእድር ጥሪታችን ተሟጦ የጮሪዋ እየተያየን ነው' ሲሉኝ 'እንዴት?' አልኳቸው ። መልሳቸው ዘግናኝ ነበር ። 'የእድር ዳኛቸው ጎዘን ደረሰብን ከሚሉት ሰዎች ጋር እየተመሳጠሩ ፣ ያልሞተ ዘመድ ሞተ በማሰኘት ገንዘብ ይቀራመታሉ የሚል ወሬ በድንገት ተናፈሰ ። ደሀ ጉጉ ነው ። እንዴት ልበለዋ በሚል ፈሊጥ ያለ የሌለ ዘመዱን መግደል አመጣ ። በተለይ ብዚህ በጦርነቱ ፡ ወታደር የነበረ ወንድም ፡ አጎት ፣ አጣሁ የሚለው ሰው ቁጥር እያየለ ሄዶ አይናችን ፈጠጠ!' 'አዬ ሰው!' ብዬ ጆሮዬን በዝሀ ብጣሽ ጠቀጠ ቅሁ ።"

"ጉድ!ጉድ!" አለች የዋግነሽ ፣ ነገሩ ሰቅጥጧት ።

"እንዲህ ሆነን አረፍነው?" አለ ማከያውም ተደናግጦ ።

"ኤዲያ!" አሉ አባ ምትኩ ፣ "ለአንተማ ምን ክፋት አለው? በየቀኑ ጡሩምባህን መወልወል ነው ።"

የዋግነሽ ከትከት ብላ ሳቀች ።

"እኛ ዘንዳ እንኳ እንዲያ አይሆንም!" አለ ማከያው። ግን ፍላጐቱን መግታቱ ይሁን ወይም ድርጊቱን መቃወሙ ግልጽ አይደለም።

"ለምን አይሆን?" የአባ ምትኩ ጥርጣሬ ነበር። "በእኛ ሆነ በሌሎቹ ቀበሌዎች ዘንድሮ መርዶ አልበዛም? ክፉ ማሰብ ክፉ ያናግራል አትበሉኝ እንጂ ፣ እኔ አቶ ተገኔን ጠርጥሬዋለሁ" ብለው በሹክሹክታ መለኪአቸውን አነሱ ።

አቶ ተገኔ የቀበሌያቸው የእድር ዳኛ ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አመለኛ ሆነዋል በሚል ስሜት ሰፈርተኛው እየራቃቸው ነው ። ውሎዋቸውንና ማምሻቸውን ከማይረቡ ሰዎች ጋር አድርገዋል ። አንዱ ወዳጃቸው እላት የላሰው ደላላ አራጌ ሲሆን ፣ ሌላው ፍራሽ ሰፊው አብጤ ነው ። አራጌ የማይገባበት ጓዳ ፣ የማያቀባብለው ነገር የለም። በዚህም አድራጐቱ ብዙውን የአገሬውን ሰው አነካክቶ በየደረሰበት እርግማን ቀለቡ ሆኗል ። አብጤም ቀን ቀን የጭድና የጀንያ ፍራሹን ያገላብጥ እንጂ አገር በጨለማ ድባብ ሲሸበብ ፣ የአዳም ልጅ በእንቅልፍ አለም ሲታጀብና ቀየው ፀጥ ረጭ ሲል ወንዝ ያመጣው ግንድ በሚያንሸለው ክንዱ ቤት እየሰረሰረ እንደሚዘርፍ ሰው ደፍሮ ፊት ለፊት ባይናገረውም ቡና ይጠጣበታል ። በዚህ ላይ ሽማሌ ያሰለቸ ጠበኛ ነው ። እሱ በዞረበት መሸታ ቤት ሰው በራሱ ጉዳይ ተያይቶ ቢሰቅ "በኔ ነው የምትሰቀው? ምናባህንስ !·· እኔ ለበኑ!" ብሎ

ለግድያ ይገለገላል ። ድፍረቱንም ፣ ጉልበቱንም ያደለው በመሆኑ እንኳን ያልሞላለት ተደላደልኩ ያለ ባለጠጋም በአይኑ ሙሉ አያየውም።

"ተገኔ የተበላሸው ከአብጤና ከአራጌ ጋር ከገጠመ ወዲህ ነው" አሉ አባ ምትኩ ወደ ገቡበት ፍሬ ሐሳብ በመመለስ ። "አብጤ አማቴ አረፈች ብሎ በያ ሰሞን አስለፍፍህ የእድር ገንዘብ ኪሱ አስገባ ። የመዋጮ እንጀራውን አድርቆ አስወቅጦ ሲበላ ከረመ ። አማቱ ከሞተች አስር አመት ያለፈ መሆኑን ከሁነኛ ሰው ሰምቻለሁ ።"

"እኽ!" አለ ማከያው ፣ የሆነ ሐሳብ ብልጭ ብሎለት ። "መርዶ ነጋሪውስ አራጌ አልነበረ?"

"እያልኩህ! ሰው ኑሮ በዘዴ ብሎ የያዘው ይኸው ጉድ ሆኗል ።"

ምሽቱ እየገፋ ሄዶ ፈኋለማው ሰፍኗል ። የዋግነሽ መጠጡም ፣ እንቅልፉም ከብዷት አስራ ያፋሽጋታል ። አባ ምትኩና ማከያው ግን ገና እያንቆረቆሩ ነው ።

"ቡና ላፍላ?" አለቻቸው የዋግነሽ ፣ መቀመጡ ቢጨንቃት ።

"አይ! አይ!" አሏት ሁለቱም ፣ "ካቴሽ ማለፊያ ነው።"

"አንድ ብርሌ ለመንገድ በይን ። ሂሳቡም በእኔው ነው" በማለት አባ ምትኩ በመርፌ ቁልፍ የሰፉትን የእጀ ጠባባቸውን ኪስ በረበሩ ። ማከያው አላግደረደራቸውም ። አስር ብር የዋግነሽን አስጨበጧት ።

"እና ነገ ማለዳ ስራ አታጣም!" አሉት ማከያውን

በክርናቸው ጐሸም አድርገውት እየሳቁ ። ማከያውም ሳቀ ።

"ደሞ ምን መጣ?"

"አራጌ የእናቱን ሞት ሊረዳ ነው" አሉት አባ ምትኩ እየተንከተከቱ ።

"እሪ ባዛኟቱ!... ጉድ!" አለና ማከያው ጆሮውን ማመን እያዳገተው ። "ማ ነገረዎ?"

"ከነገረኝ ሰው ምን ጉዳይ አለህ?"

"አይ!...እንደው ..." አለ ማከያው በማቅማማት ፤ "ለጫወታው ብዬ እንጂ ... ምነ ፋይዳ አለው!"

መለኪያዎቻቸውን በፍጥነት ቁሜ ብድግ ሲያደርጉ ቆይተው ከዋግነሽ ቤት ወጡ።

"አባ ምትኩ" አለ ማከያው ፡ በመንገድ ላይ ሳሉ ፡ "ላምን አልቻልኩም ። ጊዜውን ዘነጋሁት እንጂ ፣ እናቱ እንደሞቱበት ከዚህ ቀደም ራሱ አራጌ አውስቶልኝ ነበር ። ትዝ ይለኛል ፤ ያሁኑ የዋግነሽ ቤት ይሁን ሌላ ቦታ፡ ተገናኝተን እንዲሁ እንደዛሬው ስንጫዋወት በዚያ በክፉ ዘመን ፡ በረሃቡ ወቅት እናቱ ባቲ መጠለያ ገብተው ሕይወታቸው ሲያልፍ እሱ ኩሊነት ይሰራ እንደነበር አውግቶኛል ።"

"እኔም የሰማሁት ይሄንኑ ነው" አሉት አባ ምትኩ ።

በዚሁ ተለያዩ ። ነገሩን እያብላላ ማከያው ብቻውን ወደጐጆው ደፋ ደፋ ማለቱን ቀጠለ ። የዚያ ቀደሙን የፍራሽ ሰፊው የአብጤን ዘለፋና ማስፈራራት ከዚሁ ጉዳይ ጋር አዛመደው ።

ቤቱ ከከተማው ጥቂት ወጣ ይላል ። የመንገዱ ግራና ቀኝ በባሕር ዛፍ ቁጥቋጦ የተጀቦነ ነው ። ገባ ብሎ ከተፀዳዳ

በኋላ ሱሪውን እያጠባበቀ ብቅ ሲል ሁለት ሰዎች ከቅርብ ርቀት ወደ እሱ አቅጣጫ ሲመጡ ተመለከተና አጭር ወፍራም በትሩን አጥብቆ ጨበጠ ። ልቡ ትር ትር አለች ።

"እንደምን አመሸህ ፣ ማከያው?" አሉት አቶ ተገኔ ፣ የእድር ዳኛው ። "ቤትህ ብንሄድ አጣንህ ።"

አብጤ ፍራሽ ሰፊው ፈንጠር ብሎ ቆሟል ።

"ባከህ ችግር ገጥሞናል ።" የአቶ ተገኔ መግቢያ ነበር ።

"ምነው? ደህናም አይደላችሁ እንዴ? ምን እክል ገጠማችሁ ?"

"እባክህ ንጋት ላይ ቶሎ በል!" አሉት አፋቸው እንደመ ተሳሰር እያለ ። "የዚያ የእድርተኛችን... ታውቀው የለ እንዴ? ያ...አራጌ ደላላው! እናቱ ሞተዋል ፣ ቶሎ በል!"

"እንዴት ሞቱ?"

"ምን ያደርግልሃል ? አጥብቀህ ስትጠይቅ አበ ልጅ ያለህ አትመስልም? ከአማሟታቸው ምን አለህ?"

"እረ በጉዴ ወጣሁ!" አለ ማከያው እየተልጮመ ጮመ ።

"ወይ ጥጋብ! አንተ ምናለብህ እናቴ! ያገሩ ሰው አንዱን ጠዋት ቀብሮ ሌላውን ማታ እየደገመ የእዝኑ ፍትፍት ላንተ ሰርግ ነው የሆነልህ ... ልብህ አበጠ ! ተበሪዱን ይስጥህ!"

"ምን አርግ ነው የሚሉኝ?" አለና እንደማፍጠጥ ብሎ አቋረጣቸው ።

"ደግሞ ምን ለማድረግ ያምርህ ኖሯል? ድሮውንስ ቢሆን ዝሆንና አውራሪስ አታድን ። እንደ ጋለሞታ መንደር

ለመንደር እያውደለደልህ ፣ ጡሩንባህን እየነፋህ ፣እድሜ ለሙታን ፣ እድሜህን ቀጥል እንጂ!"

"እረ ጉዱ!" አለ ማከያው ።

"መድሃኒአለም ለጉድጓድ ይዳርግህ ፣ አቦ!" አሉና ማጅራቱን አንዳች በሚያክል መዳፋቸው ይዘው "የ—ዚ—ያ የ—ደ—ላ—ላ—ው እ—ና—ት ሞ—ተ—ዋ—ል! የአራጌ!" ብለው ሲገፈትሩት ተውተርትሮ ቆመና ፈገግ ብሎ አያቸው ።

"ጥርስህ ይርገፍ! ደግሞ ይስቃል?"

"መቸ ሞቱ?" አለ ማከያው እንደማስተዛዘን ብሎ በሽሙጥ አነጋገር ።

"ሰውየ! ሰይጣን ሰርሃል እንዴ! ጤና የለህም? ትላንት ቢሞቱ ዛሬ ፣ ዘልዝለህ ቋንጣ አታድርጋቸው!" አሉት ኮስተር ብለው ።

"አላልኩም ! አልወጣኝም !"

"በል ወንድሜ!" አሉ አቶ ተገኔ እልህ እየተናነቃቸው። "ከእኔ ጋር እንካሰላንትያውን ተወውና ሙር ፍራ! አራጌ እንደ ሰው እድርተኛ ነኝ ብሎ ውጭው ከፍሎና የማታ እራት ብቻ ይዞ አይደለም የሚያስተዛዝነው ። ሰው ሞተ ሲባል ቀድሞ ቀብር የሚቆፍረው እሱ ነው። የናቱን መርዶ ንገርለትና እድርተኛው ያስተዛዝነው!"

ማከያው ነገሩ በቀጥታ ገብቶታል ። አይኖቹን አይናቸው ላይ ተክሎ "አየ ሰው!" አለ በልቡ ። የፍራሽ ሰፊው ዛቻና ማስፈራራት እንቆቅልሹ ተገለጠለት ።

"አድምጠኸኛል ያዘዘኩህን?" አሉና የእድር ዳኛው ማከያውን ገፋ አደረጉት ።

"አላዳምጥም አባ ተገኔ ። ጆሮ የለኝም!" አለ ማከያው
"አላዳምጥም አባ ተገኔ ጆሮ የለኝም!" አለ ማከያው
ብትሩን በጉያው ይዞና በሁለት እጆቹ ሁለት ጆሮዎቹን ጥርቅም አድርጉ ።

"የታዘዝከውን አትሰራም?"

"አላደርገውም!"

"በምን ምክንያት?"

"ሀሰት ነዋ! አራጌ እናት የለውም! ጠንቅቄ አውቃለሁ። ኃጢያት በገዛ እጇ አልሰራም!... ለነብሳችን እንዘን እንጂ አባ ተገኔ! በላይ ቤት መጠየቅ አለ'ኮ"አለና ማከያው ብትሩን ወደ ሰማይ ቀስሮ አንጋጠጠ ።

"እንዴት እናት የለውም?"

"የለውም ብያለሁ የለውም! አንድ ሰው አንድ እናት ነው ያለው! በኛ ይቅር ... ፀያፍ ነው ፣ አባ ተገኔ! እንኳን የአራጌ የየሀ ቀደሙ የአብጤም መርዶ ሽፍጥ ነው ። ጀስጢራችሁን በሆነ ቦታ ደርሼበታለሁ ።"

•"እኔ አዝኛለሁ! ባትለፍፍና ይኸ ምስኪን የጎዘኑ ደንብ ቢሰናከልበት ውርድ ከራሴ!" አሉት ። ግን ዛቻ ያዘለ ማስጠንቀቂያቸው ማከያውን ደንገጥ አላደረገውም ።

"የሐሰት ሞት አላውጅም! እድርተኛው ይፍረድ ብኝ!" አላቸው ማከያው ፍርጥም ብሎ ።

"ነግሬሃለሁ ! ያንተ ሞት እንዳይለፈፍ! ስም አጥፊ!... ቆሽማዳ! ማነህ አንተ የእድርተኞችን ስም የምታጠፋ!" የእድር ዳኛው በስጋትና በጥርጣሬ በግነው የስድብ ናዳቸውን አወረዱበት ።

"በሕግ አምላክ! የሀሰት ሞት ለፋፊ አይደለሁም። ለሁለት ብር ብዬ ማተቤን አልበጥስም። ክርስቲያን ነኝ! ማተቤ ጥብቅ ነው" አለና ማከያው አንገቱ ላይ የዞረውን ክር በጣቶቹ ሳብ ሳብ አደረገው ።

"ቆይ ታገኛታለህ!"

"ምን ሊያደርጉኝ?" አለና ማከያው ጉያው ውስጥ የነበረውን ጡሩንባ አወጣ ። "ጉዳችሁን ነው የምለፍፈው! እኔ ማከያው ነኝ የምሰድበው ፣ የምዋረደው? አገር ይወቅ! በዚህ ጡሩምባ ጉዳችሁን ነው የምለፍፈው!" አለ መላ ሰውነቱ በንዴት እየተንዘፈዘፈ ።

"ሞት ሽቶሃላ! በል ሞክር!"

ፍራሽ ሰፊው ከዚህ መጣ ሳይባል ተቀላቀላቸውና ለነገሩ አዲስ በሚያስመስለው አይነት ስሜት የእድር ዳኛውንም ማከያውንም ቃኛቸው ።

"ታያላችሁ!" አለ ። ማከያው ራመድ ራመድ ብሎ ፊቱን ወደ ፀሐይ መውጫ አድርጎ ጡሩንባውን በረዥሙ ከነፋ በኋላ ... የወጣው ቃል አልነበረው ። አፉን ጥርቅም አድርጎ ካፈነው ጠንካራ መዳፍ ለመላቀቀ ተጣጣረ ። ... ተንፈራገጠ ። አልቲሳካለትም ። ትንፋሽ አጠረው ። ወደቀ።

የእድሩ ዳኛ ጀርባቸውን ሰጥተዋቸው ሲሄዱ ፍራሽ ሰፊው መራራ ፈሳሽ ነገር አፉ ላይ አንጠባጠበበት ። ማከያው ሰመመን ያዘው ። ብዥታ ተጫጫነው ።...

ከዚያ በኋላ የእድር ለፋፊነት ስራውን አልቀጠለበትም። ስለአረጋሽም ሆነ ስለሆዴ እንደወትሮው ማሰቡ ቀረ ።

በዋለበት ውሎ ፣ በመሸበት የሚያድር ባተሌ ወጣው ። ከቀናው የምፅዋት እህል ይቀምሳል ። ካላገኘም አንጀቱ እንደታጠፈ ከደረሰበት ታዛ ጋደም ብሎ ያነጋል ።

ምንም ነገር አይታየውም—ባዶ ቀፎ…በድን አካል ሆነ ።

ልብ ብሎ የሚያዳምጠው ባይኖርም ቀኑን ሙሉ በአዳጉ አካባቢ እየተዘዋወረ አንዲት ነገር ብቻ ይናገራል ። እሷኑ ሲደጋግማት ይውላል ። "ጉዳችሁን ልለፍ?" አመል ካች ጣቱን አላፊ አግዳሚው ላይ እየቀሰረ ። የማንን ጉድ? የመቼ…? ማንም ቢሆን ምላሽ አላገኘለትም ፣ ለማከያው ጥያቄ ።

የካቲት 1984

"ወሬ ከማሪዉ"

ጋዜጣኛው ድንቃለም ሀይለየሱስ ጥቁር ጠላ ፍለጋ በባሻ ወልዴ ችሎት ሰፈር ይዘዋወራል ። የወይዘሮ ባፈሳ ጥቁር ጠላ ደንበኛ ነው ። ወዳጅነትም አፍርተዋል ። ከስራ መልስ ወደ መሸታ ቤታቸው ሄዶ ነበር ። "አልቋል" አሉት ። ስላለቀ ግን አልነበረም ። አርባ አምስት ብር ያህል እዳ ነበረበት ። በተደጋጋሚ እንዲከፍላቸው እየጠየቁት ለትላንት ማታ ሊያመጣላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር ። ስላልተሳካ ቀር ቷል። በአድራጉቱ የተናደዱት ወይዘሮ ባፈሳ 'አልቋል' ያሉት በዚህ ምክንያት ነበር ።

ድንቃለም ጥቁር ጠላ ይወዳል ። የወደደው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን ዋናው ምክንያቱ ሌላ መጠጥ ለማዘዝ የገንዘብ አቅም ስላልነበረው ነው ። ከስራ ጓደኞቹ እይታ

እየተደበቀ ነበር ጥቁር ጠላን የጀመረው ፣ ሀሜታቸው እያስፈራው ። የጓላ ጓላ ግን መደበቁን እርግፍ አድርጐ ተወ ። ከቢሮው እንደወጣ በቀጥታ እሱኑ ፍለጋ ሽቅብ ቁልቁል ይላል ። የስራ ጓደኞቹ ሆኑ ሌሎች ቢያገኙትም ግድ አልነበረውም ። እንደ ድሮው ሊዋሻቸው አይፈልግም ። ጥቁር ጠላ ፍለጋ እንደሚዞር ይነግራቸዋል ። ፈገግ ይሉበ ታል ። እሱም አብሮ ይፈግጋል ።

ከወይዘሮ ባፈሳ ጋር የተዋወቀው በአጋጣሚ ነበር ። አንድ ምሽት የተጠናወተው ሱሱን ለመወጣት ሲቅበዘበዝ እኘህ ቀይ ዳማ ወይዘሮ በጥቁር ጠላ የተሞሉ ጠርሙሶችን ከባልዲ እያወጡ ጠረጴዛ ላይ ሲደረድሩ ተመለከተ ። አላመነታም ።

"ጥቁር ጠላ ይኖርዎታል ?" አንገቱን ብቅ አድርጐ ።

"ያውም አፍ የሚሞላ! ድራፍትን የሚያስንቅ!" አሉት ተኩራርተው ።

"እንዴት ማለት?" እየተቀመጠ ።

"ቀምሶ ማረጋገጥ!" ተሞልተው መደርደሪያው ላይ ከተቀመጡት ጠርሙሶች አንዱን አንስተው በብርጭቆ ቀዱለት ። ከማቅረብ አልፈው ብርጭቆ የሚሞሉት በወይዘሮ ባፈሳ ግምት ፣ ሚዛን ለሚደፉ ሰዎች ነው ።

"ማጨስ ይፈቀዳል?" ሲል ጠየቃቸው ፣ የሚገላበጠው መቀመጫቸውን አፉን ከፍቶ እየተመለከተ ።

"የፈለገ ያምቢለው ! እሱ ሊያጨስ ፣ ራሱ ሊጨስ እኔን ለምን ያስፈቅዳል?" አሉት በመሸኮርመም መልክ ፈገግ ብለው ።

"እርስዎስ ለምን አይጠጡም?" አላቸው ጭውውታቸው የሚቀጥልበትን መንገድ ካውጠነጠነ በኋላ ።

"አብሮኝ ውሎ ስለሚያድር እያንገሸገሸኝ ነዋ!" ብለውት ወጣ ያለውን ቦራጫቸው በሁለት እጆቻቸው መታ መታ እያደረጉ በተለያዩ ቅርፆች የተሰሩ አራት የጣት ቀለበቶቻቸውን አሳዩት ። "ራሴ የጠመቅሁትን ጠላ መጠጣት አቃተኝ ። መጠጥ ሲያምረኝ ቢራ ነው የምቀምሰው ! " አሉት ። መሸታ ቤታቸው ሁለገብ ነው ፤ ጠጪ እንደየኪሱ ፣ እንደየፍላጐቱ ያሰኘውን እንዲጨብጥ ፣ ያበሻውም የፈረንጁም መጠጥ የሚገኝበት ።

"ታዲያ ምናለ ! ይጠጡዋ! ውስኪም ቢሆን እከፍላለሁ። የትውውቅ ግብዣ ይባላል ።" ሲጋራውን አውጥቶ ለኮሰ ። ለአፍ ያህል እንጂ ምርጫቸው ውስኪ እንደማይሆን ተማምኗል ።

"ውስኪ እንኳ የለኝም ፣ አመሰግንዎታለሁ!" አሉና አመልካች ጣታቸው ላይ ያጠለቋትን የወርቅ ቀለበት ወጣ ገባ እያደረጉ ተቅለሰለሱ ፣ ሲግደረደሩ ።

"ቢራ ይያዙዋ !" ከማለቱ ሁለት መዳፋቸውን ጉልበቶቻቸው ላይ አስደግፈው ከቲነሱ በኋላ መቀመጫቸውን ከፍ ዝቅ እያደረጉለት አንድ ጠርሙስ ቢራ ከሳጥኑ አውጥተው ከፈቱና ተጐነጩ ፤ በቁማቸው ።

"ይጫወቱ!" አሉ ወይዘሮ ባፈሳ ፊት ለፊት ተቀምጠው ።

"አንቱ ለምን ይሉኛል ?" የጨዋታ መክፈቻ በማግኘቱ ደስ አለው ።

"እርስዎስ አንቱ ለምን ይሉኛል?"

"እኔ ሶስት ምክንያቶች አሉኝ ። አንደኛ ከርስዎ በድሜ አልበልጥም ። ሁለተኛ ደግሞ አዲስ ደንበኛ ስለሆንኩ አስክንላመድ ... አለ አይደል ? ሌላው ምክንያቴ ደግሞ ጋዜጠኛ 'አንቱ' ስለማይባል ነው ። ለምን የማቱሳላ እድሜ አይኖረውም! አንተ እንደተባለ ነብሱ ምንጥቅ ትላለች" አላቸው ያለቀችውን ሲጋራ ወለሉ ላይ ጥሎ በጫማው ተረከዝ እየደፈጠጠ ።

"እኔም አንቱ ሲሉኝ አልወድም" ብለውት ፊታቸውን ለአፍታ ኮስተር አደረጉና "ውፍረቴ'ኮ የእድሜ አይደለም ። የምቾትም አልለው ፣ መች ደልቶኝ! ጋን ሳገላብጥ ነው የምኖረው ። እንደውም ደስ የሚለኝ ሰው 'ባፈሳ'! ሲለኝ ነው። አንዳንዶቹማ 'ባፊ! ባፊየ! ባፊና!' ሲሉኝ በጣም እወዳቸዋለሁ ።" በረዥሙ ሳቁ ።

"እኔም 'ባፊ' ልበላ ታዲያ?"

"ደስ ይለኛል!" ብለውት የቢራ ጠርሙሳቸውን ተጐነጩላትና ወደ ላይ ከፍ አድርገው ተመለከቷት ፤ ባዶ መሆኗን ለማመልከት ።

"ጨምሪ ባፊ ፣ እከፍላለሁ ።"

"ያንተን ስም ማን ልበል?" ሌላ ቢራ ጠርሙስ ከፈቱ ።

"ድንቃለም ! የጋዜጣ አዘጋጅ ነኝ ።... ጋዜጠኛ"

"ባፊ ካልከኝ እኔም 'ድንቂ!' ነው የምልህ!" በግራ አይናቸው ጠቀሱት ። ድንቃለምም ጐንተል አደረጋቸው ።

"ቤቱን ዘጋ ላድርገው እንዴ?"

"ደስ ይለኛል ባፊ!" አላቸው በፍትወት ግሎ ። የቢራ

ጠርሙሷን በግራ እጃቸው ይዘው ፣ በቀኝ እጃቸው የቤቱን በር የውስጥ መቀርቀሪያ ዘንግ ከጥግ በኩል እነሱና "አልጋው ላይ ውጣ!" አሉት ።

በሩን አጥብቀው ዘግተው ፣ ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ውን መጋረጃ ቁልቁል ለቀው ሲመለሱ ድንቃለም አልጋቸው ላይ ወጥቶ አላገኙትም ።

"አልጋው ላይ ውጣ እንጂ !" አሉት በአይናቸው ቂጥ እየተመለከቱት ።

ድንቃለም ዝም አለ ፣ ጠጉሩን እየቀነጣጠበ ። በሀሳብ ተግባቡ ።··· እና ተላመዱ ። ወደዳቸው ። ዱቤ ሲጠይቅ አይከለክሉትም ። ምን ያህል መጠጣት እንዳለበት ወስኖ አያውቅም ። ከወይዘሮ ባፈሳና ጥቁር ጠላቸው የሚገላግለው ሰአት እላፊ ሆነ ። ያራት ኪሎን ጥበቃ ጓዶች እንደ ጉድ ስለሚፈራቸው ውስጥ ውስጡን እያሳበረ ቤቱ ይገባል ።

ዛሬ ግን ወይዘሮ ባፈሳ "ጥቁር ጠላ የለም !" ብለው ታል። ስለሆነም ጥቁር ጠላ ፍለጋ ይዘዋወራል ።

ሁለት እጆቹን ፣ ሱሪው ኪሶች ውስጥ ከቶ ሲዘዋወር በአካባቢው የሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች በራፋቸው ላይ እንደ ቆሙ ቃል ይጥሉበታል ። በዘዴ ይጠሩታል ። ወሲብ ይጋብዙታል ። አየት አድርጉአቸው ያልፋል ፣ ጥቁር ጠላ ፍለጋ አይናቹን ግራ ቀኝ እያማተረ ።

"ጂሚ!" አለችው አንዲ ሱሪ የታጠቀች ።

ጥቁር ጠላ የተሞሉ ጠርሙሶች ለአላፊ አግዳሚው እንዲታይ ሆነው የተደረደሩባት አንዲት ጠባብ ክፍል በር ላይ የተገተረች ወጣት ነበረች ። ያን እንደተመለከተ ሳያመ

ነታ ጥልቅ አለ ።

"ምን ልታዘዝ?" አለችው ገና ተደላድሎ ሳይቀመጥ ።

"ምን ምን አለ?" አላት ከጥቁር ጠላ በቀር ሌላ ምርጫ ያለው ይመስል ።

"ጥቁር ጠላ ፣ የአበሻ አረቂ ፣ አፕሬቲፍ ..."

"አፕሬቲፍ ! እንዴት ?" ግራ ገባው ።

"አፕሬቲፍ አያውቁም?" ፈገግ አለች ።

"እንዴት አልኩሽ? ምን ያስገለፍጥሻል?"

"አፕሬቲፍ ማለት ጥቁር ጠላና የአበሻ አረቂ ተደባልቆ ማለት ነው ። ሌላ ስም አለው እንዴ?"

"ጥቁር ጠላውን ስጭኝ!" አላት ሲጋራ እያወጣ ።

ጋዜጠኛው ድንቃለም ሚስት ድስት የሚባል ነገር የለውም ። የዛሬ ሶስት አመት ግን ነበረው ። ኢየሩሳሌም የምትባል ሚስትም ነበረችው ። ኢየሩሳሌም አንበሴ ፣ የፍራሽ ተራው ጆንበሴ ማን ችሎት የበኸር ልጅ ። ጥሩ ትዳር ነበረው ። ግን አልዘለቀለትም ።

አለቆቹ ጋር የማይግባባና በጥሩ አይን የማይመለከቱት፣ ራሱን ከሙያውና ከወቅቱ ጋር ማጣጣም የተሳነው በመሆኑ ዘወትር ብስጩ ነበር ። ኢየሩሳሌም ደግሞ ችግሩን አትረዳለ ትም ። ሲበሳጭ አታሰክነውም ። በብቸኝነት ባህር ውስጥ ሰጥሞ ሲንከላወስ አይዞህ አትለውም ። ሃሳቡን እንዲያካፍ ላት አትወተውትም ። አታግባባውም ። እሷም በሀሳብ ጭልጥ!··· ቤቱ ድብርት ወረረው ። ቤቱን መጥላት ሲጀምር እሷም እንደዚያው ። ለሷ የነበረው ፍቅር በመቀነስ ላይ ያለ እየመሰላት ፣ ራሷ በፈጠረችው ጥርጣሬ ትዳሯ አስጠላት ።

ማታ ለአልጋ ላይ ይገናኛሉ ፤ በቃ ። የአልጋ ላይ ልፈያቸው ከቀረም ወራት አስቆጠሩ ። ከአንገት በላይ ብቻ ያወራሉ ። ያም ገደብ አለው ።

ደመወዙን ተቀብሎ ፣ የወር ወጭ በሰጣት የጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምነት ላይ ግን የከረረ ጠብ ገጠሙ ።...

"እራት የለም እንዴ ኢየሩስ?" ምንም ሃሳብ ቢገባውና ቢበሳጭም ባለቤቱን 'ኢየሩስ!' ብሎ ከመጥራት ታቅቦ አያውቅም ፣ ስሟን መጥራት አስፈላጊው ከሆነ ።

"የለም!"

"ለምን?"

"ለምን ራሱ ጥያቄ ነው!"

"መልስ ግን ሊሆን አይችልም ?"

"ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ።"

"እራት ለምን የለም?"

"ራስህ ሰርተህ ለምን አትበላም?"

"እንደዚህ አይነት ጥያቄ ከአፍሽ ወጥቶ አንደማያውቅ ልቤ እያልሽ!"

"የወጥ ቤትና የጓዳ ስራ ለኔ የፈረደብኝ ማነው?"

"ከዚያች ቀልቃላ የቀበሌ ሴቶች ሊቀመንበር ጋር መዋል እንደጀመርሽ መች አጣሁት! ኖ ማተር ።"

"ለማያውቅህ በለው! ሆ...ሆ!... አንተስ ማን ጋር እየዋልክ ነው? ሀና አታበላህም እንዴ ? ወይስ የማድ ቤት ስራ አይሆንላትም ?" ሳቋን ለቀቀችው ፣ የንዴት ሳቅ ።

"ሀና!...ሀና ገብረመድህንን ማለትሽ ነው?"

"ባክህ ዝጋ! ኢየሩሳሌም መደበሪያህ አይደለችም ።

ከሀና ያነሰ ቁንጅና ካለኝ ሞቴ ነው!... ለዚያች በስባሳ ደግሞ!" ብላው ምራቋን ጢቅ አደረገችበት ።

"ለምን እንዲህ ትያለሽ ? እኔ ለአንቺ ግልፅ ያልሆንኩበት ጊዜ አለ? ለምን አትጠይቂኝም?"

"ምን ብዬ ነው የምጠይቅህ? አንዴት እንዳወጣህት ፣ እንዴት እንደምትላፉ...ነው? ሰው አታውቅምና!"

"እኔ ላንቺ ግልፅ ሆኜ አላውቅም?"

"ግልፅነትህን !? ምንህን ብላ ! ዝንተ አለም ስታሞኝኝ ልትኖር ነው?"

"ሃቁን ልንገርሽ! ሀና የስራ ባልደረባየ ናት ። አንድ ቀን ፓርቲ አዘጋጅታ ጠራችን ፤ ሄድን ፤ እንዴት እንደሆነ አላውቅም ፤ ሌሊቱን እሷ ጋር አድሬአለሁ ። በቃ! ...ብዙ ጠጥቸ ነበራ! ከዚያ ወዲህ በወሲብ አታውቀኝም ፣ አላውቃትም ። በርግጥ ይህን አልነገርኩሽም..."

አላስጨረሰችውም ። "የሷን ለምን ደበቅከኝ?"

"ረስቸው ይሆናላ! ሌላ ብዙ ችግር አለብኝ አይደል?"

"ግንኙነታችሁ ቢቀጥል እንጂ!... ሀናን ለፍቅር ፣ ኢየሩሳሌምን ለመደበሪያ !" አስካካችበት ፣ ፀጉሯን በንዴት ጨምድዳ ።

"ታዲያ ችግሩ እራት ባለመስራት ይፈታል?"

"ምን ታደርገዋለህ!"

"አኬ !... ከእንግዲህ እንዳሻሽ ልትፈነጭብኝ አትምጣ" አላት ተቆጥቶ ። "ፍቺ ከፈለግሽ አልጋዬንና ጠረጴዜን ከነመፃህፍቶቼ ትተሽልኝ ውልቅ ማለት ትችያለሽ ።

መነፍረቅ ጀመረች ።...

በበነጋው ከስራ ሲመለስ ብቤት ውስጥ ያገኘው አልጋውን ፣ ጠረጴዛውን ፣ ወንበሮቹንና መፃሕፍቱን ብቻ ነበር ።

በባዶ ቤት ሁሉ ነገር ስላስጠላው ወደ ድራፍት ቤት ጉራ አለ ። በዚያን ጊዜ ላዚያ የሚሆን ገንዘብ አላጣም ነበር ። ከዚያም በኋላም ወደ ድራፍት ቤት ። ...በብድር ድራፍት... እየተበደረ ድራፍት... የሚያበድረው ሲያጣ ወደ ጥቁር ጠላ! ...በዱቤ ጥቁር ጠላ...ዱቤ! ዱቤ! ዱቤ!... የታዋቂው ጋዜጠኛ ኑሮ ።...

የዛሬው ጥቁር ጠላ እንደ ወይዘሮ ባፈሳ አፍ የሚሞላ ሆኖ የመጠጥ ልክፍቱን ባያስወርፍለትም የቤቷ ፀጥ ማለት ግን አስደስቶታል ። ጥቁር ጠላ እየጠጣ ብቸኛ መሆን ለሚፈልግ የምትመረጥ አይነት ናት ።

"ልጨምር ጋሼ?" ባዶ ጠርሙስ ከፊቱ እያነሳች ።

"ምን ይመስልሻል?"

"እኔ ምን አውቄ ጋሼ!"

"ሳንቺ ውሳኔ እመራለሁ ብልስ!"

"ሰአቱ ገና አንድ ተኩል ነው ። ቢጨምሩ ይሻላል ።" አንድ ጠርሙስ ጥቁር ጠላ አመጣችለት ።...

ድንቃለም ከጋዜጠኝነት ሙያው ከተራራቀ ሳምንታት አልፈዋል ። በሙያው እያፈረበት መጥቷል ። "ጋዜጠኛ ፣ መንጋ ግይም ባለስልጣን እንደፈለገ የሚያሾረው ፣ እንዝርት ነው!" ይላል ለራሱ እየደጋገመ ።

በአግርኛ ቋንቋ በዲግሪ ተመርቆ ፣ በፕሬስ መምሪያ ውስጥ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደ ተመደበ ደስተኛና

በአፍላ የወጣትነት ጊዜውም 'ጋዜጠኛ' ሲባል ኩራት የሚሰማው ሰው ነበር ። ለሙያው የነበረው ክብርና የሚያሳየው ስነምግባርም ጥብቅ ነበር ።

የኋላ ኋላ ግን አለቆቹ የሱን ችሎታ እየተጠቀሙ ፣ የስራ ውጤቶቹን በባለቤትነት ለበላይ አለቆቻቸው እያቀረቡ ሲመሰገኑበት ፣ ሲሾሙበትና ሲሸለሙበት መታዘብ ጀመረ ። ቅሬታ እየገባው መጣ ። በመጨረሻም የቅርብ አለቃው ጋር አለመግባባት ተፈጠረበት ።...

"አቶ ድንቃለም! ካሁኑ ስራህ በተጨማሪ ርእሰ አንቀፅ እያዘጋጀህ እንድታቀርብ ወስነናል ። ከዛሬ ጀምሮ እሱን ደርበህ ትሰራለህ ።!"

"እስከዛሬ የተመደበበት ሰውስ?"

"እሱ አይመለከትህም!"

"እንግዲያው እኔም አይመለከተኝም ። ከአቅሜ በላይ ነው ፣ አይሆንልኝም!"

"አይሆንልኝም ስትል አጥር እየጣስክ መሆኑን ታውቃለህ?"

"ጋዜጠኛ ሲባል'ኮ ወረቀትና ቀለም እየጐረሰ ፅሁፍ የሚያመርት ፋብሪካ አይደለም ። ጋዜጠኛ በሚያምንበትና በሚመስጠው ርእሰ ጉዳይ ላይ ማተኮር አለበት ። አለበለዚያ ጋዜጠኛ መሆኑን አቁሟል። ራፖር ፀሃፊ ሆነ ማለት'ኮ ነው?"

"ጋዜጠኝነት ያረጀንበት ነው ። 'ኋላ የመጣ አይን አወጣ!' አሉ ። ጋዜጠኝነትን ለኛ ነው የምታስረዳን? ለፓርቲ ዲሲፕሊን አትገዛም?"

በተለይም ለኋለኛው ጥያቄ የሚሆን መልስ አልነበረ

ውም ። ከባድ ዝምታ ዋጠው ።...

ከዚያ ጊዜ በኋላ በአለቆቹ የቂምና የጥርጣሬ መነፅር ውስጥ ገባ ። ያዘዙትን ይፈፅማል ። ያልተደረገውን እንደተደረገ አድርጐ እንዲፅፍ ይታዘዛል ። ቢያምንበት ባያምንበት መፈፀም ግዴታው ነበር ።

ከስራ ባልደረቦቹ ውስጥ ደግሞ ተጠላፊዎቹና ጠላፊዎቹ በዝተዋል ። እሱ ከተጠላፊዎቹ ነው ። የራሱንም ሆነ ጠቅላላ ተጠላፊ ጋዜጠኞች ሁኔታን ሲያስተውል "ጋዜጠኛ ነት ወሬ ኮማሪነት ፣ ጋዜጠኛ ወሬ ኮማሪ!" ማለት ጀመረ ፣ ከራሱ ጋር ሲወያይ ።

ጠልፎ በመጣል በኩል ደግሞ ግራ ኮሌታው ላይ የሌኒንን ምስል የሚለጥፈው አንድ አይናው አምደ ማርያምን የሚያክል ማንም አልነበረም ፣ በብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ህንፃ ውስጥ ።

አምደ ማርያም አንዳንድ ጊዜ 'የቃላት ትራፊክ!" እየተባለ ይጠራ ነበር ። ታዲያ ፊቱ አይደለም ። የሚተማመኑ ቴሰባስበው እንደዋዛ ሲያወሩ ነው ። ቃላትን ከቃላት እያዋጋ ብዙዎችን ለችግር የዳረገ ነው ይባላል በሌለበት ። በ69 አመተ ምህረት አካባቢም በሌኒን ስም ይምል እንደነበር ይነገራል ።

አንድ በሞንም አምደ ማርያም የድንቃለም አለቃ ሆኖ ነበር ። በዚህ የስራ ዝምድናቸው ምክንያት ድንቃለም ያዘጋጀው ፅሁፍ እንዲፀድቅለትና ወደ ህትመት እንዲላክ ለአምደማርያም ያቀርባል ።

"ኢትዮጵያ ስትል ምን ማለትህ ነው?" ይለዋል አምደ

ማርያም ፤ አንድ ቀን ።

"ኢትዮጵያ ስል ያው የምናውቃት ኢትዮጵያን ማለቴ ነዋ!" ድንቃለም በአጭር ይመልሳል ፤ የአምደ ማርያም አመጣጥ እየገባው ።

"አባባሌን ግልፅ ላድርግልህ! ኢትዮጵያ ስትል የትኛዋን ኢትዮጵያ ማለትህ ነው ? አሻሚ ነገር'ኮ ሆነ ። እኛ ጋዜጠኞች ነገሮችን ግልጥልጥ አድርገን ፤ ሀቅን አፍረጥርጠን መፃፍ አለብን ። የጋዜጠኛ መዝገበ ቃላት በጣም ትልቅ ነው ። የጋዜጠኛ ዋና ካፒታሉ ቃላት ናቸውና!..."

"ኢትዮጵያ ስል ይቺ ኢትዮጵያ ማለቴ ነው" ብሎ በንዴት ወለሉን በጫማው መታ መታ አደረገና "ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራ ሌላ አገር ስለሌለ ለምን አሻሚ ይሆናል?" አለው ።

"አልገባህም ! የምልህን በፖለቲካ አይን ብታየው ። ሌኒን ሁሉን ነገር በፖለቲካ አይን ማየት ይወድ ነበር ይባላል።" ከንፈሩን መጠጠ ። ቀጠለና "ለምሳሌ ውሀን እንውሰድ ። እኛ የምንጠጣውን ውሀና ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሚጠጡትን ውሀ በእኩል አይን ትመዝነዋለህ?" በሀሳቡ ያሸነፈ ይመስል የዛጉ ጥርሶቹን እያሳየው ሁለት እጆቹን ዘረጋለት ። "አቶ ድንቃለም! ኢትዮጵያ አንዲት ብትሆንም ብዙ ናት!"

"አልገባኝም!"

"አትቸኩል፤ ሀቀኛ ጋዜጠኞች አይቸኩሉም። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ፣ የፊውዳሎች ኢትዮጵያ ፣ የወያኔ ግንጥልጥል ኢትዮጵያ ፣... መልኳ ብዙ ብዙ ነው ። እና ግልፅ ይደረግ!

ውም ። ከባድ ዝምታ ዋጠው ።...

ከዚያ ጊዜ በኋላ በአለቆቹ የቂምና የጥርጣሬ መነፅር ውስጥ ገባ ። ያዘዙትን ይፈፅማል ። ያልተደረገውን እንደተደረገ አድርጉ እንዲፅፍ ይታዘዛል ። ቢያምንበት ባያምንበት መፈፀም ግዴታው ነበር ።

ከስራ ባልደረቦቹ ውስጥ ደግሞ ተጠላፊዎቹና ጠላፊዎቹ በዝተዋል ። እሱ ከተጠላፊዎቹ ነው ። የራሱንም ሆነ ጠቅላላ ተጠላፊ ጋዜጠኞች ሁኔታን ሲያስተውል "ጋዜጠኛ ነት ወሬ ኮማሪነት ፣ ጋዜጠኛ ወሬ ኮማሪ!" ማለት ጀመረ ፣ ከራሱ ጋር ሲወያይ ።

ጠልፎ በመጣል በኩል ደግሞ ግራ ኮሌታው ላይ የሴኒንን ምስል የሚለጥፈው አንድ አይናው አምደ ማርያምን የሚያክል ማንም አልነበረም ፤ በብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ህንፃ ውስጥ ።

አምደ ማርያም አንዳንድ ጊዜ 'የቃላት ትራፊክ!" እየተባለ ይጠራ ነበር ። ታዲያ ፊቱ አይደለም ። የሚተማመኑ ተሰባስበው እንደዋዛ ሲያወሩ ነው ። ቃላትን ከቃላት እያዋጋ ብዙዎችን ለችግር የዳረገ ነው ይባላል በሌለበት ። በ69 አመተ ምህረት አካባቢም በሴኒን ስም ይምል እንደነበር ይነገራል ።

አንድ በሞንም አምደ ማርያም የድንቃለም አለቃ ሆኖ ነበር ። በዚህ የስራ ዝምድናቸው ምክንያት ድንቃለም ያዘጋጀው ፅሁፍ እንዲፀድቅለትና ወደ ህትመት እንዲላክ ለአምደማርያም ያቀርባል ።

"ኢትዮጵያ ስትል ምን ማለትህ ነው?" ይለዋል አምደ

ማርያም ፤ አንድ ቀን ።

"ኢትዮጵያ ስል ያው የምናውቃት ኢትዮጵያን ማለቴ ነዋ!" ድንቃለም በአጭር ይመልሳል ፤ የአምደ ማርያም አመጣጥ እየገባው ።

"አባባሌን ግልፅ ላድርግልህ! ኢትዮጵያ ስትል የትኛዋን ኢትዮጵያ ማለትህ ነው ? አሻሚ ነገር'ኮ ሆነ ። እኛ ጋዜጠኞች ነገሮችን ግልጥልጥ አድርገን ፤ ሀቅን አፍረጥርጠን መፃፍ አለብን ። የጋዜጠኛ መዝገበ ቃላት ዐጣም ትልቅ ነው ። የጋዜጠኛ ዋና ካፒታሉ ቃላት ናቸውና!.."

"ኢትዮጵያ ስል ይቺ ኢትዮጵያ ማለቴ ነው" ብሎ በንዴት ወለሉን በጫማው መታ መታ አደረገና "ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራ ሌላ አገር ስለሌለ ለምን አሻሚ ይሆናል?" አለው ።

"አልገባህም ! የምልህን በፖለቲካ አይን ብታየው ። ሌኒን ሁሉን ነገር በፖለቲካ አይን ማየት ይወድ ነበር ይባላል።" ከንፈሩን መጠጠ ። ቀጠለና "ለምሳሌ ውሀን እንውሰድ ። እኛ የምንጠጣውን ውሀና ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሚጠጡትን ውሀ በእኩል አይን ትመዝነዋለህ?" በሀሳቡ ያሸነፈ ይመስል የዛጉ ጥርሶቹን እያሳየው ሁለት እጆቹን ዘረጋለት ። "አቶ ድንቃለም! ኢትዮጵያ አንዲት ብትሆንም ብዙ ናት!"

"አልገባኝም!"

"አትቸኩል፤ ሀቀኛ ጋዜጠኞች አይቸኩሉም። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ፣ የፊውዳሎች ኢትዮጵያ ፣ የወያኔ ግንጥልጥል ኢትዮጵያ ፣... መልኳ ብዙ ብዙ ነው ። እና ግልፅ ይደረግ!

በተለይ ደግሞ እኛ 'አዲሲቷ ኢትዮጵያ' የምንላት ሳታጣ ያጣች ፣ አንሙራ ሀብቷን በጀግኖች ልጆቿ ደምና አጥንት ክፋይ ጠብታ የኖረች ፣ ኩሩ አፍሪካዊት እመቤት እንደመሆኗ በለሷ ስትፅፍ መነፅርህን ከዚያ አንባር ብታስተካክለው ጥሩ ነው ።"

"እንዳልከው በርግጥ ሀቀኛ ጋዜጠኞች አይቸኩሉም ። አይክለፈለፉም ። የእውነት ጠበቆችም ናቸው ። ማንንም ለማወደስ ሲሉ በቃላት አያጫውቱም" አለና በአሽሙር ጀመረ ፣ ድንቃለም ። ቀጠለና "የማውቃት አንዲት ኢትዮጵያ ናት ። ያልከኝን ሁሉ የምፅፍ ራፖር ፀሀፊህ አይደለሁም" አለ ፍርጥም ብሎ ።

"ጋዜጠኛ አይናደድም ። ጋዜጠኛ በሂስ ያምናል ። ጋዜጠኛ ስህተቱን ፈጥኖ ያርማል ። ጋዜጠኛ አለቃውን ያከብራል ።"

"ግን አሻንጉሊት አይደለም!" ድንቃለም አቋረጠው ።

"ማን አሻንጉሊት አደረገው?" አምደ ማርያም አፈጠጠ ። ድንቃለም አልመለሰለትም ።

"የታዘዝከውን እንድትሰራ የሚያደርግህ አመራሩ ነው። አመራሩ ደግሞ የአገሪቱ ነው ። 'ጋዜጠኛ አሻንጉሊት አይደለም!' ስትል አሻንጉሊት ያደረገው' አለ ማለትህ ነው። ይህ ለበላይ አካል የሚቀርብ ጉዳይ ነው ። ግን ባልረባ ክርክር አስር ደቂቃ አጠፋን ። አብዮቱን በአስር ደቂቃ እንዶጉተት ነው ይገባሃል?"

ክስ በዛበት ፣ ከቃላት እያጋጨ ፣ ቃላትን እየበለቱ ሰላም ነፈጉት ። እፎይታ አጣ ። ፍርሀትና ስጋት ተጫጫኑት ።

ችሎታውን ሊጠቀሙበት ስለፈለጉ ግን አላባረሩትም። አላሰሩትም ። ግን ያስጨንቁታል ። እድገት ይከለክሉታል ። የሚቀመጥበትን ወንበርና የሚውልበትን ቢሮ እንኳ መጠራጠር ጀመረ ። አንድ ፅሁፍ ፅፎ ሲጨርስ ቢያንስ አስር ጊዜ ያነበዋል ። እና ሙያውን ጠላው ።

"ጋሼ አንድ ነገር ልጠይቃዎት ብዬ ነበር!" ተቅለሰለሰ ችበት ፣ ባለ ጥቁር ጠላዋ ።

"ምን ነበር ጥያቄሽ?"

"የማውቀዎት መስሎኛል!"

"ታዲያ ምን አለ!? ግን የት ቦታ ነው የምታውቂኝ?" ጠርሙሱን አንስቶ ቀዳና ብርጭቆዋን በአንድ ትንፋሽ ከለበሳት ።

"እንጃ!... ብቻ አንድ ቦታ..." ብላ ማሰብ ቀጠለች ። አንድ ቦታ ላይ የሚተዋወቁኝ ሰዎች በሚሊዮን ይቆጠራሉ ። ግን እውቂያ አይባልም ። ሌላ ጠርሙስ አምጭልኝ!"

ከመደርደሪያው አንድ ጥቁር ጠላ የሞላ ጠርሙስ አውርዳ ፊት ለፊቱ ጉብ አደረገችለት ።

"አሁን አስታወስኩት ጋሼ...አስታወሰኩት!" እያጨበጨበች ።

"በይ እስኪ አምጭው!" አላት እያፋሸገና "ከኔ ጋር አድረሃል"

"ብርሃንና ሰላም ሀገሃ ውስጥ ነው ። አንድ ጊዜ መጥቼ ነበር። እኚያ የናንተ ጓደኛ...ጉድጓድ ይከተታቸውና አንድ ወር ሙሉ ጥቁር ጠላየን በዱቤ ሲጠጡ ከርመው ሂሳብ ላይ ነገ ዛሬ እያሉ ሲያጉላሉኝ ከስሻቸው ፣ መጥሪያ ልሰጣቸው ቢሮአ

ቸው ድረስ ስመጣ አግኝቸዎታለሁ ። እንዳውም በሽምግልና
ገብተው ነበር ። ያውም እንኳ እዳቸውን ራስዎ ነበር
የከፈሉላቸው ። ስድሳ ሁለት ብር ከኪስዎ መዘው አልሰጡ
ኝም? እንዴት ረሱት?"

"አሁን ገና ትዝ አለኝ! አምስት አመት ሊሆነው
አይደል?" ክብሪት ጭሮ ሲጋራውን ካቀጣጠለ በኋላ "ለምን
ከሰስሽው ግን? በዚያን ወቅት ከባድ ችግር ስለነበረበት ነው
እንጂ አያስቀርብሽም ነበር ። ጨዋ ሰው ነው ። ጥቂት
ብታተግሺው ደግ ነበር" አላት አበራን እያስታወሰ ። መጥሪያ
ይዛ ስትመጣበት ምን ያህል እንዳፈረና "መጣች! መጣች!
የለም በላት!...እያለ ቁም ሳጥን ውስጥ ለመግባት ያደረገው
ጥድፊያ ትዝ አለው ።

"ምን ማለትዎ ነው ጋሼ? ታዲያ ምን ላድርግ? ከኔ
እላቸው ይሻላሉ ። የወር ገቢ እንኳ አላቸው ። ከጠላ ከሚገኝ
ገቢ ተብሶ ባዶዬን አጨብጭቤ ልቅር? ስድሳ ሁለት ብር'!
ነው ። ሶስት መቶ ጠርሙስ ጠላ ሸጬ የማገኘው ትርፍ ነው ።
እንዲያውም ለምን ላዋርዳትው ብየ ነው እንጂ ብዙ እዳ
ነበረባቸው ። ግን ምን ያደርጋል?"

"ሌላ ምን የሚሉት እዳ ነበረበት?" በመገረም ተመለከ
ታት ።

"እሪ ይቅር! ምኑ ይወራል!"

"ካልተወራ ይቅር!" ትከሻውን ከፍ አደረገ ።

"ምን መሰለዎት? ብቻ ያሳፍራል!...ግን ምኑ ያሳፍ
ራል! ለምደውኝ ነበር" አለችና ተሸኮረመመች ።

"መላመድ እዳ ነው እንዴ?"

"ይቀልዳሉ መሰለኝ? አሁን ማን ይሙት ነገሬ ሳይገባ
ዎት ቀርቶ ነው? አንድ ወር ሙሉ ለደመወዝ እያሉ እኔ ጋር
አድረዋል ። ..." ሀፍረት የተሰማት ይመስል አቀረቀረች ።
"በስመ አብ በይ! ባለትዳር ነው' ኮ? እንዴት እንዲህ
ትያለሽ?"

"ተባለ እንዴ? ጋዜጠኞች ስትባሉ ቀልድ ትወዳላ
ችሁ። አሁን ሊያናግሩኝ ነው እኮ! ስንቱን እናውቀዋለን...
ባለትዳርም ይሁን ወንደላጤ ሁሉንም በአይነት በአይነቱ
አይተናል ። ሙች ይታወቅባቸውና ጆሮ ባለትዳሩ ይብሰል!"

"እድለኞች ናችኋ ታዲያ!" አለ ።

"በልተን ማደራችን ነው!"

"እሱን ያልታደለ ስንት አለ!"

"እንሰላ እንኳ በልቶ የድራል ። በልቶ ማደር ካልቻለ
ለምን ይኖራል? ራሱን ማጥፋት አለበት ። ምን ሊያገኝ ብሎ
ይኖራል? ምንን ተስፋ አድርጐ ይጠባበቃል? በአስር ሳንቲም
ገመድ ህይወቱን ለምን ሲጥ አያደርጋትም? ስለኛ የሚያስ
ብ'ኮ ማንም የለም ። ስንቱን ቻለን መሰለዎት?"

"ልክ ነሽ! ሴቶች ጭቆና አለባችሁ ። ግንኙነት
ስታደርጉ እንኳ ሁል ጊዜ ከታች ነው የምትሆኑት ።"

አንድ ወጣት ድንገት ክፍሏ ውስጥ ጥልቅ አለና
ያለምንም ሙዚቃ ስብርብር ፡ ዝልፍልፍ ማለት ጀመረ ።

"ሙዚቃ ! ሙዚቃ!" ብሎ ጮኸ ወጣቱ ።

"መጀመሪያ ምን ልታዘዝ?" አለችው ኮስተር ብላ ።

"አንቺን!" አሁንም ይብረከረክል ።

"ከኔ በፊት?"

"ጠላ!" አላትና ባንኮኒዋን ተደግፎ ቆመ ። ግንባሩ ላይ ላብ ቸፍፍ ብሏል ። የተቀዳለትን ብርጭቆ ጠላ በአንድ ትንፋሽ አጋባና እጇን ይዞ እየጐተተ ወደ ጓዳ ገባ ። ጥቂት ካንሾካሾኩ በኋላ መጋረጃውን ሰብሰብ አድርጋ አንገቷን ብቅ አደረገችና "ጋሼ ቤቱን ይጠብቁልኝ ። አሁን መጣሁ ። አደራ!" አለችው ።

"እንዴ! ነይ ውሰጂ ሂሳብሽን!" ጮኸባት ድንቃለም የውስጥ ኪሱን እየዳበሰ ።

"ታዲያ ምን አስቆጣህ?"

የአራት ጠርሙስ ጥቁር ጠላ አራት ብር ጣለላትና ውልቅ አለ ።

"ምን ይጨማለቃል" አለችው በሩ ላይ ብቅ ብላ ። ወዲያው በሯን ዘጋች ። ድንቃለም የወሲብ ስሜቱ ተቀስቅሶ በት ፣ በገጠመው ድርጊትም እየተበሳጨ ወደ ወይዘሮ ባፈሳ ቤት አዘገመ ። ኪሱ ውስጥ ድፍን ሀምሳ ብር ቀርቶታል ። ሰአቱን ሲመለከት አምስት ሰአት ይላል ፣ ከምሽቱ ።

"ባፈ! ቢራ አለሽ?" አለ ገና ከመግባቱ ።

"ድንቄ! ግባ...ቅድምኮ ተበሳጭቼ ስለነበር ነው ። አንድ ጉረኛ አበሳጨኝ ። የተማረ ይግደለኝ ። በቶለይ ጋዜጠኛ ! አይ አንደበት ...አይ ለዛ...አይ ጨዋታ...የጋዜጠኛ ሚስት ታደለች! ...ሳትስቅ የምትውልበት ቀን ይኖር ይሆን?" ሁለት ጠርሙስ ቢራ ከፍተው አንዱን ለድንቃለም አቀረቡለት ፣ ለራሳቸውም አንድ ጨበጡ ። ደጋግሙ ። የተቀመጡት ጉን ለጉን ስለነበር ሳብ አድርጉ አቀፋቸው ።

"ልዝጋው እንዴ በሩን?"

"አዳሬ እዚሁ ነው!" አለ ።

"ይሻላል ብለህ ነው?"

"ምነው ባፈ? ምርጫው ያንቺ ነው!"

"እስቲ እናየዋለን!" ወይዘሮ ባፈሳ አቅማሙ ። ልቡን ሊስቅሉት ፈልገዋል ። 'ወንድ ልጅን ምንጊዜም አይለምዱ ትም' የሚል አባባል አላቸው ። ከድንቃለም የበለጠ የሚጋ ብዝ ፣ ገንዘቡን ከምንም ሳይቆጥር ከኪሱ እያወጣ የሚረጭ ከመጣ አይናቸውን ሳያሹ ይቀይሩታል ።

"ይሽው የናንተ ጋዜጣ በጨረታው አይገደልም ነው የሚለው?" አሉና ሳቁ ።

"አዎ ባፈ! ግንኛውም ነገር በጨረታው አይገደ ድም!"

አንድ ጠቆር ያለ ፣ ቦርጫም ሰውዬ ኮረጆውን አንጠል ጥሎ ዘው አለ ። ፊቱ ተኮሳትሯል ። ግልምጫው ከሚጉረጠረ ጡት አይኖቹ ጋር ሲታይ ከሞቀ አምባ ጓሮ አምልጦ የመጣ ያስመስለዋል ።

"ቢራ! ቢራ!" አለና በወይዘሮ ባፈሳ ላይ ተኮሳተረ ።

"ሀሩይ ሙት! ዛሬ እንዴት ይሙቅ ቤቱ? ስትቀርብኝ ጊዜ ጭንቅ አለኝ ። ቢራ እጠጣለሁ" አሉት የውሸት ሳቃቸውን እያፈኑ ።

"ጠጭ! ማን ከልክሎሽ! እኔ ሀሩይ ቢራ እንጂ ወሬ አልጋብዝም!" አለና በድንቃለም ላይ አፈጠጠ ። ኮረጆውን ከፍቶ 'የዛሬዱቱ ኢትዮጵያ' ጋዜጣ አወጣ ።

"ዛሬ የወጣ ነው እንዴ?" ድንቃለም ነበር ።

መልስ አላገኘም ።

"አንድ ጊዜ ታውሰኛለህ? ይቅርታ ግን..."

"ምን ያደርግልህል? የፃፍከው ራስህ ፤ ያዘጋጀኸው ራስህ ፡ ለምን ላንበው ትለኛለህ? አዲስ ነገር የለውም ። የውሸትና የውሸንብር ሚስቶ ነው!" ሀሩይ የቢራ ጠርሙሱን አነሳ ። ቦርጩን አሻሸና ከለበሳት ።

"የውሸትና የውሸንብር ሚስቶ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው?"

"አርፈህ ጠጣ! ግን አናገረህ አሁን? ሀግ ሳስከብር እንጂ ወሬ ስቃርም አልዋልኩም ። ልረፍበት!" አለና ሀሩይ ጋዜጣውን አጣጥፎ የኩረጀው የውጭ ኪስ ውስጥ ከተተው።

"ወሬ የሚቃርም ማነው?"

"ወሬኛ ነዋ!"

"ወሬኛው ማነው?" ድንቃለም ቱግ አለ ።

"አጥብቆ ጠያቂ የእናት ሞት ይረዳል !' አሉ" ሀሩይ ፈገግ አለና "ጋዜጠኛ ነዋ! ጠበቃ መሰለህ? የወሬ ቋት!..."

ድንቃለም አላስጨረሰውም ። "የት ታውቀኛለህ? እብድ ነህ?" አለው ሲጋራውን ሊለኩስ ክብሪት እየጫረ ።

"የወሬ ቋት ! ይልቅ ጠጣ! ከኋላህ መጥቼ ሶስት መጠጣቴ ነው ። አንተ ጡጠ የሚጠጣ ህፃን ይመስል አንዲን ለመጨረስ ታቃትታለህ!"

ወይዘሮ ባፈሳና ጠበቃው ሀሩይ አንድ ላይ ሳቁ ። ድንቃለም ሲጋራ ለኮሰ ።

ጠበቃው ከፍተኛ ቅናት ስለሚሰማው ወይዘሮ ባፈሳ ቤት ሲጠጣ ያገኘውን ሁሉ ይገላምጣል ። በነገር ዱላ

ይወግራል ። ድንቃለምን ያውቀዋል ፡ ከወይዘሮ ባፈሳ ቤት ወጣ ሲል በእግሩ እንደሚተካ ።

ጠበቃው ሀሩይ ያን እለት አዳሩን ከወይዘሮ ባፈሳ ጋር ለማድረግ ወስኖ የመጣ ነበር ። እቅዱ እንዳይሰናከልበት ድንቃለምን ለማባረር ከወዲሁ ነገር ጀምሯል ።

"ተጫወቱ እንጂ! የምን ዝም ዝም ነው?" ብለው ወይዘሮ ባፈሳ በሁለቱም ላይ አፈጠጡ ።

"ቢራየ አለቀች!" አሉ በዘፈን ቅላፄ ። ጠርሙሷን አንስተው ወደ አይናቸው አስጠግተው ተመለከቷት ።

"ጋዜጠኛው አይጋብዝሽም ማለት ነው?" ጠበቃው ሀሩይ ነበር ።

"ድንቄ!" ድንቃለምን የጎሪጥ ተመለከቱት ፡ ቀይ ዳማ ፊታቸውን በሚያማባባ ፈገግታ እየቃኙ ።

"ጠጪ!" አለ ድንቃለም በታከተ አነጋገር።

"ታድዬ!" አሉና ወይዘሮ ባፈሳ እየተገናደሱ ወደ ጓዳ ገቡ ።

"አንድ ቢራ ብቻ ነው?" ጠበቃው ሀሩይ ድንቃለምን እየተመለከተ ሳቀበት ።

ወይዘሮ ባፈሳን ጨምሮ ጋዜጠኛውና ጠበቃው ተፋጠዋል ። በመካከላቸው ከባድ ዝምታ ሰፍኗል ። ጠበቃው ፡ ጋዜጠኛው ድንቃለምን የሚያስወግድበት መንገድ ያሰላሰላል ። ጋዜጠኛው ደግሞ የአዳሩ ጉዳይ ብዙም ሳያሳስበው ስለሙያው ፡ ስለስራው ፡ ስለኑሮው...ያስባል ፡ ይጨነቃል ፤ ይሰጋል ። አደጋ እየታሰበው ተጠቧል ።

ወይዘሮ ባፈሳም ያስባሉ ። ይኸው ፍጥጫ የት እንደሚ

ደርስ አስግቷቸዋል ። ከጋዜጠኛውና ከጠበቃው አንዱን ማስወጣታቸው የማይቀር ነው ። ከተቻለ አንዱን ይሸነግሉ ታል ፣ የተለያየ ዘዴ ፈጥረው ። ሽምግልናውና ማግባባቱ ካልሰራ "በሀግ አምላክ!" ብሰው እሪታቸውን ሊለቁት አቅደዋል ።

ማንን እንደሚያስወጡ ግን ጨንቋቸዋል ። ጋዜጠኛው ድንቃለም ጥሩ ተጫዋች ነው ። አንደበቱ ይጣፍጣቸዋል ። በፍቅር ጨዋታ ያረካቸዋል ። ግን በቂ ገንዘብ የለውም ። በቂ ገንዘብ ስለሌለው ደግሞ ሊያርቁት አይፈልጉም ። በመልክ መልካምነቱ ከጠበቃው ይመርጡታል ። ረዘም ያለ ቁመና ውና ቅላቱ ፣ ጎላ ያሉት አይኖቹና ሉጫ ፀጉሩ ማርኳቸዋል ።

ጠበቃው ሀሩይ ደግሞ በመልኩም ሆነ በፍቅር ጨዋታው ከቁጥር የሚገባላቸው አይነት አይደለም ። በጣም ይደክምባቸዋል ። ጐኑ አልጋ በነካ በጥቂት ደቃቂዎች ውስጥ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ይወስደዋል ። በዚህ ስንፍናው ጁንቁ ታል ። ቢሆንም ግን የማይነጥፍ ገንዘብ አለው ። ግብግው የሚያኮራቸው ነው ። አያፍሩበትም ።

ብዙ ካሰላሰሉ በኋላ የገንዘብ ጉዳይ ላይ ልባቸው አልቆርጥ አለና ጋዜጠኛው ድንቃለምን ለመሸኘት ወሰኑ።

"ምን ልበለው? አዎ! 'ሀሩይኮ ለጋብቻ ፈርሞልኛል ። ሚስቱ ማለት ነኝ ። ስለዚህ ዛሬ ቤትህ ግባ! ሌላ ጊዜ አስደስትሀለሁ' ብለውስ? እምቢ ቢል ግን በጥበቃ ጓደኞ አስይዘዋለሁ ። በቃ!" እያሉ በሀሳባቸው ዘዴአቸውን ሁሉ አውጠንጥነው እንዳበቁ ድንቃለምን ሊጠሩት ከመቀመጫ

ቸው ሲነሱ ሌላ ሰው ዘው አለ ።

ባፈ! ለኔም ቢራ...ለአንቺም ቢራ!" አለ በንርናና ድምፅ ፣ ገና ደጃፉን እንደተራመደ ። የአራት ኪሎው ደላላ ቾምቤ ነበር ።

ቾምቤ የታወቀ ደላላ ነው ። ታዋቂነቱ በድላላ ብቻ አልነበረም ። ጉልቤም ነው ። ቾምቤን ማን ደፍሮ ይናገረዋል! ማጅራት መቺም ነው ይባላል ።

ቾምቤ የወይዘሮ ባፈሳ የኖረ ውሽማ ነው ። የኪራይ ቤት ፣ የሚሸጥ መኪና ፣ ቪዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ሲደልል ውሎ ማታ ወደ ወይዘሮ ባፈሳ ቤት ብቅ ይላል ። የሚጠጣው ቢራ ነው ። ከቢራ ውጭ ሌላ አይቀምስም ። በቀናው ሰዋን የወይዘሮ ባፈሳ ጓዳ ቀንና ማታ ክፍት ይሆንለታል ። ደባል ይመስል ውሎውም አዳሩም ከዚያው ነው ። መኝታ ካማረው "ሞት የሸተተው አለ? ሞትን ከቾምቤ በነፃ ማገኘት ይቻላል!" ይልና ወይዘሮ ባፈሳ ላይ ያፈጠጡትን ጠጭዎች ይገላምጣል ። ያኔም ሁሉም ሹልክ ሹልክ እያለ ይወጣለታል ፣ ሂሳቡን እየከፈለ ። የቤቱ በር ወዲያው ይዘጋል ፣ ገና ሳይመሽም ቢሆን ።

"ሞት የሸተተው አለ? በነፃ እጋብዘዋለሁ!" ሲል ቾምቤ እንደልማዱ ጮኾ ጋዜጠኛው ድንቃለምና ጠበቃው ሀሩይ ላይ አፈጠጠ ። "ሂሳብ ከፍለውሻል ባፈ? እንዚህ ትኋኖች!" የጋበዛቸውን ቢራ ጠርሙስ አንቀው በኩራት የተኮፈሱትን ወይዘሮ ባፈሳን ቃኛቸው ።

"እያየሀቸው አይደል ቾምቤ?"

ድንቃለም ከኩቱ የውስጥ ኪስ ድፍን ሃምሳ ብር

ሲያወጣ ፣ ጠበቃው ሀሩይም ኪሱን ፈትሾ የገንዘብ ቦርሳውን መዘዘ ።

እያንዳንዳቸው መልሳቸውን ከወይዘሮ ባፈሳ ተቀብለው አቀርቅረው ሊወጡ ሲሉ "ቶሎ! እኔ ቾምቤ!...እንደ ጌሾ ሳትወቀጪ ሁልሽም ቶሎ ጥፊ!" በማለት ድልህ አይኖቹን አጉረጠረጠባቸው ።

"ባፊ ቢራ ድገሚኝ!" ሲል ተኩራርቶ ቾምቤ መቀመጫውን ተደላድሎ ከመያዙ ባፈና በር ላይ የሚቀባበል የመሳሪያ ድምፅ ተሰማ ። ቾምቤና ወይዘሮ ባፈሳ በፍጥነት ወደበሩ ብቅ ሲሉ የአራት ኪሎው 'ጥበቃ ጓድ' ኡስማን መሳሪያውን በጠበቃውና በጋዜጠኛው ላይ ደግኗል ። "እጅ ወደ ላይ!" ጮብለው ሁለቱም እጆቻቸውን ሰቅለው ቆመዋል ። "ናውጣ...አይንህ ይውጣና!" አለው ኡስማን ቾምቤን የጮሪጥ እያየው ።

ቾምቤ ኣስከ ክርኑ የሰቀሰቃቸው እጅጌዎቹን ቁልቁል እየዘረጋ ወጣና ከነድንቃለም ጋር ተቀላቅሎ ቆመ ።

"ቀጠሮዋችሁ ፀረ አብዮት ወረቀት ለመበተን ነው ፣ አይደል? አሁን ስንት ሰአት ነው?" የመሳሪያውን አፈ ሙዝ እያሂዘረ ደነፋባቸው ። ከድንጋጤያቸው የተነሳ የሚሉት አልነበራቸውም ። "እንደናንተ አይነቶቹን ያለምንም ጥያቄ መድፋት ነበር !! ቶሎ በቀጥታ ወደ ቤታችሁ!!"

ሶስቱም ወደየመንገዶቻቸው ገቡ ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኡስማንና ባፈሳ ከርቀት ሰላምታ በቀር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበራቸውም ፣ ለክፉ ቀን ፈጥኖ ደራሽ ይሆንል ኛል በሚል እምነት ባፈሳ ያስጠጉት ኡስማን ጥበቃ ጓድ

ከተባለ በኋላ ነበር ።

የወይዘሮ ባፈሳን ብር ራቡ ከውስጥ ቀረቀረና ልብሶቹን አወላልቆ የተንጣለለው አልጋቸው ላይ ተጋደመ ፣ ወይዘሮ ባፈሳን በጉጉት እየተጠባበቀ ።

እቅፉ ውስጥ እንደገቡለት "እነዚህን ሰዎች የት ታውቂያቸዋለሽ? አንቺ ወስላታ!" አላቸው ።

"እረ እኔ እቴ! ..ያት አውቃቸውና? ገላገልከኝ ።"

"ተጠንቀቂ! ያሳሰቁሻል።"

"እሽ! ..." አሉት ልብሳቸውን እያወላለቁ ።

*ለብርሐኑ አክርር (ሀይል የካቲት) ጥራሪ 1982

የአንጀራ ገመድ

"ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው ?" እያለ አላፊ አግዳሚውን የሚለከፈው ወፈፌ በአንድ ወቅት አትክልተኛ ነበር ። በሆነ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከአንድ ዓመት በላይ በቅን መንፈስ ያገለገለ ሲሆን አንድ ቀንም ከሥራው ቀርቶ አያውቅም ። ያረፈደባቸው ቀናት ቢኖሩ እንኳ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ። በየወሩ ያችን ደሞዙን ለመቀበል ካልሆነ በቀርም ወደ ዋናው ህንፃ ፊቱን አዙሮ አያውቅም ። ከሌሎች ሰራተኞችም ጋር የሚያገናኘው አምብዛም ጉዳይ አልነበረውም ። በእረፍት ጊዜው ጨዋታ ሲያምረው ጠጋ የሚላት አንዲት ፅዳት ሰራተኛ ብቻ ነበረች ። ደመቀች ትባላለች ። ከእርሷ ጋር ሲያወራ በአጋጣሚ ሌላ ሰው ደብለቅ ቢል እንኳ ከመቅጽበት ወደዝምታ ይሸጋገርና ራሱን በሀሳብ ባህር ውስጥ ያሰጥ ማል ። ችግሩ ከአይናፋርነት የመነጨ አይመስልም ። አንደበተ ርቱዕ ነው ።

ከስራው ከተባረረ መንፈቅ ሳይሞላው ለወፈፌነት ተዳርጎ አስደንባሪ ፍጡር ከሆነ ዓመታት አልፈውታል ። ለመባረሩ ምክንያት የሆነበትንም ጉዳይ የሚሰማው አጣ እንጂ ያነሳል ። ሆኖም መታመኑ ቀርቶበት ከልብ አድምጦ ያዘነለት ወይም ያፅናናው አንድም ሰው አላገኘም ።

በአትክልተኝነት ከቆየባቸው አሥራ አራት ወራት የመጀመሪያዎቹን ሦስቱን ብቻ በቀን ሞያተኛነት አስቆጥሮ በአራተኛው ቋሚ ሆነ ። የመጨረሻዎቹን ቀናት ያሳለፈው ግን በምሬት ነበር ። የተቀጠረበትን እለት እየረገመ ። ተላላኪ ይመስል ፣ ያለወትሮው ከፐርሶኔሉና ከሕዝብ ግንኙነት ክፍል ኃላፊው ቢሮዎች ወጣ ገባ ማለቱን ያበዛው ያኔ ነው ። ለስንብትም የበቃው ከሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ጋር የፈጠረው አምባጓሮ እንደሆነ ይወሳል ።

የሚያስገርመው አንድ አትክልተኛ መሬት መርገጥ ከሚጠየፍ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ጋር የከረረ ቅራኔ ውስጥ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ነው ። አጋጣሚው ያልተለመደ በመሆኑ ፣ ምክንያት ብሎ የሚያቀርበውን ሀሳብ የማያዳምጠው ሞቂያምነውም ቢያጣ አያስደንቅም ። ሆኖም ‹‹ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው ?›› እያለ ማነብነብ የጀመረው በስንብቱ ዋዜማ ነው ።

ከስንብቱ በኋላ ያ ሰው በአዲስ አበባ ከተማ ‹‹ወፈፌው›› በሚል መጠሪያ ብቻ ታውቆ ስሙ ተረሳ ። አንሙት ካሴ መባሉን ግን የሚያውቅ ያውቀዋል ። የደብተራ ካሴ ሁነኛ የበኸር ልጅ ፣ ለ ያውም ወንድ እርሱ ብቻ ሲሆን ፣

ተወልዶ ባደገበት በብቸና አውራጃ ፣ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ፊደል ቆጥሮ ለድቁና በቅቶ ነበር ። ታታሪ ገበሬም ነበር ይባላል ። ዘመኑ ያመጣበት የገበሬ ማህበራት ቱማታ ፣ የሠፈራና የሚሊሺያ ምልመላ ግርግር አስመርሮት በድንገት ወደ አዲስ አበባ ጠፍቶ ከመጣ በኋላ የውኃ ሽታ ሆኖ የቀረ ሰው ነው ።

አድራሻውን አጠያይቆ ከደረሰበት የሩቅ ዘመድ ዘንድ ተጠግቶ የቋጠራትን ጥሪት እስኪጨርስ ኑሮ አልከፋውም ነበር ። ከአንድ ዓመት በኋላ ግን ዘመድ ተብዬውም ሆነ የክተማው አስተናጋጅነት አከተመበት ። የሚላስ የሚቀመስ እስኪያጣ ወጣ ወረደ ። ሽሮ ሜዳ አካባቢ ፣ የአንድ ድርና ማግ ኒጋዴ ሚቲዎች ፊደል አስቆጣሪ ሆነ ። የመንደሩንም ህፃናት አሰባስቦ በማስተማር ጥቂት ወራት አሳለፈ ። ግን ያች የቁጥቁጥ ገቢው የዓመት ልብሱን ቀርቶ የዕለት ጉርሱን የምትሸፍንለት አልሆነችም ። ቀጥሎም በመርካቶ ፣ ከዚያም በተክለሃይማኖት ፣ በኋላም በሰንጋ ተራ አካባቢዎች በሽቃይ ነት ተሰማርቶ ሲያገኝ ጠግቦ ፣ ሲያጣ ደግሞ ጦም ማደሩን ተላመደው ።

ከዕለታት አንድ ቀን ፣ በፋሲካ ዋዜማ ፣ በለስ ቀናው ። ገመድ ብጤ አንጠልጥሎ ከአንድ በግ ገበያ ወደሌላ እየተዘዋወረ ሲሸከም ውሎ ምሽት ላይ ከክንፈ በልሁ ጋር እግዜር ያገጣጥመዋል ።

ክንፈ እንደዛሬው ቦርጩ የሚዋልልና ወደ ኋላው የሚለጠጥ ሰው አልነበረም ። አንጀቱ በረሃብ የታጠፈበት ይመስል ፣ የሚራመደው ጉብጠ ነበር ። ግን እንደ ፊኛ

ከተወጠረ የኪስ ቦርሳው አራት ባለሃምሳ ድፍን ብሮች መዝዘ እንዲት ጠቦት ሲገዛ ያየው አንሙት ይህን ግምት የለወጠው ያኔውኑ ነው ። አንከብክቦለት ጠቦቷን እስከመኪናው ለማድረስ ዋጋ አልጠየቀውም ። የተከፈለውም ካሰበው በላይ ሆነለት ።

"አርደህ ብልት ማውጣት ትችላለህ ?" አለው ክንፈ ፣ ያሮጌ አፔሉን የኋላ ኮፈን ከፍቶ በጉን ሰፍራ እንዳስያዘለት ።

"አዬ ጌታዬ !" ሲል መለሰለት በአጠያየቁ ተገርሞ ። እንዲያ መባሉን እንደ ነውር ቆጥሮታል ።

"እችላለሁ ወይም አልችልም ማለት እንጂ ጥያቄዬ ግብራሪያ አያስፈልገውም" በማለት አንድ ብር ወርውሮለት ዘወር ሲልበት አንሙት አላስቻለውም ።

"ያቂግሁበት ነው ብዬ ነዋ!" አለው በልመና ቅላፄ ።

"በል ግባ" ብሎት የመኪናውን የኋላ በር ከፈተለት ።

ገብቶ ከክንፈ ኋላ ካለው ባዶ ወንበር ጫፍ ላይ ተቀመጠና ሚዛኑን ለመጠበቅ ሲል የክንፈን መቀመጫ በሁለት እጆቹ ተሞረቦዘ ።

"በዚያኛው ጥግ !" አለው በጣቶቹ እየጠቆመው ። "ዘና ብለህ ተቀመጥ ።"

እየተንፏቀቀ ተጠጋና እግሮቹን ዘረጋ ። አቀማመጡ የመጋደም ያህል ነበር ። ክንፈ ዘወር ብሎ እንኳ ሳያየው መኪናውን እያከነፈ ከቤቱ ደርሶ ጡሩምባውን ለቀቀው ።

አንዲት ጉቶ ቢጤ ፈርጣማ ሴት የውጭውን በር ከፍታ አስገባቻቸው ። ከአለባበሷና ከእጅ አነሳሷ የክንፈ ሠራተኛ እንደሆነች አንሙት ገመተ ። በሩ ሲከፈትለት ጣደፍ ብሎ

ወጣና በጉን እየጐተተ ወደ ጓሮ አመራ ።

ሰፊ ግቢ ያለው ዘመናዊ ቤት ነው ። ግን ከመጠን በላይ ጭር አለበት ። ቢላዋዎች ፣ ለመለቃለቂያ የሚሆነውን ውኃና ሌሎች የሚያስፈልጉትንም ነገሮች ወጣ ገባ እያለች የምታቀራርብለት ያችው ሠራተኛ ብቻ ነበረች ።

"ይባርኩልኝ በያቸው" አላት ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ ።

ክንፈ በመስኮት ብቅ ብሎ "አንተው አትባርከውም ?" አለው ።

"እስላም ልሁን ክርስቲያን ምኔ ታውቆ ?"

"እስላም ሆነ ክርስቲያን ፣ የቀረበለትን ማዕድ እንደየእምነቱ ባርኮ እስከ ቀመሰ ፣ ማንስ ቢያርደው ምናለበት ?"

"አበስገበርኩ !" ብሎ አንሙት ሲያማትብ ፣ ክንፈ ክትክት ብሎ ሳቀበት ።

"በል እረድ ።"

"እሺ ። በስመአብ ፣ ወወልድ ፣ ወመንፈስ ቅዱስ ..."

"ክርስቲያን ነሃ !"

"የቄስ ልጅ ነኝ" አለው አንሙት ፣ ተፍ ተፍ እያለ ። "ዲያቆንም ነበርኩ ።"

"የት ?"

"ጐጃም ።"

"ወደ አዲስ አበባ ምን አመጣህ ?"

"ስራ ፍለጋ ። እድሌ ሆኖ በከንቱ ስማስን ዘንድሮ አራተኛ አመቴ ።"

"ስራ መች ጠፋ ? የጠፋው ሰራተኛ ነው ። አለሀ ብሎ

የሚቀርበው ሁሉ ዳተኛ ወይ ሌባ ሆነ ።”

“አይ ጌታዬ ! ሁሉ መች እንዲያ ሆነና ?!”

“እንዲያ ብሎ አንገቱን ሰብሮ የሚገባው ነው በመጀመሪያ ደሞዙ ቀና የሚል ፤ በሁለተኛው ደሞዙ ደረቱን የሚገለብጥ ፤ በሦስተኛው አሰሪውን የሚገላምጥ ፤ በአራተኛው ከቀበሌ እስከ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሚያሯሩጥ ፤ ...”

“እኔ እንዲያ ያለሁ ሰው አይደለሁም” ብሎ አንሙት ቀና ቢል ክንፈ የለም ። ወደ ተግባሩ ተመልሶ ቀና ደፋ ሲል የቤት ሰራተኛዋ ብቅ አለች ፤ ልታግዘው ።

“የምጠጣው ውኃ !” አላት ። ላቡ በግምባሩ ይንቆረቆራል ።

ወደ ቤት ገባ ብላ ማንቆርቆሪያና ብርጭቆ ይዛለት ተመለሰች ። የሞላችለትን በአንድ ትንፋሽ ገልብጦ ቁና ቁና እየተነፈሰ ብርጭቆውን ሲመልስላት “ልድገምህ ?” አለችው ።

እጅ በመንሳት አምንታውን ገለጸላት ። ሞላችለት ። ከዚያም ማንቆርቆሪያውንና ብርጭቆውን ውኃ ልክ ላይ አስቀምጣ ትእዛዙን ስትጠባበቅ “ሌላ ሰው የለም?” የሚል ጥያቄ አንሙት ወረወረላት ።

“ለምን ?”

“የሚያግዘኝ ።”

“ለዚሁ ብዬ አይደል የመጣሁት ?”

“በግቢው ያላችሁት እርሳቸውና አንቺ ብቻ ናችሁ እንዴ ?”

“አይመለከትህም ። የመጣህበትን ጨርሰህ ውጣ”

አለችው በቁጣ ። አነጋገሯ እንደቁመናዋ ከርር ምጥን ያለ ኮስታራ ብጤ ናት ።

“ይብላኝለት አብሯት ውሎ ለሚያድር !” አለ አንሙት በሆዱ ።

በዝምታ ስራውን ጨርሶ አስረከባት ። በዝምታ ተለታልቆ እጆቹን ሲያራግፍ “ጠላ ካስፈለገህ ፤ ያውልህ” አለችው እንደተኮሳተረች ።

የዶሮ ዓይን የመሰለ ወፍራም ጠላ ስለነበር ሊግደረደር አልፈለገም ። አከታትሎ ሁለቱን ብርጭቆ በቁመ እንደለመጠጠ ክንፈ ብቅ አለለት ።

“ቆዳውን ውሰደው ። ለመንገድ ይኸ አይበቃህም?” በማለት ዝርዝር ብሮች ሲሰጠው አንሙት እጅ ነስቶ ተቀበለ ።

“አነሰህ ?”

“አረ ጌታዬ ! በቂዬ ነው ። እግዜር ይስጥልኝ ለአመት ሰው ይበልዎ!” የሚል ምርቃቱን አክሎለት ቆዳውን አነሳ ።

“ስራ ፈላጊ ነኝ ብለሃል ።”

“አቤት ?” አለ አንሙት ። ጆሮውን አላመነም ።

ቋሚ ስራ ትፈልጋለህ ?”

“እንዴታ ጌታዬ !”

“ተያዥ አለህ ?”

“አለኝ ።”

“ነገ ጠዋት ብቅ በል ።”

“ተያገርን ይገዬ ?”

“አዎ ።”

አንሙት እውነት አልመሰለውም ። እየፈነጠዘ ከክንፈ ገቢ ወጥቶ ወደ መርካቶ ገሠገሠ ። ቆዳውን በስድስት ብር ቸብችቦ ከቀን ገቢው ጋር አዳመረው ። የዚያን ዕለት ቀንቶታል ። ባገኛት አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም ምን እንደሚያደርግ እቅድ አወጣ ። በመጀመሪያ ድቅን ያለበት የአክፋይ ስጦታ ነው ። ከጐጃም ሲመጣ ላስጠጋው የሩቁ ዘመዱ አንድ ነገር ይዞ መሄድ እንደሚገባው ታየው ። በተያዥነትም ሊያቀርበው ያሰበው እርሱኑ ነው ። ዘመዱ ከእጅ ወዳፍ በሆነ ገቢ የሚተዳደር የፋብሪካ ሰራተኛ ቢሆንም ፥ የራሱን ጎጆ የቀለሰ ፥ ባለትዳርና የልጆች አባት እንደመሆኑ ለአንድ ጠርሙስ ካቲካላ መግዣ ሰባት ብር መደበለት ።

በርበሬ ተራ ፥ ከዋናው መንገድ ገባ ብላ ከምትገኘውና ከአምስት ደባሎቹ ጋር ከሚኖፎባት አንዲት ማድቤት ጐራ አለ ። በዚያን ዕለት ቀድሞ የገባው እርሱ ነበርና ሰሌኖቻቸው ተሸቅለው ከዋሉበት ጥግ አንድ በአንድ እያነሳ ካራገፈ በኋላ አቀጣቶሎ አነጠፋቸው ። የቀን ልብሶቹን በስርአት አጣጥፎ ትራስ አደረጋቸውና አሮጌ ብርድልብሱን ተከናንቦ ተጋደመ ። ጓደኞቹ እየገቡ ቦታ ቦታቸውን ያዙ ። ሁሉም ሞቅ ብሎዋቸው ስለነበር ጉናቸው ገና መሬት ከመንካቱ እንቅልፍ ወሰዳቸው ። ሲገላበጥ ያደረው እርሱ ብቻ ነበር ።

ከሁሉም በፊት አንሙት ማልዶ ተነሳ ። ከመኖሪያቸው ፊት ለፊት ወደምትገኘው ሻይ ቤት ተሻግሮ ፊቱን በውኃ እበስ አደረገና ለቁርሱ ግንፍልፍል አዘዘ ። ተቆልሎ ቀረበለት ። ያን በሁለት ኩባያ ሻይ አወራርዶ እያገሳ ወጣ ።

ጠርሙስ ካቲካላውን ከየት እንደሚገዛ ወስኗል ። በቀጥታ የሄደውም ወደ ወይዘሮ ሰውነቴ መሸታ ቤት ነው ። የአገሩ ሰው ናቸው ። አረቄያቸውንም የሚያስመጡት ከጐጃም እንደሆነ ይወራላቸዋል ። በዚህ ላይ ያያትን ሁሉ የምታማልል ምንታምር የምትባል ኮረዳ አሻሻጭ ስላለቻቸው ገበያቸው ምንጊዜም ሞቅ ያለ ነው ። አንሙት በየቀኑ ጐራ እያለ ፥ በተለይ ከምንታምር ጋር ፥ ዝምድናውን ካጠናከረ ቆይቷል ። ጠርሙስ ካቲካላውን ያለማስያዣ የለቀቀችለትም እርሷው ነበረች ።

ከዘመዱ ቤት የደረሰው የሩጫ ያህል በፈጠነ ርምጃ ነው ። እንደገባም ፥ ወጥ አይቀርምና ፥ ያልተነፋፋቁ ቢሆኑም ተሳሳሙ ። ዳቦና ጠላ ቀረበለት ። ዳቦውን ዋምሶ ጠላው እንዳይቀዳለት ተማፀነና ወደ መጣበት ዋና ጉዳይ ገባ ። የትናንት ታሪኩን በዝርዝር ካወሳ በኋላ የአዎንታ ምላሽ በማግኘቱ በጣም ተደሰተ ።

በዚያኑ እለት ተያይዘው ወደ ክንፈ ቅጥረ ግቢ ሲዘልቁ ፥ ክንፈ በጐጆማው ላይ ጋቢ ደርቦ በረንዳው ላይ የጠዋት ፀሐይ ይሞቅ ነበር ። ያችኑ ገደል ፊት ሠራተኛውን ጠርቶ ወንበር አቀረበችላቸው ። ዳቦና ጠላም መጣላቸው ። አንሙት ጠላውን የተጐነጨው ከብዙ መግደርደር በኋላ ነበር ። ለዚያውም ከእንዲት ብርጭቆ በላይ አልሄደም ።

ክንፈ የተያዥን መታወቂያ ወረቀት አይቶ ፥ አድራሻውን በማስታወሻ ላይ ከመዘገበ በኋላ ሦስቱም በፈረሙበት በአንዲት ብጣሽ ወረቀት የቅጥር ፎርማሊቴው ተከናወነ ። አንሙት ቀለቡንና መኖሪያውን ቀጣሪው ችሎልት ፥ ፀወር

ሃያ አምስት ብር ክፍያ ፡ ለአዲስ የህይወት ምዕራፍ በቃ ። የስራውን አይነት መዘርዘረ አላስፈለገም ። ዘበኛ ፡ አትክል ተኛ ፡ ተላላኪ ፡ … ሁሉንም መሆን እንደሚገባው ቀጣሪና ተቀጣሪ የተስማሙ ይመስላሉ ።

ክንፈ በህይሉ ዋዛ ሰው አይደለም ። በእድሜው አርባዎቹን አመታት ለማገባደድ የተቃረበ ሲሆን ሃያ አምስት አመታቱን በስራ አለም ያሳለፈ ነው ። ያልገባበት የመንግስት መስሪያ ቤት የለም ። የስራ ልምዱም የዚያኑ ያህል ሰፊ ነው ። ሲጀምር ተላላኪ ነበር ። የመዝገብ ቤት ፀሐፊም ሆኗል ። ከአንድ መስሪያ ቤት ወደ ሌላ የሚሸጋገረው በእድገት እየሆነ በአንድ ወቅት ረዳት ፕሮሰኔልም እስከመ ባል ደርሶ ነበር ይባላል ። በመጨረሻም አሁን ባለበት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሕዝብ ግንኙነት ኃላፊነት ሽር ጉድ እያለ ነው ።

ክንፈ በምላሱ ጤፍ ይቆላል ። እንደ አብሮ አደሳቹ በቀለም ትምህርቱ እምብዛም አልገፋም ። ለአንቱታ ደረጃ የበቃው በሙሌነቱና በተግባቢነቱ ነው ። እርሱ ‘ዲፕሎ ማሲ’ ይለዋል ። የስራውንም ጠባይ በዚያ መስፈርት አስቀምጦት ፡ ያጠመደ ሰው ከቢሮው አያገኘውም ። ሳምሶና ይጥ ሠርሳውን አንጠልጥሎ ከአንዱ ቢሮ ወደ ሌላው ሲሮጥ ፡ ከአንዱ ጋር ሻይ ፡ ከሌላው ጋር ቡና ሲል የጠዋቱን የስራ ሰአት አሳልፎ ከሆነ ከሰአት በኋላ እስካናካቴው ከዚያ ግቢ ደብዛው ይጠፋል ። ስራው ወደ ሌላ መስሪያ ቤት ወስዶታል ማለት ነው ።

የዘመን መለወጫና የገና በአላት በመጡ ቁጥር በርካታ

ካርዶችን አሳትሞም ይሁን አስገዝቶ ለአለቆቹና ወደፊት ሊተዋወቃቸው ላሰባቸው የሌሎች መስሪያ ቤቶች ባለ ሥልጣናት ይበትናል ። ለበአላቱ በሰላም በመድረሳቸው የተሰማውን ደስታ ከመግለጽ አልፎ ተርፎ በትጉህነታቸውና በሰራተኞቻቸው ዘንድ ባላቸው ተወዳጅነት ወደፊት ለታላቅ ቦታ የሚታጨ እውነተኛ የአገሪቱ ዜጎች እንደሚሆኑ ምኞቱንም በእርግጠኛነት ያሰፍርላቸዋል ። ሽንገላው የሚያስገኛለትም ጥቅም በዚያው መጠን ሰፊ ነው ።

ለማንም ሰው ሁል ጊዜ ሀሳቡ ሁሉ አይሳካለትምና ክንፈ አንድ ቋሚ ችግር አለበት ። ትዳር አልተዋጣለትም ። እንደ መስሪያ ቤቱ ፡ ሚስትም እድሜ ልኩን እንደቀያየረ ነው ። አንዷ ባማሟቀችው ቤቱ ሌላዋ ትገባበታለች ። እርሷም እግር በእግር በሌላዋ ትተካታለች ። ደግነቱ ከአንዳቸውም ልጅ አላፈራም እንጂ ቢያፈራ ኖሮ ቁጥራቸው በሽበቱ ልክ በሆነ ።

አንሙት ይህን የተረዳው ስራ በጀመረበት እለት ነው ። በፊትለፊት በር የተቀበላትን በኋላ በር መሸኘት የየእለት ተግባሩ ሆነ ። በዚህ ላይ ከሰራተኛይቱ ጋር ሊግባባ አልቻለም ። የቤቱ ፈላጭ ቆራጭ እርሷው ሆና ፡ ሲያሰኛት ኩርማን እንጀራ ትጥልለታለች ። ካላሰኛት ጠሙን አውላው ልታሳድረው ይዳዳታል ። አንዳንዴም ወደ ገበያም ሆነ ወፍጮ ቤት ስትሄድ እንደ ግል አሽከሯ የምታስከትለው ጊዜም ነበር ። እናም አንሙት የእንጀራ ገመዱን ላለማሳጠር ሲል ችሎ ግደሩን እንደሁነኛ አማራጭ ወስዶ ብዙ ታግሷል ። እንዲያ ግድረጉም ስለ ክንፈ ተጨማሪ ወሬ እንዲያገኝ ረድቶታል ።

"ለምን ትዳር አይዙም ?" አላት አንድ ቀን ፡ በመሀላ
ችው ሰላም ወርዶ በመጨዋወት ላይ ሳሉ ።
"ማግባት መፍታቱ ሰልችቷቸው ።"
"ታዲያ እንዲህ ሆነው እስከመቼ ሊዘልቁ ነው ?"
"እንጃ !"
"አንቺ እዚህ ቤት ስንት ጊዜ ሆነሽ ?"
"አመት ሊሞላኝ ነው ። ስገባም አንዲት ሴት ነበረች ፡
ሚስት ተብዬ ። የተለያዩት በቅርቡ ነው ።"
"ምን ይሆን የሚያጣላቸው ?"
"ሰውዬው ሁሌ ያመሻሉ ። ሲያሰኛቸውም በዚያው
ያድራሉ ።"
"አሃ ! በሴቶቹ ጥፋት ያልም በይኛ !"
"እርሱን እርሳቸው ይወቁ ።"
"ለሰራተኞችስ እንዴት ናቸው ?"
ሳቅ አለችና "ደህና ናቸው" ብላው ተሽኮረመመች ።
አንሙትም ነግሩ ገብቶት ፈገግ አለ ።
ይህን በተባባሉ ሰሞን አንድ ቀን ማለዳ ላይ እርሷም
ንዟን ጨቅላላ ተሰናበተችው ። አንሙት ብቻውን ቀረ ።
ቢሆንም ኑሮ አልከፋውም ። ቢችል ራሱ አብስሎ እንዲበላ
ተፈቅዶለታል ። ከደሞዙ በተጨማሪ ከከንፈ እንግዶች
የሚያገኘው የገንዘብ ጉርሻም የበሰለ ምግብ ፍለጋ ወጣ
ገባ ማለት የሚያስችለው ነበር ።
ግቢውን በአትክልት ከማሳመሩም በላይ ልብስ አጥቦ
የሚተኩስ ባለሞያ ነው ። የቤቱን ወለል በየቀኑ መስተዋት
አስኪመስል ይወለውላል ። በንቁ ዘበኛነቱም የሚመሰገን

ሆነ ። በሽልማት መልክም በአንድ ዓመት ውስጥ አንድ አሮጌ
ኮት ፡ ሁለት ሱሪዎችና ሦስት ሸሚዞች አገኘ ።
"እስቲ ሰራተኛ አፈላልግ" አለው ክንፈ አንድ ቀን ።
"በደላላ የሚመጡት ጤና ቢሶች ሆኑ ።"
"እሺ ።"
"ተያዥ ያላት ፡ ቢያንስ በአበሻ ምግብ አሰራር ባለሞያ
የሆነች ፡ ንፅህናዋን የምትጠብቅ" በማለት ሀሳቡን ሲሸርብ
ቆይቶ "ፊቷ የፈካ" አለው ።
"ከፍትፍቱ ፊቱ ይባል የለ" አለ አንሙት ።
"እም ። የእጅ አመል ቢኖርባት ግድ የለኝም ።
ልቆጣጠር ብልም አይሆንልኝማ ። እንደምታየው በቂ
የእኩል ቤት ነውና ለዚያ የሚያደርሳት ጉጉትም አይኖራ
ትም ። ብቻ ነጭናጫና ነገር እንደ መስቲካ የምታላምጥ
እንዳትሆንብኝ አደራ !"
"ግዴለትም ! ሁነኛ ሰው እፈልግልዎታለሁ ።"
"አንተስ ፡ ቤቱ ተስማማህ አይደል ?"
"እግዜር እድሜዎን ያርዝምልኝ ። የጐደለብኝ ምንም
ነገር የለም ።"
"በርታ ! በዚሁ ጠባይህ ከቀጠልክ ፡ ወደፊት ቋሚ
የመንግሥት ስራ አፈላልግልሃለሁ !"

አንሙት ለጥ ብሎ እጅ ነሳ ። ቀኑ ቅዳሜ ነበር ፣ ከሰዓት በኋላ ።

"እና" አለ አንሙት "ከመቼ ጀምሬ ላፈላልግ ?"

"ዛሬውኑ መጀመር ትችላለህ" የሚል መልስ ስላገኘ ለመውጣት ወደ በሩ ሲንደረደር" "ቆይ ! አንዲት እንግዳ ስለምትመጣ ፣ እርሷን አስገብተህ ትሄዳለህ ።"

"እሺ ።"

የውጭው በር ስር በተለመደው ቦታው ተቀምጦ ሰራተኛ የት ብሎ እንደሚያፈላልግ ማውጣት ማውረድ ጀመረ ። የወይዘሮ ሰውነቴ አሻሻጭ ፣ ምንታምር ትዝ አለችው ። ምርጫውም በእርሷ አከተመ ።

ብትለብስና ብታጋጊጥ የሚያምርባት ፣ ትምቡኬ ገላ ናት ። ግምባሯና አገጭዋ ላይ ካሉት የመስቀል ንቅሳቶቿ በቀር ክንፈ ቤት ሲገቡና ሲወጡ ከሚከርሙት ኮረዶች የሚለያት ነገር የለም ። በዚህ ላይ ሳቋ ልብ ይሰርቃል ።

ይህን ሲያሰላስል ፣ በር አንኳክታ የገባችውን ወጣት የመዘናች በምንታምር ስእል ነበር ።

"ምንና ምን !" እያለ ተከተላት ። "ይህች ፀጉር ብቻ ናት ። በእርግጥ ዳሌዋ ከምንታምር ሰፋ ይላል ። ግን እግረ ሰላላ ፣ ቀትረ ቀላል ናት ።..."

በቀለም የተሻሻረነረች አሻንጉሊት መሰልችው ። የቤቱን በር አንኳክቶ ለክንፈ ሲያስረክባት በሲጋራ የበለዙ ጥርሶቿን ብልጭ አድርጋለት "ቴንኪዩ !" አለችው በእንግሊዘኛ ።

"ከውካዋ !" ብሏት በሆዱ "መሄዷ ነው" አለው

ለክንፈ ።

"ሂድ ! ሂድ !" አለው ክንፈ ። ጊዜ ሊያጠፉ አልፈለገም ።

ከተሸለማቸው ሱሪዎችና ሽሚዞች ሻል ያሉትን አጥልቆ ኮቱን ደረበና ውልቅ አለ ። የበረረው በታክሲ ነበር። ከወይዘሮ ሰውነቴና ከምንታምር ጋር እንደ ስጋ ዘመድ ተቃቅፈው ተሳሳሙ ። ግብዣ አወረደላቸው ። እርሱ ግን አልቀመሰም ።

"ምነው ?" አሉት ወይዘሮ ሰውነቴ ።

"መድኃኒት ወስጄ ነው ።"

"ነገር አለሙን ረስተኸው እንደሁ ብዬ !"

"አዬ ! እንዴት ተብሎ ?"

"አምሮብሃል !"

"ይመስገነው !" አለ ወደ ጣራ አንጋጦ ። "ጥሩ ስራ አግኝቻለሁ ።"

"ጐሽ ! የት መስሪያ ቤት !"

"የሰው ቤት ነው ።"

"ምን ዐይነት ሥራ ? ዘበኝነት ?" አሉት ወይዘሮ ሰውነቴ

"አይ ! አትክልተኛ ነኝ ።"

"ደግ ! ይህና ይከፍልሃል ?"

"ቀለብና መኖሪያ ያስቡልኛል ። ደሞዜም አይከፋም ።"

"ታዲያ እንዲህ ጥፍት ይባላል ? ዘመድ አይጠየቅም ?" ምንታምር ነበረች እንዲያ ያለችው ፣ በናፈቀው ፈገግታዋ

እያማለለችው ።

"አልመች ብሎኝ" አላት ምራቁን እየዋጠ ።

አምና ለፋሲካ የወሰደውን የካቲካላ ጠርሙስ ሳይመልስ መቅረቱን ወይም ሂሳቡን አለመክፈሉን ሁለቱም ያስታውሳሉ ። ሆኖም ሰውነቴ ፊት ያን ማንሳት አልፈለጉም።

"ተጫወት" አለችው ምንታምር ።

"ምን ይዤ ?" አላት ። ለስላሳ መጠጥ ቤታቸው እንደማይገባ ያውቃል ።

"እርሷኑ !" አሉት ወይዘሮ ሰውነቴ ።

ምንታምር እንደማፈር ብላ "ቡና ላፍላልህ ? ወይስ ሻይ ?" ስትል ጠየቀችው ።

"ምንም አልሻ ፣ ካንቺ ወዲያ !" አለና አቀፋት ።

እየተሽኮረመመች ጉኑ ሻጥ አለች ። ወይዘሮ ሰውነቴም "መጣሁ" ብለው ከቤት ወጣ አሉ ። ሁለቱ ፍቀረኞች ብቻቸውን ቀሩ ።

"በሩን መለስ አርጊው ።"

"ሆሆ ! መሸተኛ ቢመጣስ ?"

"ከታዛ ይቆያ !" አላት እንደማይሆን እያወቀ ።

"አጣላኛ ከእቴቴ ጋር !" ስትል ተጐናደረችበት ።

"በይ ተይው ! ቀረብሽ !" ብሎ ጭንዋን ለመዘጋት ።

"በሽታ ይለምዝግህ !" በማለት ልትቧጭረው ጥፍሮቿን ስታሾልበት ሁለት እጆቿን ጥርቅም አድርጎ ሳማት ። ውኃ ሆና አንገቱ ስር ገባች ።

በሰመመን አለም ውስጥ እንዳሉ "ስራ ትፈልጊ ያለሽ ?" የሚል ጥያቄውን አቀረበላት ፣ በሹክሹክታ ።

"አግኝቼ!"

"ወይዘሮ ሰውነቴ ይለቁሻል ?"

"ይህን ካቲካላ እንደኑው ስትግፊ ከምታመሽ ፣ ምነው ቀንቶሽ በሄድሽልኝ ፣ምትለኝ እርሷው ናት ። ጡት እናቴ ናት'ኮ !"

"ናቸው ፣ መች ይህን አውቄልሽ ! ተያዥም ይሆኑሻላ ?"

"እንኳን ለእኔ ለሌላም ትተርፋለች ።"

ስለ ክንፈ ቸርነት ፣ ስለቤቱ ሲሳይ ፣ ስለግቢው ማማር ሲዘረዝርላት ምንታምር አፍን ከፍታ ቀረች ። ግሳንግሷን አዝላ በዚያኑ እለት አብራው ብትሄድ በወደደች ።

እየተጐነታተሉ ስለራሳቸውም የወደፊት እድል አወሱ። በቅርቡም የመንግስት ስራ ይዘ ፣ ጐጆዋቸውን ቀልሰው ሰው ለመባል ሲበቁ ታይቷቸው በደስታ ተንሳፈፉ ።

በማግስቱ እንደሚወስዳት ወስነው ሲለያዩ ፣ ምንታምር መንገድ ድረስ ሸኘችው ። እንደአመጣጡ በታክሲ በሮ ክንፈ ግቢ ሲደርስ ጨለምለም ብሏል ። የውጭው በር ሲኮፈት የሰማው ክንፈ ሲንቆራጠጥ ቆይቶ ኖሮ ወደ በረንዳው ብቅ አለና "እህ ? የሄድክበት ቀናህ ?" በሚል ጥያቄ ተቀበለው ።

"አዎ ፣ ተያዥ ያላት ጥሩ ሠራተኛ አግኝቻለሁ ።"

"መልካም ፣ መች ታመጣታለህ ?"

"ከተመቸዎት ነገ ከሰዓት በኋላ ወይም ጠዋት ከረፋዱ

=”

“ጠዋት ይሻለኛል ። ከሰዓት በኋላ እንኳ ቀጠሮ
ኝ ።”

“እሺ ፣ ማለዳ ሄጀ አመጣታለሁ ።”

ክንፈ ወደ ውጭ ለመውጣት የመኪናውን ሞተር
ጀመሩቅ ቆይቶ ወደ ቤት ሲመለስ አንሙትን ጠራውና
ጣ ግለቴ ነው ። አመሽ ይሆናል” አለው ።

“እንግዳ ቢመጣስ ?”

“መጠበቅ ይችላል ።”

የክንፈ እንግዶች የታወቁ ናቸው ። አጠያየቁም ለይስ
ላ ያህል እንጂ ምላሹም ያው የተለመደው እንደሚሆን
ቃል ። ስራ በጀመረ ሰሞን ፣ እንደ ዛሬው ሳያረጋግጥ ፣
ት እንግዳ ተቀብሎ ሽርጉድ በማለት ላይ ሳለ ፣ ክንፈ
እንግዳ ጭሟ አለጊዜ በመምጣቱ በቤቱ ውስጥ ተፈጥሮ
ረውን ፍጅት ሲያስታውስ ይዘገንነዋል ። ባስከተለው
በዚያኑ ምሽት ከስራው የሚሰናበት ነበር የመሰለው ።
ት እንደዚህ ባያውቅም ፣ አጅሬ ክንፈ በራሱ ሰላሙን
ርዶ በማግስቱ ጠዋት ሁለቱን እንግዶች በአንድ ላይ
ኛቸው በቅቷል ።

ክንፈ ከወዳጁ ጋር እንደወጣ ፣ አንሙት የግቢውን
ራቶች አብርቶ ሲንቆራጠጥ አመሽ ። ጭልል ማለቱን
ዶታልና አይጨንቀውም ። እያንጐራጐረ ግቢውን
ር አድሮ ፣ እንቅልፍ የሚጥለው ንጋት ላይ ነው ።

ክንፈ እኩለ ሌሊት ገደማ ተመለሰለት ። እየሮጠ የመጣ
ል ቁና ቁና እየተነፈሰ ከመኪናው ወረደ ። እንግዳ

አልነበረውም ።

“የመጣ ሰው አለ ?”

“የለም ።”

“ግልግል !” ብሎት ተለየው ።

“‘እንቺው ታመጪው ፣ እንቺው ታሮጪው’ አሉ ።
እንዲህ ካስመረረው ለምን አይተወውም !” በሚል ትዝብት
መግቢያው ድረስ በአይኑ ሸኘው ።

ጠዋት ክንፈ ቤቱን ሲከፍትለት ፣ አንሙት ሳሎኑንና
መተላለፊያዎቹን ወልውሎ ካበቃ በኋላ ወደቀጠሮው ቦታ
እንዲሄድ ፈቃድ ጠየቀ ። ለታክሲ አምስት ብር ተከፈለው ።

ወይዘሮ ሰውነቴና ምንታምር በጉዳዩ ተወያይተውበት
ወስነው አድረዋል ። ቡና ተፈልቶለት ፣ ያን ፉት እያሉ
ሲያወጉ ቆያይተው መጨረሻ ላይ ምንታምር ዘማ ፀጉሯን
በኩርሲስ ልጋና የክት ልብሷን አጥልቃ ተዘጋጀች ። የእን
ጨት ሳጥኗን አንሙት ተሸክሞላት ፣ ሦስቱም ተያይዘው
ወጡ ።

የቅጥር ፎርማሊቴው ከአስር ደቂቃ በላይ አልወሰደባቸ
ውም ። ቀለብ ከቤት ሆኖ በአርባ ብር ደሞዝ እንድትጀምር
ተስማምተው ቤቱን አስረክቧት ክንፈ ወዲያው ውልቅ አለ ።
ከዚህ ቀደም እንብዛም ባትጠቀምበትም ምንነቱን ታውቃለ
ችና ምንታምር በመጀመሪያ ሙመገቢያ ክፍሉ ውስጥ ጥግ
ላይ የተገተረውን ተለቅ ያለ ማቀዝቀዣ ከፍታ ተመለከተች ።
የተከፋፈቱ የቆርቆሮ ምግቦች ፣ የተፈጨና የተቆራረጠ ስጋ
ለየብቻ ፣ እንቁላሎች ፣ አትክልታክልት ፣ ... ወዘተ·
ታጭቀውበታል ። አብዛኛውን ስፍራ የያዘው ግን ቢራ ነው ።

ቀጥላም የጐበኘችው ማብሰያ ክፍሉን ሲሆን ፥ ይህም በብዙ መልኩ የተሟላ ነው ። አንዳንዱን እቃ ግን አጠቃቀሙን ቀርቶ አይታውም ስለማታውቅ ልትነካው አልፈለገችም ። ወደ ዋናው መኝታ ክፍል ገባች ። ከአልጋው ስፋት የአንሶላ ዎቹ ንጣት ፥ ከፍራሹ ትንቡኬነት የብርድልብሱና የአልጋ ልብሱ ልስላሴ ትንፋሿን ሰለበው ። በተመሳሳይ ውበት የደመቀ ሌላ አነስተኛ ክፍልም አጋጠማት ። የእንግዳ ክፍል መሆኑ ነው ። መዐዳጃ ቤቱን ፥ በስተጓሮ ዞራም የእርሷን መኝታ ክፍል ፥ የጢስ ቤትና የእቃ ማከማቻ ጓዳ ጐብኝታ ወደ እለቱ ተግባሯ እስክትመለስ አንሙት አልተለያትም ።

ከዚያም እየተረዳዱ የክንፈን መኝታ አንጥፈው እንዳበቁ ምንታምር ምግብ ለማበሳሰል ወደ ማጀቷ ገባች ። አንሙትም መኪና ጋራዥ ውስጥ ወደተዘረጋው የእንጨት አልጋዋ ሄዶ ተጋደመ ። ጥሩ እንቅልፍ ወሰደው ።

ክንፈ ያለወትሮው ገና ለአይን ያዝ ሲያደርግ ቱሚለሰ ። ተከታዩ ቀን ሰኞ እንደመሆኑ እርሱም ጥሩ እንቅልፍ ሳይናፍቀው አልቀረም ። ምንታምር ከመኝታ ክፍሏ ስትሮጥ መጥታ እስከሚጠራት ድረስ ማብሰያው ክፍል ተቀመጠች ። ክንፈ በቀጥታ ወደመኝታ ክፍሉ ገብቶ ፒጃማውን ካጠለቀ በኋላ ቢራውን በብርጭቆ ሞልቶ ፉት እያለ ምንታምር ወዳለችበት ክፍል ዘው አለ ።

"ራት ላቅርብ ?" አለችው ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ።

"ምን አለሽ ?" ሲል ጠየቃት ።

"እንቮራ ስለሌለ ፥ የአትክልት ሾርባና ስጋ ጥብስ አዘጋጅቼያለሁ ።"

"አ!" አለ ክንፈ በድንጋጤ ቅላፄ ። እንዲህ የሾረች አልመሰለውም ።

"ከዚህ በፊት ሰው ቤት ሰርተሻል ?"

"አዎ ፥ ባህርዳር ፈረንጆች ቤት ሰርቻለሁ ። ሰርተፊከም አለኝ ።"

"በወጥቤትነት ?"

"የተቀጠርኩት እንኳ በሞግዚትነት ነበር ። ሴትየዋ ምግብ አሰራር አስተማረችኝ ።"

"ለምን ወጣሽ ?"

"ፈረንጆቹ ወደ ሀገራቸው ሄዱ ።"

"ሌላ ቦታ ፥ እበሾች ቤትስ አልሰራሽም ?"

"እዚያም ሳለሁ ፥ አዲስ አበባም ከመጣሁ በኋላ ሞክሬ ነበር ። ..." ብላ ሀሳቧን አንጠልጥላ አስቀረችበት ።

"እናስ ?"

"የማይሆን ሆኖብኝ ተውኩት ።"

"እንዴት ?"

ምን እንደምትለው ግራ እንደተጋባች ሁሉ ፈዝዛ ቀረች። ክንፈም መልሷን መስማት ስለፈለገ ጠረጴዛ ተደግፎ ቆመ ። አውጥታ አውርዳ "የሳው አመሉ ብዙ ነው ። አንዳንዱ ወጪውን ቆጥቦ ብዙ ነገር ያምረዋል ። አንዳንዱ ደግሞ በትንሽ በትልቁ ጭቅጭቅ ያበዛል ። አጠራቅሙልኝ ያልኳቸው ይመስል ደሞዜን በሰአቱ አልከፍል እያሉኝ ያስቸገሩኝም አሉ" በማለት ማብራሪያዋን ካቀረበችለት በኋላ ጣቶቿን እያፍተለተለች ወለሉ ላይ አይኖቿን ተክላ "እርግፍ

አድርጌ ትቼው እቴቴ ዘንድ ተቀመጥሁ" ስትል ደመደመች።

"የጠዋቷ ሴትዮ ባለመጠጥ ቤቷ ?"

"አዎ ፣ የጡት እናቴ ናት ።"

"ደህና ፤ እኔ ቤት ያ ሁሉ ችግር የለም ። ለመሆኑ ራት በምንድን ነው ያበሰልሽው ?"

"በፈርኔሎ ።"

"በጋዝ ምድጃ አብስለሽ አታውቂም ?"

"እ?" ድንግር ብሏት ። "በነጭ ጋዝ ነው የምትሉት?"

"ያ ሳይሆን በቡታ ጋዝ ።"

"በዚህ ?" አለችው አጠገቧ ወዳለው ምድጃ በጣቷ እየጠቆመችው ።

"አዎ ።"

"ፈረንጆቹ ቤት የዚህ አይነት ነገር አይቻለሁ ። ግን ሁሌም የምትለኩሰው ሴትዬዋ ነበረች ።"

"ቁሩ ፤ አጠቃቀሙን ነገ አሳይሻለሁ ።"

"እሺ" በማለት እጅ ነሳች ።

"ከእንጀራ ምጣድ በተጨማሪ ሌሎች በኤሌክትሪክ የሚሰሩ እቃዎችም አሉ ። የእነዚያን ሁሉ አሰራር አሳይሻለሁ በቅርቡ ራስሽን ትችያለሽ ። ዋናው ነገር ቅንነት ነው ። ካወቅሽበት ቤቴ ቤትሽ ይሆናል ። አሁን ራት አቅርቢልኝ" ብሏት ወደሳሎን ተመለሰ ።

እንጀራ ከማስፋትና የዶሮ ብልት ከማውጣት በቀር ፣ ክንፈ በባልትና ከማንም ሴት አላንስም ባይ ነው ። ምንታምር ስልጡን ሆነችለት ። ሽርጧን ሽብ አድርጋ ሰሀኖቿን ፣ ሹካና ማንኪያዎቿን ፣ ከዚያም ሾርባውን በስሱ ከተቆራረጠ ዳቦ

ጋር ፣ አስከተላም ጥብሱን አቀረበችለት ። ክንፈ እያጣጣመ አስገባላት ።

"ሌላስ?" አላት ፣ በልቶ እንደጨረሰ እቃውን እንድታነሳ በጭብጨባ ጠርቷት ።

"ሌላስ የለም!" አለችው እንደማፈር ብሏት በአንድ እጇ አፍን ግጥም አድርጋ ይዛ ።

"ሞልቶ! አሁን አላስፈለገኝም እንጂ ፣ ሌላ ጊዜ ከፍራፍሬ ወይነት ታስመርጭኛለሽ ። ሻይ ወይም ቡና ሊያስኘኝ ይችላል ።"

"እሺ" አለች አንገቷን እንደሰበረች ።

"ለአንሙት ራቱን ስጭው ። አንቺም በልተሽ በጊዜ ወደመኝታሽ!"

"እቃዬን አጣጥቤ ነው!" ስትል ቀልጠፍ ብላ መለሰች ለት ፣ ሊታዘባት እንዳይሆን ሰግታ ።

"አሃ! ለካስ ያም አለ!"

ተከታዮቹ ጥቂት ወራት ለአንሙትና ለምንታምር የተድላና የፍስሀ ጊዜያት ነበሩ ። በአንድ ጣራ ስር አንድ አልጋ በመጋራት ባለትዳርነታቸውን ይፋ አያድርጉት እንጂ ተጋብተዋል ማለት ይቻላል ። የክንፈ መኝታ ከፍል የዘወትር መዝናኛቸው ነበር ። በእንግዳ መኝታውም ከፍል እንግዳ ሆነው ጋደም የሚሉበት ጊዜ አለ ። የእርሷም ሆነ የእርሱ መኝታ አይቆረቁራቸውም ።

አንሙትና ምንታምር በአፍላ 'ትዳር' እፍ ባሉ በአራተኛው ወር ፣ አንሙት በጊዜያዊ ሰራተኛነት ክንፈ መስሪያ ቤት አንገቱን አስገብቶ ሳያውቀው ቋሚ ሆነ ። ከክንፈ

ጥገኝነት ግን አልተላቀቀም ። ለመላቀቅም አልፈለገም ። ያለ ደሞዝ የዘበኝነት ስራውን ቀጠለ ። ከመደበኛ ስራው መልስና በእረፍት ቀናቱ የግቢውን አትክልት መንከባከቡን አላቋረጠም ። ክንፈም ግልጋሎቱን ወዶለታል ።

ምንታምር አረገረገች ። ደምግባቷ ከእለት ወደ እለት እየፈላቀ ሄዶ ሲያቅፍት የምትሚሚ ልዩ ፍጡር መሰለች ። በአለባበሷና በፀጉር አሠራሯ ከከተሜዎቹ የማትተናነስ ሆነች ። በስነምግባሯ ልዝብነት የተጠጓትን ሁሉ መግዛት መቻሏ ሌላው መስህቧ ነው ። ክንፈን ከአንቱታ አላወረደች ውም ። ለአንሙት ያላት ፍቅርም የሚቀዘቅዝ አልሆነም ። ባጭሩ የምታሳሳ የቤቱ አዋይ ለመሆን በቃች ።

ታዲያ ጉዷን በጉያዋ ደብቃ እንጂ ልትፈታው ያልቻለችው እንቆቅልሽም ሳይገጥማት አልቀረም ። ወገቧን ብትጠመጥምና የቀሚሶቿን ሽንሽን እየተረተረች ሆዷን ከተት ለማድረግ ብትሞክርም እርግዝናዋ እያፈጠጠ መጣ ። ክንፈም አንሙትም ጠያቂዎቿ ነበሩ ። ከሁለቱም ጋር ስትንጐዳ ጉድ እንደመቆየቷ ፣ ከማንኛቸው እንደፀነሰች አታውቅምና ራሷው መስካሪም ዳኛም ሆና በረከቷን ለሁለቱም አደለቻቸው ።

ክንፈ የአባትነቱን ምስራች በሰማ ሰሞን ሊያሰናብታት አስቦ ነበር ። አይጣል እንዲሉ ፣ የምንታምር ፍቅር ፍርጃ ሆነበት ። በዚያ ላይ ስሙን የሚያስጠራለት ፍሬ የማግኘቱን እጣ ፣ በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ እንደ ታላቅ ፀጋ ቆጠረው። ስለዚህ በሚስትነት ባይፈልጋትም ፣ ማርያም አለሁሽ ትበላትና ፣ ቀኗ ሲደርስ ወደ ጡት እናቷ ልኳት ከዚያ

እንድትገላገል ፣ ለማሳደጊያ ብቂ ገንዘብ እንደሚደጉማትና ሁለቱንም እንደሚንከባከባቸው ቃል ገብቶላታል ። እርሷም ተስማምታለች ።

በአንድ ጉኑ ጉዳዩ በዚያ ያከተመ ቢመስልም ፣ በሌላ ጉኑ ችግር አቄጥቁጧል ። ክንፈ ውሳኔውን የገለጸላት በጣም ዘግይቶ ነበር ። እያመነታታ ልቧን ሲያዋልልባት በመክረሙ ፣ ምንታምር መጣያ እንዳታጣ በመስጋት ፍሬዋን ለአንሙትም አበርክታለች ። 'የምስራች!' ስትሉው እርሱም 'ምስር ብይ!' ብሏት ያጠራቀማትን ጥሪቱን አሟጢ ልብስና ጫማ ገዝቶላታል ። ዘዚህ ላይ ክንፈ ምንታምርን አለማባረሩ እርግዝናዋ የማይመለከተው ቢሆን ነው ብሎ ገምቷል ።

እግዜር ሁን ያለው አይቀርምና አንድ ቀን ጉድ ፈላ ። እለቱ እሁድ ነው ። ማለዳ ላይ አንሙት ክንፈ ዘንድ ቀርቦ እየተቅለሰለሰ "የማማክርዎ ጉዳይ ነበረኝ" አለው ።

"ምንድን ነው?"

"ላደረጉልኝ ድጋፍ እግዜር አጠፌታውን ይክፈልዎ እንጂ ...መቼስ...እኔማ ምን ላደርግልዎ እችላለሁ?! እድሜዎን ያርዝምልኝ! የልብዎን ይፈጽምልኝ!.." በማለት ምስጋናውን ደርድሮ ለማለት የፈለገው አልወጣልህ ያለው ይመስል በዝምታ ተቁለጨለጨ ።

"ምን እንዳደርግልህ ፈለግህ?"

"ጓዳ ብጤ ተከራይቼ ልወጣ አስቤያለሁ ።"

ክንፈ ደንገጥ አለ ። ያልጠበቀው ሀሳብ ስለነበር በቀላሉ የሚዋጥለት አልሆነምና "ምነው? ምን ችግር ገጠመህ?" አለው ።

"እረ ምንም ችግር አልገጠመኝም?"

"ታዲያስ?"

"እንዳው" አለ ሲፈራ ሲቸር ፤ "ሰው ከማስቸገር ራሴን ልቻል ብዬ ነው ።"

"ችገረኝ አልኩህ ?" አነጋገሩ የቁጣ ነበር ።

"አዬ ጌታዬ ! ጣጣው መች ከርሶ ሆነና!"

"ምን ታዲያ እዚያና እዚህ ትላለህ! መሄድ ከፈለግህ መንገዱ ያውልህ!" በማለት ወደ በሩ ጠቆመው ።

"እረ እንዲያም አይደል ።"

"አፋ! ውጣልኝ !" ሲል ክንፈ ጮኸበት ።

አንሙት ቆሌው ተገፍፎ ሹልክ ብሎ ወጣ ። ከክንፈ ጋር ሳይተያይ ውሎ አደረ ። ምንታምር በፈቃድ ወይዘሮ ሰውነቴ ዘንድ ውላ የተመለሰችው ማምሻ ላይ ነበር ። ከእርሷ ጋር እንደወትሮው ለመገናኘት አልቻለም ። ሀሳቡንም ቀደም ብሎ ፣ ካንዴም ሁለቴ ፣ አንስቶላት ስለነበር ባለመቃወሟ ተስማምታበታለች ብሎ አስቧል ።

ከክንፈ ጋር የተገናኙት ፣ በማግስቱ ሰኞ ክንፈ ቢሮ ውስጥ ነበር ።

"አቋምህን ባጭሩ ግልጽ አድርገህ ንገረኝ ። በትናንቱ ውሳኔህ እንደፀናህ ነህ?" አለው ክንፈ በቀጥታ ።

"አዎ ፣ አማራጭ የለኝም ።"

"ለመሆኑ ምን ችግር ገጠመኝ ልትል ነው?" በማለት ቱግ አለበት ። "እንደ ልብህ ትበላለህ ። የምትለብሰው አላጣህም ። ደሞዝህን እያጠራቀምህ ሰው ለመሆን ጥረት በማድረግ ፋንታ ቁልቁል ትመለሳለህ! አሁን በዚች ደሞዝ ራስህን ትችላለህ?"

"ቆሎ ቆርጥሜም..." በማለት አንሙት የጀመረውን ሀሳብ ክንፈ አላስጨረሰውም ።

"ውጣ!"

"አያመናጭቁኝ እንጂ ጌታዬ ! ችግሬን አላወቁልኝም'ኮ!"

"ውጣልኝኮ ነው የምልህ! እንዲህ ያደረገህ ጥጋብ መሆኑን መች አጣሁትና!"

"አይደለም!"

"ታዲያስ? ምን ሊባል ነው?"

"ልጅቷ" አለ ራሱን እንደደፋ "መውለጃዋ ስለደረሰ ሸክም እንዳንሆንብዎ ብዬ ነው ።"

"የቷ?" ሲል ጠየቀው ። አዝማሚያው ሳይገባው አልቀሪም ።

"ምንታምር ።"

"ምን!"

አንሙት መልስ አልነበረውም ። እንዳቀረቀረ በዝምታ ጠበቀው ። "ባለጌ! ልክስክስ!"

አንሙት ደሙ ፈላ ። ክንፈን ያስቆጣው ምን እንደሆነ ሊገባው አልቻለም ።

"ውጣ!" ሲል አምባርቆበት "ምናምንቴ!" የሚል ሰድብ ክንፈ አከለለት ።

"በህግ አምላክ !" አለው አንሙት ቀና ብሎ እያየው ።

"ግቢዬን ዛሬውኑ ለቀህ ውጣልኝ ። ከዚያም በኋላ እዚህ መስሪያ ቤት እንዳላይህ ። ማንነትህን የማታውቅ..."

"እንዴ!" አለ አንሙት በቁጣ ስሜት እየተንቀለቀለ ።

"እንዴተ ማንነቴን አላውቅም ? ሰው ነኝ እኮ ፥ የሰው ልጅ!"

"ሂድ!" አለው ክንፈ በመጠየፍ ። "አንተም ከሰው ተቆጥረህ?! ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው? እስቲ ንገረኝ!"

አንሙት ንዴቱን መቆጣጠር አቃተው ። "አንተስ ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው?" በማለት በተራው ዘረጠጠው ።

የክንፈ ዓይኖች ተጐለጐሉ ። "ለስድብም ደረስክ?" ሲል ከተቀመጠበት እመር ብሎ ተነሳና እጆቹን ጨብጦ ወደ አንሙት ተንደረደረ ። አንሙትም ጡንቻውን አፈርጥሞ ቆየው ፤ ግብግብ ገጠሙ ፤ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት አንሙት ሀይሉን አሳየው ። ክንፈ ወደቀ ።

አንሙት ያለገላጋይ ቢሮውን ለቆለት "ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው ይበለኝ! እንደሰው ሰው ነኛ ! ሰው!" እያለ በደረጃው ቁልቁል ተንደረደረ ። ከቅጥር ግቢውም ወጥቶ ነጐደ ።

መንገዱን እንዴት እንዳገባደደው ሳይታወቀው ከክንፈ ቤት ደረሰ ።

ገና ከመግባቱ "ምንታምር!... ምንታምር!..." ሲል ተጣራ።

"ምነው ምን ሆነሃል?" እያለች ምንታምር ብቅ አለች ። አባረውት መደበቂያ የሚፈልግ ይመስል ሲርበደበድ አይታው ደነገጠች ።

"ይኸ ሴት አውል ሰደበኛ!" ብሏት ወደ ማደሪያው ሮጠ ። ምንታምር ተከተለችው ። "ማንነቱን የማያውቅ ፥ ምናምንቴ ይበለን?! እኔ አንሙት ቀን ጥሎኝ እንጂ..." እያለ ጨርቃጨርቁን በከረጢት ማመቅ ጀመረ ።

ጥሉ ከክንፈ ጋር እንደሆነ ምንታምር ገባት ። ግን የምትለው ጠፋት ። በድን ሆነች ። " 'ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው' አለኛ ! እኔም በአገሬ ሰው ነበርኩ" አለና የቀረቀበውን ትከሻው ላይ አድርጐ ተመለከታት ።

"ምን አጣላችሁ ?" ድንገት የመጣላት ጥያቄ ነበር ።

"ነፍሰጡር እንደሆንሽ ያውቃል ። ሽክም እንዳንሆን በት ቤትህን እንልቀቅልህ ማለት ይህን ያህል ያስደነፋል?" ሲላት ምንታምር ሰማይና ምድሩ ዞረባት ። ጉልበቷ ሲከዳት ታወቃት ። ተዝለፍልፋ መሬቱ ላይ ዘርፈጥ አለች ።

"እኔ በቃኝ ። ከመሰለሽ መሰንበት ትችያለሽ ። አሊያም ወይዘሮ ሰውነቴ ዘንድ ሂጂ ። የወደፊቱን እግዜር የውቅልናል። ለፍሬ ብሎናልና ። እርሱው እንደሚያደርገን እንሆና ለን" ብሏት ውልቅ ሲል የጥላቸው መንስኤ እሷው እንደሆነች ምንታምር ተረዳች ።

ቃል ሳይወጣት በዝምታ ሸኘችው ። የህይወት ጐዳናዋ እየጨለመ ሲሄድ ታያት ። በሆዷ የያዘችው ፍጡር ውኃ ሆኖ ቢቀርላት ደስ ባላት ። የምታደርገው ጠፍቷት በጭንቀት ቁጭ ብድግ እያለች በሀሳብ ስትዋልል ክንፈ ከተፍ አለባት ።

የውጪውን በር ስትከፍትለት ፥ በመኪናው ሊገፈትራት ምንም ያህል አልቀረውም ። እንደወጣ በሩን ደርግሞ የተንደረደረው ወደ አንሙት መኝታ ቦታ ነበር ። እንደሄደ ተረዳ ።

"አንቺም ቅራቅርቦሽን አዝለሽ አሁኑኑ ውጪልኝ !

ምናምንቱ ሁላ!” ብሏት እየተጐናደረ ወደ ቤት ገባ ።

ምንታምር እቃዋን ሸክፋ ግቢውን ለመልቀቅ እኩል ለአተ አልፈጀባትም ። ሳትሰናበተው መሰስ ብላ ወጣች ።

* * *

ይህ ሁናቴ በተፈጠረ በሦስተኛው ቀን ነበር አንሙት ወደ መሥሪያ ቤቱ ብቅ ያለው ። እንደማይሰነብትበት አውቋል ። በቀጥታ የሄደው ወደ ፐርሴኔሉ ቢሮ ነበር ። ከዚያም ወደ ክንፈ ክፍል ብቅ ብሏል ። በመጨረሻም መዝገብ ቤት ።

‘ወፈፈው’ በለገሀር አካባቢ እየተዘዋወረ እስከዛሬ “ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው?” የሚል ፈሊጡን ያነበንባል ። ረሀብ በከረከረው ወገቡ ዙሪያ ትልታይ ጨርቆችን አጥ ብቆ ተብትቦ ሽቅብና ቁልቁል ሲጣደፍ ይውላል ። አንዳንዴም ይለምናል ። ግን ድርቅ አይልም ። ጠጋ ብሎ ሁለት እጃቹን አጋጥሞ ይዘረጋና አቀርቅሮ ምድር ያያል ። ከጣሉለት ጐንበስ ቀና እያለ ምስጋናውን ይገልጻል ። ካላገኘም እንዳቀረቀረ ወደ ሌላው ይሸጋገራል ። “እግዜር ይስጥህ!” የሚሉት ላይ ግን ያፈጥና አስደንጋጭ ሳቁን ለቅቆባቸው ‘ማነህ ቢሉህ’ ማነኝ ልትል ነው?” በማለት ያፋጥጣቸዋል ።

ጥብቅ መመሪያ

ረኽም ምንሽሩን በሆዱ አቅፎ ያደፈጠው ‘ጥበቃ—ጓድ’ ላቀው ከርቀት በሚያየው አጥር ላይ አይኖቹን ተክሏል ። በግራ እጁ ዳጎስ ያለ የካርኒ ጥራዝ ይዟል ። ከቀኝ ጀሮው መጋጠሚያ የገነፈለ ቢክ እስክሪፕቶ ብቅ ብሏል ።

ግስላ ሲጋራውን እየሳበ ፡ ካቲካላ ያቦዛቸው አይኖቹን አጥሩ ላይ ሰክቷል ።

ፀሃይ አዘቅዝቃለች ። ገበያተኛው ወደየቤቱ ይትማል ። አንዳንዱ ዕቃውን በኩሊ አሸክሞ ፡ የተረፈውን አንጠልጥሎ በድካም ተውጦ ያዘግማል ። ቅራቅንቦአቸውን አዝለው ፡ አሮጌ ጀንጥላቸውን ዘርግተው የሚያዘግሙ አርሶ ቶችም ይታያሉ ። ...

ከንጋት ጀምሮ ምንም ያልቀናው ‘ጦበቃ—ጓድ’ በመሰ ላቸት እያፋሸገ አጥሩን አጥብቆ ይመለከታል ። የካቲካላ ሱስ እያቁነጠነጠው ‘ዲስኮ’ ሰዓቱን ተመለከተ ፤ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ትላለች ።

‘ጥበቃ—ጓዱ’ ባተኮረበት አጥር ላይ ፡ ምንም እንኳ ቂለሙ ደብዝዞ ምን እንደሚል በውል ባይለይም ፡ ‘በዚህ አካባቢ መሽናት ክልክል ነው !’ የሚል ጽሁፍ እንደሰፈረ በት ግምት የሚጭር አንድ የቆረፈደ ካርቶን ተንጠልጥሏል ። በዚያ አካባቢ ሲሸና የተገኘ እንዲቀጣ ለማድረግ የቀበሌው ጽህፈት ቤት አንድ ‘ጥበቃ—ጓድ’ መድቧል ። ይኸው የተመደበው ‘ጥበቃ—ጓድ’ ፡ ላቀው ፡ ደግሞ ስራውን

በጅመረ ማግስት 'እዚህ መሽናት ከፈለጉ አምስት ብር መያዝዎን ያረጋግጡ !' የሚል ጽሁፍ ከደቃቅ ከሰል በተሰራ ቀለም ትንሽ ካርቶን ላይ አፅፎ ሰቅሏል ።

ላቀው አሁንም አጥሩ ላይ እንዳፈጠጠ ነው ። ተኩሶ የሚጥለው ጠላት ያጋጠመው ይመስል ከተቀመጠበት በድን ገት እመር ብሎ አጠገቡ ከሚገኝ ምሽግ ውስጥ ገባ ።

ረዥም ምንሽሩን አነጣጥሮ "ቁም ! እንዳትነቃነቅ !" አለ ፥ የተጨፈነ አንድ አይኑን ወደ ማነጣጠሪያ አስጠግቶ ።

ከምሽጉ ወጥቶ እየሮጠ አጥሩ ላይ ሲሸና ወደነበረው ሰው ተጠጋ ።

"አምስት ብር ! ... አምስት ብር !" እያለ ካርኒው ላይ ብዕሩን አሾለ ።

"የምን አምስት ብር ?" ሰውየው መሽናቱን አላቆመም።

"መሽናት ያስቀጣል ! ጥብቅ መመሪያ ነው !" አለው የካርኒውን ጥራዝ ገልብጦ በእስክሪፒቶው ፀጉሩን እያከከ ።

"ታዲያ እኛን ነው የምትቀጣው ?" አለና ሰውየው ሳቀበት ።

"ምን ትቀልዳለህ ! በህግ ! ..."

"ንቃትህ ጥሩ ነው ። እኔ የዜሮ አንድ ሊቀመንበር የጓድ ሺመክት ዋሲሁን ታላቅ ወንድም ነኝ ። ዜሮ ሶስቶች በእርግጥ ጠንክራችኋል ማለት ነው ። የኛ ቀበሌ ጥበቃዎች እንኳ ፈዛዞች ናቸው ። ሃ ... ሃ ... ሃ ... !" አለና ሰውየው እጁን ለሰላምታ ዘረጋለት ፥ ሽንቶ እንዳበቃ ።

"ምን እናድርግ ! አብዮቱ ጤናችሁን ጠብቁ ብሎ የለ ? ጤና መጠበቅ መመሪያ ነው" አለና ላቀው የተዘረጋለትን እጅ ጨበጠ ። ...

ሰውየውን ለመቅጣት ባለመቻሉ እየተናደደ ቀድሞ ወደነበረበት ቦታ አዘገመ ።

እለቱ ቅዳሜ ነበር ። ሁልጊዜ ቅዳሜ እንኳ ደህና ገቢ ነበረው ። በተለይም በአላማጣ ከተማ አካባቢ የሚገኙ ገበሬዎች ከገበያ መልስ ጠላ—ጠጅ ጠጥተው ወደየመንደራቸው ሲሄዱ አጥሩ ላይ የሚሸኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው ። ሲሸኑ አድፍጦ የሚጠባበቀው ላቀው በዛቻና ማልመጫ አምስት ... አምስት ብር ያስከፍላቸዋል ።

አብዛኞቹ ማስረጃ ወይም ደረሰኝ አይጠይቁም ፥ ለተቀጡበት ። የሚጠይቁ ካሉ ይሰጣቸዋል ። የኮርኒውን ጥራዝ ፥ ይሰረቀው ወይ ወድቆ ያግኘው እንጃ ፥ ከአንድ እስክሪፒቶ ጋር ያስታቀፈው የዜሮ ሶስቱ ቀበሌ ሊቀመንበር 'ጓድ' ፀደቀ ነበር ። ካርኒው የታተመውም በ1952 ዓ.ም. ሲሆን በዚያን ወቅት ቤተክህነት ከምዕመናን መቀጮ የምትሰበስብበት ነበር ።

ላቀው ማይም ነው ። ስሙን እንኳ መፃፍ አይችልም ።

በዚህ ላይ መሠረተ ትምህርት በሚሰጥበት አካባቢ መድረስ አይወድም ። የሚያነሳበትም ጠላቱ ነው ። ያንገራገሩበት ወጣቶች ጥፊውንና አርግጫውን ፈርተው ትተውታል ። ስለዚህ ሊቀመንበሩ ራሱ በእያንዳንዱ ካርኒ አናት ላይ ታትሞ የነበረውን የቤተ ክህነት አርማ በጥንቃቄ ቆርጦ በምትኩ 'ጥብቅ መመሪያ' የሚል ፅሁፍ አስናሮበ

ታል ። የከፋይ ስም በሚሞላበት ባዶ ስፍራ ላይ ደግሞ 'መሽናት ክልክል ነው ። የሸና ይቀጣል' ሲል ገጥጦበ ታል ። የመቀጫው መጠንም በአሀዝና በፊደል ተሞል ቷል ። ግን የቀበሌው ቁጥርም ሆነ ማህተም አይታይበትም ። እና የላቀው ስራ ለከፋይ ካርኒውን ከጥራዙ እየገነጠለ መስጠት ብቻ ሲሆን ብእሩን የሚያሾለው ለስሙ ነው ። ሁሉም በቅድሚያ ተዘጋጅቶ ቀርቦለታል ።

በቅጣት መልክ የሰበሰበውንም ገንዘብ ከአለቃው ጋር ይከፋፈላል ። ሁልጊዜ ቅዳሜ ቢያንስ ቢያንስ አስር ··· አስራ አምስት ብር አያጣም ነበር ። ዛሬን ግን አልቀናውም ።

እንደምንም ብሎ አምስት ብር እንኳ ማግኘት ነበረ በት ። የሰሞኑ የቤቱ ጭቅጭቅ ታየው ። ···

"አሁን ትዳር ተብሎ ነው ?" ብላዋለች ሚስቱ ፣ ለተከታታይ ቀናት ፣ ሲገባና ሲወጣ ፣ ንትርክ አምሯት ምላሷን አሹላበታለች ።

"ምናለ ብትተይኝ ? እኔ ብር ልሁን ታዲያ ?"

"እኔስ ምን ልሁን ? አሁንማ ነብስ አባታችንም ተቆጡ ። በቀደም ቤተ ስኪያን ልሳለም ብሄድ ያሉኝን አልረሳውም ። እንዲህ እየተሳቀቅኩ ፣ የጐረቤት መሳቂያ ልሁን ? ወይእዳ ! ··· አየ እድል !" እየነፈረቀች ።

ነፍስ አባታቸው ቂስ መሀሪ አኩርፈዋቸዋል ። ባልና ሚስቱ ዝክር ብጤ የማያወጡ በመሆናቸውና ለአጥቢያቸው ታቦት ወርሃዊ—ክፍያ ባለማስገባታቸው በተደጋገሚ ወቅሰ ዋታል ። ለነገ እሁድ አንድ ብር ከሃምሳ ይዛ አንድትመጣ ፣ ባታመጣ ግን ሌላ ነፍስ አባት እንዲፈልጉ አምረው ስለነገ

ሯት ተጨንቃለች ።

"ታዲያ ብር ከየት ይገኝ ? ዛሬ ማን ያበድራል ?"

"እንደምንም ብለሽ ፈልጊ ብለውኛል !"

"ድሆች መሆናችንን ዘንግተውት ነው ? ቀበሌውን እያገለገለ ነው አትያቸውም ? ካስፈለገ የትብብር ደብዳቤ ላጥፍ"

"የምን ትብብር ? ቤተስኪያን ውስጥ ቀበሌ ምን አገባው ? ደሞስ 'የነጣ ደብዳቤ ይዛ ሂደች !' ተብየ ጉረቤት ይሳቅብኝ !? 'ባለቤትሽ ቤተ ስኪያን አይሳለሙም ። ሰንበቴ አይጠማም ···' እየተባልኩ መሳቂያ መሳለቂያ መሆኔ አንሶኝ ። ···"

"ባንከፍል ምን ሊያደርጉን ነው ?" አላት ረኽም ምንሽሩን ቅባት በጠጣ ቁራጭ ጨርቅ እየወለዉለ ።

"ባንከፍልማ ስንሞት ማን ይፈታናል ? መቀበሪያ ቦታስ ማን ይሰጠናል ? እንደምንም ብለህ ብር ካምሳ ፈልግ ! አለዚያ ዋ !"

"እስቲ ደግሞ እሞክራለሁ ።"

"አስብበት ! ኋላ ይኸ ነገር እያዋጣንም !"

"ምን ዋጋ አለው ? መሰረተ ትምህርት የሚሉት ጣጣ ከመጀመሩ በፊት ቅጣት ይገኝ ነበር ! ዛሬ ዛሬ ግን ሰው እያነበበ ነው መሰለኝ መሽናት አቁሟል ።"

"እኔ ነግሬያለሁ ! ···"

"በቃ ··· ዝም በይኝ !"

ሚስቱ ከምትጠብቅበት ብር ከሃምሳ ሌላ ካቲካላ የሚቀምስበት ገንዘብ ያስፈልገዋል ። ሳይጠጣ ውሎ ግደር

አይችልም ። እናም አጥሩ ላይ ሽንቶ የሚቀጣ ሰው ለማግኘት ተስፋ አድርጎ ነበር ወደ ምሽጉ ያመራው ። እግረመንገዱንም ሁለት መለኪያ ካቲካላ የዱቤ ጠጥቷል ፣ በቁሙ ። ቢሆንለት በየቀኑ ካቴውን ፉት እያለና ባለ መረዋ ድምጿ አርሞ ድርብ ለገሰን እያደመጠ ፣ ከጓደኞቹ ጋር ሲያውካካ ቢውል— ቢያመሽ በወደደ ። አንዳንዴም ሞቀ ሲለው ግጥም እያቀበላት ፣ ጠጪዎችን እያስደሰተ ።

“አሥር ሣንቲም ያለው — አያዘረዝርም
ውጊያ የቀመሰ — ጡር አይናገርም ።
አይነ መልከ መልካም — ጋሜነው ስሬቷ
የራያ መጋላ — መቃ ነው አንገቷ

በነላቀው ክልል — ዜሮ ሶስት ነው ቤቷ ... ” እያለ አንድ ቀን ሲገጥምላት ፣ ጠጪው ጭብጨባውን አጋግሎለት በኩራት ተከፍሶ ዙሪያውን መገላመጡ ፣ በሁለት ውጊያዎች ተካፍሎ ከሌሎቹ ‘ጥበቃ—ጓዶች’ ብልጫውን እንዳስመሰከረ መናገሩ ፣ ‘ትከሻየ ላይ ቆስያለሁ’ ብሎ በሞቅታ ግፊት ፣ አሮጌ ካኪ ሸሚዙን ገልብጦ የሆነ ጠባሳ ለጠጪዎቹ ማሳየቱ ከበሬታን አትርፎለት በተደጋገሚ ያንኑ ካቲካላ እንደተጋበዘ ሲያስታውስ የልቡ ትርታ ይጨምራል ። ...

በሀሳቡ ያን የደስታ እለት እያወጣ—እያወረደ በርቀት ያለውን አጥር ሲመለከት ብርድ ልብስ የተከናነበ ሰው አጥሩ ላይ ሲሸና አጋጠመው ።

ረዥም ምንሽሩን አቀባብሎ እያነጣጠረ “ቁም ! ... እንዳትነቃነቅ !” አለና በጐርናና ድምፁ አምባረቀ ።

አጥሩ ላይ ሲሸና የነበረው ሰው ወዲያውኑ አቋርጦ ፣

የቁምጣ ሱሪውን ቁልፎች ቆላልፎ መሬት የነካ ብርድልብሱን ሰብስቦ ወደ ተቀባበለው መሳሪያ ፊቱን መለሰ ።

“አትሽኑ ማለት ምን ማለት ነው ? አምስት ብር ተቀጥተሃል ! ብዙ የምታውቅ አይደለህም እንዴ ? በል ክፈል !” አለና ላቀው በንነፈለ እስክሪፒቶው ካርኒውን መወጋጋት ጀመረ ። ማማሰያ አንጂ ብእር የጨበጠ አይመስልም ።

“ምን አድርጌ ?” አለ ሰውየው ቆሌው ተገፎ ።

“የጤና ጠንቅ ሆነሃል ! እዚህ ለምን ሸናህ ? ጥሁፉን አንብብ ! ጥብቅ መመሪያ ነው” አለና አጥሩ ላይ ወደተንጠለጠለው የቆረፈደ ካርቶን አመለከተው ።

“እኔ ማንበብ የት እችልና ?”

“አሃ !” አለ ላቀው ዓይኖቹን በልጦ ፣ “ያም ተጨማሪ ቅጣት አለብሃ ! ለምን አትማርም ? ‘የማያነቡ ዓይኖች ቦታ የላቸውም ... አይኖሩም’ ሲባል አልሰማህም ? የአብዮቱ ሬዲዮ ነው እንዲህ ያለው ። ...ለዚህ ጥፋትህ ከሚደርስብህ ቅጣት እግዜር ያውጣህ ! አሁን ለሸናኸው ክፈል !” አለና ረዥም ምንሽሩን ከግራው ወደ ቀኝ እጁ አዞረ ። በተለያዩ ቁርጥራጭ ጨርቆች ከተጣጣፈው ፊልድ ጃኬቱ ኪስ ከፊያውን አውጥቶ በራ ራሱ ላይ ደፋ ።

“ምህረት አድርግልኝ ! አይኔ በሽተኛ መሆኑን ታውቃለህ ። ... ” አለ ሰውየው በማስተዛዘን ።

“ስለ አይንህ የሚያገባኝ ነገር የለም ። በአይንህ አልሸናህ ! ባለመማርህ ከሚመጣብህ ጣጣ አግዜር ያውጣህ ብየሃለሁ ። አሁን ለሸናህበት ክፈል ! ጥብቅ መመሪያ ነው !

...” ካለው በኋላ ኮፊያውን አስተካክሎ ፡ ረዥም ምንሽሩን እንደገና ወደ ግራ እጁ አዞረ ፡ ዓይናቹን እያጉረጠረጠበት ።

“ከየት ላምጣ ? የሚሸጥ የሚለወጥ የሌለኝ ድሃ ነኝ ። ተው አንተ ላቀው ! ወንድምህ ፡ ጐረቤትህ አይደለሁም ? በኔ ትጨክን !’ አለና ሰውየው ተለማመጠው ። ተማፀነው ። ሚስጥር ኪሱ ውስጥ አጣጥፎ የሸጎጣትን አምስት ብር አውጥቶ ለችግር ከመዳረጉ በፊት ልመናውን ተያያዘው ። በዚች አምስት ብር ለአንዲት ልጁ ካኪ ጥብቆ ሊገዛ አቅዶ ነበር ።

“መመሪያ መመሪያ ነው ! በአብዮት ጊዜ ጐረቤት ፡ ጀኒ ቁልቋል የሚባል ነገር የለም ! አሁን አምስት ብር ትከፍላለህ ክፈል ! ካለዚያ ቀበሌ ትሄዳለህ ! ካድሬው ራሱ በአጠፌታ ያስከፍልሃል ፡ ያውም ከውርደት ጋር ! ካድሬ የሚላችሁን ተቀበሉ ብሏል አብዮቱ ...ጥብቅ መመሪያ ነው” ብሎ ረዥም ምንሽሩን አንግቶ ፡ አምስት ጥይት ብቻ የያዘ አሮጌ ዝናሩን አስተካከለ ።

‘ጥበቃ—ጓዱ’ ላቀውና ሰውየው መኖሪያ ቤታቸው ቢራራቅ ጥቂት ነው ። ጥንት ጀምሮ ይተዋወቃሉ። ሰላምታም ነበራቸው ። ላቀው ‘ጥበቃ ጓድ’ ከሆነ ወዲህ ግን ባህሪይው በመለወጡ ብዙ ሰው ሸሽቶታል ። የታጠቀው መሳሪያ ምላሱን ያረዘመለት ይመስል ማንገት ከጀመረበት ግዜ አንስቶ ነገር ነገር ይለዋል ። መኮሳተር አብዝቷል ። በተለይ ኮፊያውን ደፍቶ በሚንቀሳቀስበት ወቅት በእለት ጠብ የተፋጠጡ ሰዎች ሲያጋጥሙት እንኳ ለመገላገል መሃላቸው ዘሎ የሚገባው ‘ጥብቅ መመሪያ ነው !’ በሚል ማስጠንቀቂያ

ሆኗል ።

“ትከፍላለህ አትከፍልም?” ላቀው አምባረቀበት ።

“መረኝ ነው ያልኩህ ላቀው!” አለና ሰውየው ጉል ቱን ሊስም ጐንበስ ሲል ላቀው ወደኋላ አፈግፍጐ “ጤና አለህ?” አለና አፈጠጠበት ።

“ድሃ ነኝ! የዛሬን እለፈኝ!”

“የምንድሃ? ለአብዮቱ የማይገዛ ድሃ ድሃ አይደለም! ‘ድሃ ሁለት አይነት ነው’ ብሏል ጓድ ጠደቀ ። ‘አንዱ ጭቁን ድሃ ፡... ሌላው ደግሞ ዝም ብሎ ድሃ ።’ ከፈለ ። ጥብቅ መመሪያ ነው...!”

“ዋስ ልጥራልህ ሰርቾ ልክፈልህ?”

“የአብዮቱን ህግ የጣሰ ዋስ አይጠራም!”

“እሬ ተለመነኝ ! ወደ ስራየ ልሂድ!” ሰውየው አይ ኖች እንባ ማቅረር ጀምረዋል ።

“የምን ስራ? ከሁሉም በላይ ለአብዮቱ! ብሏል ወጣት አዛውንቱ ።”

ሰውየው ጭንቅ አለው ። የሚያደርገው ጠፋው ። ምን ቢለው ምህረት ሊያገኝ እንደሚችል ማሰብ ተሳነው ። አምስት ብርን ያክል ነገር ጨክኖ ሊሰጠው አልደፈረም ። የማይለቀው መሆኑንም ተገንዝቧል ። ላቀው ከበየነበት አምስት ብር ቀንሶ ሊከፍለው ወሰነ ።

“ሁለት ብር አለኝ ላቀው!...አንተም ወደህ አይደለም ፡ ታዘህ ነው” አለ በሚያግባባ አነጋገር ።

“የምን ሁለት ብር? ትቀልዳለህ? ጥብቅ መመሪያ ነው! በዚህ ቀልድ የለም! ‘ቀልድ የለም በአብዮቱ’ ያለው ጓድ

ጠደቀ ነው ። ጓድ ጠደቀን አታውቀውም! መመሪያ አትቀበልም ? የቀበሌያችን ሊቀመንበር ጓድ ጠደቀ ዋዛ ሰው አይምሰልህ ! ቀለም ግልብጥ አድርጐ የጠጣ ምሁር ነው! ይሻልሃል ! ዋ! … ጥብቅ መመሪያ በሚጥስ ሰው ላይ እርምጃ እንድንወስድበት አስጠንቅቆናል!”

“እሺ ሶስት ብር ይሁን!” አለ ሰወየው ደንግጦ ። ‘እርምጃ’ የሚባል ቃል ሲሰማ ከመቅጽበት ተሸበረ ።

‘ጥበቃ ጓዱ’ ላቀው ከካርኒው ጥራዝ አንድ ቅጠል ካርኒ ገንጥሎ ወረወረለትና ያነገተውን ረዥም ምንሽር ከትከሻው አውርዶ ላይ ታች ተመለከተው ።

“እረ ስለእግዜር ብለህ…” በፍርሃት የተሸበረው ሰውየ የመጨረሻ እድሉን ሞከረ ።

“ይችን ይወዳል ላቀው !” አለ ላቀው በረዥም ምንሽሩ ሰደፍ ከመሬት ሊደባልቀው እየቃጣው ።

ሰውየው ምንም ማድረግ አልቻለም ። ማንባት በጀመሩ አይኖቹ እየተመለከተው ከሚስጥር ኪሱ ድፍን አምስት ብሯን አወጣና ሰጠው ።

“ካርኒህን ያዝ!” ብሎ የቀደደውን ካርኒ አስጨበጠው። ቀጠለና “ካርኒ ማሰረጃ ስለሆነ መጥፋት የለበትም ። ጥብቅ መመሪያ ነው ። መታወቂያ ወረቀትህን ከኪስህ አትለይ! ቀበሌያችን በዚህ በዚህ እንዲበለጥ አንፈልግም ።… ለዜሮ አንዶች ምሳሌ መሆን አለብን!” ሲል ቀባጥሮ ኮፊያውን ወደ ቅንድቦቹ ዝቅ አደረገና ቁል ቁል ወረደ ።…

ሰውየው አመልካች ጣቱን ሽቅብ ቀስሮና በጉም ወደተሸፈነው ሰማይ አንጋጦ “ኤህ!…” አለ በምሬት ።

“ሃምሳ ሳንቲም መልሺልኝ! ” አለ ላቀው አጉንብሳ የጠላ ጋን ለምታለቀልቀው ሚስቱ ሁለት ብር አውጥቶ እየሰጣት ። “ ቶሎ በይ አትቀላምጅ!” ግስላ ሲጋራውን ልምጥጥ አድርጐ እየላበና እየተኮሳተረባት ።

መሸታ ቤቱ በጠጪ ግጥም ብሏል ። አርሆዋ ድርብ ለገሰ ታቅራራለች ፣ በማሲንቆ እየታጀበች ።

ላቀው እንደገባ ጥግ ያዘና የተቀዳለትን ሁለት መለኪያ ካቲካላ በሁለት ትንፋሽ አጋብቶ አጨበጨበ ። ሴላ ግስላ ሲጋራ ለኩሶ ዙሪያ ገባውን ከቃኘ በኋላ “በልብዮት ጊዜ የለም ትካዜ ! ተቀበይ!” አላት በቁሟ እየተወዛወዘች የምታቀነቅነዋን አርሆ ። ፊቷን ወደሱ መልሳ ፈገግ እያለች ስትጠቅሰው ላቀው በኩራት ኮስተር አለና

“አሥር ሣንቲም ያለው — አያዘረዝርም
ውጊያ የቀመሰ — ሙር አይናገርም

እንደሰት እንጂ — እድሜ ለጠደቀ
ዜሮ ሶስት መብለጡ — በአገር ከታወቀ ።

እህል ውሃ ሞልቶ — ከተረፈ ወጡ
ከዜሮ አንድ ልጆች — ዜሮ ሶስት በለጡ!”

ጠጪው ጭብጨባውን አቀለጠው ። በውስጡ እግሩ ወለሉን ተመተመው ። ላቀው በኩራት ተሞልቶ የካቲካላ መለኪያውን ሲያነሳና ሲያስቀምጥ አመሸ ።…

የሴቲቱ ሮንድ ተረኛ ስለነበር የራሱንና ለአርሆዋ የጋበዛትን የሁለት መለኪያ ካቲካላ ሂሳብ ከፍሎ አፉን

እየጠራረገ ወጣ ፡ ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ላይ ።

አካባቢው በጣም ከብዷል ። በዚያ ድቅድቅ ጨለማ የሚንቀሳቀሱ ቢኖሩ የሌሊቱ ሮንደኞች ብቻ ናቸው ። ሰአት እላፊው ሶስት ሰአት ነው ።

ረዥም ምንሽሩን አቀባበለና አመልካች ጣቱን ቃታው ላይ አሳርፎ ሽቅብ ቁልቁል ማለት ጀመረ ። ከሌሊቱ ተረኛ ጓደኞቹ ጋር መደባለቅ አልፈለገም ። ከሰዓት እላፊ በኋላ ሲዘዋወር ከሚገኝ ሰው ብዙ ነገር ይገኛል ። ስለዚህም 'ጥበቃ ጓዶቹ' በየግል መሰማራትን ይመርጣሉ ፡ ጥቅም ላለመካ ፈል።

ላቀው ሮንድ በሚወጣበት ግዜ ሌላም አመል አለው ። ሴተኛ አዳሪ ቤት ያድራል ። ዞርዞር ሲል ይቆያይና ከአይኑ የገባችለትንና ቀን ያሰባትን ሴተኛ አዳሪ ቤት ይቆረቁራል ። ሴተኛ አዳሪዋ ወንድ የያዘች ቢሆንም ደንታው አይደለም ። ሰውየውን 'ትፈለጋለህ!' በማለት በፈጠራ ወንጀል አስደግ ድጉ ያባርረውና ሴትዬዋን አቅፎ ያድራል ።

ለዛንለቱ ያሰባት ደግሞ ባለጠጅ ቤቷ አማረችን ነበር ። ባለንቅሳታሟና ዘርቦጥቦጥ ያለችው አማረች ልቡን ሰርቃዋ ለች ። እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰአት ድረስ ከተዘዋወረ በኋላ ሳር ቀበሌ አካባቢ ትልቁ የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ አጠገብ ከሚገኘው ጠጅ ቤቷ ሄደ ።

በሯን አንኳኳ ። በቤቷ ውስጥ ሞል ሞል ስትል የነበረችው የፋኖስ መብራት እስከናካቴው እልም አለች ። በሯን ደግሞ እንኳኳ ።

ሳል የሚያስረቀርቀው የወንድ ድምፅ ከወደ ውስጥ

ሲሰማ ላቀው ደረቱን ነፋ ።

"ክፈቱ! አማረች…ሮንድ ነን!" አለና ደጋግሞ አን ኳኳ።

"ምንድነው? ማነህ?" በበሩ ስንጥቅ አሎልቃ ተመለከ ተችው ፡ አማረች ።

"ላቀው ነኝ!… ጓድ ላቀው! ክፈቺ!"

"ለምን?"

"ክፈቺ ማለት ምንድነው?" የተቆጣ መሰለ ። ድምጿን አጠፋች ።

"ትከፍቺያለሽ ክፈቺ! የሚፈለግ ሰው ቤትሽ ውስጥ አለ ።" በረዥም ምንሽሩ አፈ ሙዝ በሩን ደበደበው ።

"እንዴ? በህግ!… እሪ እላለሁ!"

"ክፈቺ ፤ ሰውየው ይፈለጋል!"

"ማንም ሰው የለም!"

"እየደበቅሽው ነው? ጥሩ ! ፀረ አብዮተኛ ነው ብያለሁ.. እሱ አያዋጣሽም!… ጥብቅ መመሪያ ነው!" ብሎ ሲዝት በሩ ብርግድ ብሎ ተከፈተ ።

"እኔ ነኝ ተፈላጊው? ማነው ፀረ አብዮተኛ ?…" እያለ የሚደነፋ አንድ ሰው ሽጉጡን ደግኖ አፈጠጠበት ። የቀበ ሌው ሊቀመንበር 'ጓድ' ፀደቀ ነበር ። ላቀው ኩምሽሽ አለ ።

"ኧረ በስተት ነው…ጥቆማ ደርሶን ነበር! ለዚያ ነው የመጣሁ ። ይቅርታ! " አለ ላቀው እንደተሸማቀቀ ።

ፀደቀ የላቀውን ረዥም ምንሽር መንጭቆ ነጠቀውና ከጀርባው ሽጉጡን ደግኖበት ፊትና ኋላ ሆነው ጥቂት እንደሄዱ "ኧረ ማረኝ … ጓድ ጠደቀ! ሂሴን ውጫለሁ…"

አለ ላቀው በመርበቅበት ።

"ቀጥል!" በሽጉጥ አፈ ሙዝ ጭንቅላቱን አለው ። ፊቱ በደም የተሸፈነው 'ጥበቃ ጓድ' ላቀው መቀጠል አልቻለም ። ተንገዳገደና ዥዋ ብሎ መሬቱ ላይ ተዘረረ ።

"ትነሳለህ አትነሳም?"

መልስ የለም ።

"ተነስ! ሌላ አላማ አለህ ማለት ነው!?" ላቀው አልተንቀሳቀሰም ።...

በአጠገባቸው ማንም አልነበረም ። ፀደቀ ከበላዮቹ ሊመጣበት ከሚችል ጣጣ ለመዳን እየተጣደፈ ሲሮጥ ከሌላ ባለ ዲሞትፎር ' ጥበቃ ጓድ' ጋር ተገናኘ ።

"ምንድነው ጓድ ጠደቀ?" አለው ባለ ዲሞትፈሩ በተጠንቀቅ ቆሞ ።

"ላቀው ተመትቶ ወድቋል ። ግን እንደመታው እንጃ ። ይቺ ነገር ዋ!" አለና እያለከለከ "እኔ ሪፖርት ላደርግ መሄዴ ነው ። አንተ ደጋግፈህ ከቤቱ አድርሰው! ጥብቅ መመሪያ ነው!" ብሎት ፀደቀ ግራ ቀኝ እየተገላመጠ ዋናውን ጉዳና ይዞ ሽቅብ ወጣ ።

ባለ ዲሞትፈሩም 'ጥብቅ መመሪያ' የምትለዋን ሀረግ እያነበነበ በተጠቆመው አቅጣጫ ላቀውን ፍለጋ ሄደ ።...

የ 'ጥብቅ መመሪያ' ው መዘዝ እንደሚጠመጠምበት አልጠረጠረም ።

---

* ሚያዝያ, 1983 መቀሌ

ስጋ ብፃት

ዶፍ እየወረደ ፣ ነጐድጓድም አካባቢውን እያናወጠ ባደረበት የነሐሴ ወር መባቻ ላይ በሀይቅ ግንባር በኩል ቅልጥ ያለ ውጊያ ይካሄዳል ። የቢኤም አስፈሪና አስደንጋጭ ግምግማ ፣ የታንክና የመድፍ ድምድማት ፣ የመትረየስ እሩምታና የክላሽን ካካታ ፣ ይህ ሁሉ ተዳምሮ ምድር ቀውጢ ሆናለች ።

ከሀይቅ ከተማ ወደ ውጫሌ በሚወስደው መንገድ ላይ አምስት ኪሎ ሜትር ያክል ርቃ በምትገኘው ትዓሽ ጅረት አጠገብ ተኩስ ቀልጧል ። ፍልሚያው ተፋፍሟል ። ውጪ ነፍስ ፣ ግቢ ነፍስ ሆኗል ። ሀይወት ያልፋል ። ጣእር ሰፍኗል ።

አፈሙዝ በተኩስ ግሎ ፣ ሳንጃ በደም ተጨማልቆ ፣ ደም እንደጅረት እየተንኳለለ እንደ እርጎ ሲረጋ ፣ በሚንከተከተው ቀው ዶፍ የረጋው ደም እየቀጠነ ብርዝ መስሎ ሲወርድ ፣ ጀግና ወድቆ 'ውሃ ውሃ' ሲል ፣ ጠብታ ውሃ አፉ ላይ የሚያደርግለት አጥቶ እያቃሰተ የሀይወት ክሩ እስክትበጠስ በሲቃ ሲጠባበቅ ፣... የሚታየው የሞት ዋዜማ አስፈሪ ድባብ ሰው ሆኖ መፈጠርን ያስጠላል ።

ከትንሿ ጅረት አጠገብ ባለው ሰፊ ረግረጋማ ቦታ ላይ ያለችው አንዲት ጐፈሬ ወጣት ሌሊቱን በሚወርደው ዶፍ ክፉኛ በስብሳለች ። ክላሽን ብረቷን በደረቷ አቅፋለች ። ሚዛን የሚደፋው የጥይት ትጥቋ በሽንጧ እንደዞረ ነው ። ከሷ አነስ የሚል ወጣት ተሸክማ ረግረጋማውን ቦታ ለማቋረጥ ትዳክራለች ።

በዚያ ድቅድቅ ጨለማ የሚታያት አንድም ነገር የለም። የሚታያት ነገር ቢኖር የከባድና የቀላል መሳሪያ ጥይቶች ለአካባቢው የሚፈጥሩት ውጋገን ብቻ ነው ። ያም ብዙ አይቆይም ። ከገባችበት ረግረግ ተራምዳ እንድትወጣ አልረዳ ትም ።

ሰውነቷ ዝሏል ። ብርክ ይሰማታል ። የምትቀናንሰው ሽክም ስላልነበራት በዛለ አቅሟ ረግረግ ውስጥ ትንከላወሳ ለች ። እስከ ጉልበቷ ድረስ በጭቃ ተውጣለች ። ፕላስቲክ ጫማዎቿን ውጠ ስላስቀረባት የምታዘግመው በባዶ እግሯ ነው ።

የተሸከመችው ወጣት ደግሞ "ው ... ሃ !" እያለ ያቃስታል ። ቁስለኛ ነበር ።

የቆሰለው ትከሻው ላይ ነው ። ብዙ ደም ፈሶታል ። በከባድ ድካም ከመዝለፍለፉም በላይ ቁስሉ እየጠዘጠዘው መሆኖውን አሳጥቶታል ። በምን ሁኔታ ላይ እንዳለም የሚያውቅ አይመስልም ። ጉሮሮው ደርቋል ። እና በተደጋ ጋሚ የተሸከመችውን ወጣት 'ውሃ ! ... ውሃ !' እያለ ያስቸግራታል ።

እግሮቿን አላራምድ ያለው ረግረግ አሸንፎ ሊጥላት ደረሰ ። ጉልበቶቿ ተብረከረኩ ። ብርዱ ፡ ነፋሱ ፡ ዝናቡ ፡ ረሃቡ ፡ ጥማቱ ፡ ድካሙ ተዳምረው ፍፃሜዋን አቀረቡት ።

ተስፋ ግን አልቆረጠችም ። ጥርሷን ነክሳ ግብ ግብ ገጥማለች ። "ውሃ ... ው ... ሃ !" ድክም ባለድምፅ ነበር የተናገረው ፤ ቁስለኛው ።

"እ ... ሽ!"

ከረግረጋማው ቦታ ወጥታ ቀና መንገድ ለመግባት አቅጣጫዋን ለወጠችና በሰያፍ አዘገመች ። የአሁኑ ይሻላል ። ረግረጉ ቀንሷል ። ጥልቀት የለውም ። ጭቃው እንዳያዳል ጣት ብቻ በጥንቃቄ እየረገጠች ጥቂት እንደገፋች አንድ እሾሃማ አጥር ውስጥ ተመሰገች ። ቁስለኛው ስቃዩ በዛበት ። አቃሰተ ። ወደኋላ ስታፈገፍግ ሁሉም ነገር ከአቅሟ በላይ ሆነባት ። ሽክሟን የመቀነስ ግዴታ መጣባት ። ቁስለኛውን ወጣት ቀስ አድርጋ አውርዳ ምድር ላይ አሳረፈችው ። በደረቷ አቅፋው የነበረውን ከላሽን አውርዳ አስቀመጠችው።

ቁስለኛውን ከወገቡ ቀና አድርጋ ጭንቅላቱን ግራ ጭኗ ላይ አሳረፈችለት ። አቡጀዲ ተልትላ ያሰረችለት ትከሻውን ዳበሰችው ። እስሩ ላላ ብሎ ነበር ። አጠበቀችለት ። ወዲያው ድካም ደፋ ቀና ያደርጋት ጀመር ። ከቁጥጥሯ ውጪ በሆነ ኃይል አሸለበች ። ...

ተኩሱ እንደተጋጋለ ነው ። የሚች ቁጥር በሁለቱም ወገን ተበራክቷል ። ከተኩሱ የባሰው ነጮድጓዱ ነበር ። ምድርን ለሁለት የገመሳት የሚመስለው አሸባሪ ድምፁን በተደጋጋሚ ይለቀዋል ።

"እረ ውሃ ! ... ውሃ!" ቁስለኛው ደመ ነፍሱን ተናገረ ። በሽለብታ ላይ ያለችው ወጣት ግን አላደመጠች ውም ። ብታደምጠው አንኳ በዚያ ቅልጥ ባለው የሞትና የሽረት ፍልሚያ ምላሽ የምታገኝለት አልነበረችም ። ዋናው ተግባሯ ቁስለኛውን ህክምና እንዲያገኝ ባለ በሌለ ሃይሏ ተሸክማው ውጫሌ ማድረስ ነው ፤ ተስፋዋ ይኸው ነው ።

አትሙ እንደማይናፈት ብታውቅም ፥ እስከተቻላት ገፍታ በት የሚያግዟት ሀይሎች እንደማታጣ ተማምናለች ።

የወገኖቿ እቅድ አጥቅቶ የመመለስ በመሆኑ ንጋት አካባቢ በሚሰጠው ልዩ የተኩስ ምልክት ከውጊያው ጐራ በሀይወት ማምለጥ የቻሉት ወደ ውጫሌ ይመለሳሉ ። ...

ቁስለኛው የጣር ድምፅ አሰምቶ ሲንፈራገጥ ባነነች ። ጆሮዋን ልቡ ላይ ለጥፋ አዳመጠች ። ልቡ እየዘገየች ድው ... ድው ... ትላለች ። በሕይወትና በሞት መካከል እንደሚገኝ ተገነዘበችና ምን ማድረግ እንዳለባት ማሰብ ጀመረች ።

ስንት ሰአት ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ሞከረች ። አንቅሰቃሴ የተጀመረው ከሌሊቱ ሰባት ሰአት ላይ ነው ። ሰባት ተኩል ላይ ውጊያው ተጀምሯል ። ውጊያው ለሁለት ሰአታት ያክል የተካሄደ ሲሆን አሁን ዘጠኝ ተኩል ከሌሊቱ ሆኗል ማለት ነው ። ለአስር ሰአት ሩብ ጉዳይ ደግሞ መልስ ይሆናል ።

ክላሽኑን አንስታ ደረቷ ላይ አጋደመችው ። ቁስለኛውን ልታነሳው ስትሞክር ፥

"ተይኝ ! አንድ ግዜ ብቻ ... ትንሽ !" አለ ።

"ተው እስቲ አንተ ጓድ ! ቀና በል ባክህ ! ... አግዘኝ እንጂ !" አለችና ተሸክማው ማዝገሚን ቀጠለች ።

ተኩሱ ተጧጡፎ ፥ ከወዲያኛው ወገን የተተኮሰ ቤን ጋል ላይት በፈጠረው ብርሃን አካባቢዋን ቃኘች ። አቅጣጫዋን ስታለች ። ከፍተኛ ድንጋጤ ቢሰማትም ያላትን ሃይል እያሟጠጠች አቅጣጫዋን ወደ ሰሜን አደረገች ።

ጥቂት እንዳዘገመች ደግሞ ቁስለኛው ተንፈራገጠ ። ...

በዚያ ብርዳማ ሌሊት ላብ አሰመጣት ። የተሸከመችውን ወጣት ሞት የሚቀማት መሰላት ። ክፉኛ ሲንፈራገጥባት አወረደችውና መስኩ ላይ በጀርባው አሳረፈችው ።

ለመገነጣ የሚያገለግል አቡጀዲ ጨርቅ ከትጥቋ አወጣችና በሳንጃ እየተለተለች የቁስለኛውን ትከሻ በብብቱ እያዞረች አሰረችለት ።

ቁስለኛው ፀጥ ብሏል ። 'ውሃ !' አይልም ። አያቃስትም። አይንፈራገጥም ።

"ብርሃኑ !" አለችው ሁኔታው አስግቷት ።

ቁስለኛው ትንፋሽ አጥሮታል ። እንደምንም ብሎ በዚያ ድቅድቅ ጨለማ አይኖቹን ከፈተ ። የእሳት ጉማጆች እየተምዘገዘጉ እልም ሲሉ ታዩት ። የእሳት ጉማጆች ሲወረወሩ የሚያሰሙትንም አሸባሪ ድምፅ ሰማ ። ቦግ ! እልም ! ... ሕይወት ! ... ሞት ! ያ ነበር ቅፅበታዊ የጦር ሜዳ ትርኢት ።

ግራ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገና "ማነሽ ?" አላት ።

"እንወይ ነኝ ! በርታ ባክህ ብርሃኑ !" ንግግሯ የልመና ቅላፄ ነበረው ።

"እንወይ !?" አለ ቁስለኛው ንግግሩን ረገጥ አድርጎ ። "ታዲያ እዚህ ምን ታደርጊያለሽ ? ምሽግሽን ለምን ትለቂያለሽ ? እቅድሽን እያፋለስሽ ነሽኮ ! ሂጂና መትረየሴን ያዢው ..." ንግግሩን ድንገት አቋረጠና አንቋረረ ። ወዲያው ደግሞ ጀመረ ። "መትረየሴን ... መትረየሴን ..."

እጁን ጥብቅ አድርጎ ይዟል ። ትንፋሹ ፈጣን ነው ። የልቡ ምትም እንደዚያው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ናረ ።

"እረ ዝም በል! የውጊያ ወረዳ ውስጥ'ኮ ነው ያለነው ..." ወደ ጆሮው ተጠግታ አንሾካሾከችለት ። ያዳመጣት አይመስልም ።

"ልጄን ... የዛሬ ወር ገደማ የሚመጣልኝን እንግዳ ...! ሳላየው ማለፌ ነው'ኮ! ...አዲስ አበባ መቼ ነው የምን ገባው ? ... ልጄ ስሙ ማን መሰለሽ ? ሴት ከሆነች ..."

"አይዞህ ፣ ወንድማለም ! እንዲህ አታስብ ። ... ስጋ ብያት !" የመጨረሻዎቹ ሁለት ቃላት መሀላዋ ናቸው ። በህይወት እንደሚቆይ ያላትን ፅኑ እምነት የገለጠችባቸው ።

ግን አልሆነም ንግግሩን አቋረጠ ። ፀጥ አለ ። ትንፋሹ ጠፋ ። ከሰኮንድ በፊት ህያው ነበር ። ግኡዝ አካል ሆነ ። ቅፅበታዊ ለውጥ ! ...

ደረቱ ላይ ተደፍታ ተንሰቀሰቀች ። እንባ ግን አልነበራትም ። ማዳን ትችል ይመስል እየተስረቀረቀችና ሳግ እየተናነቃት መላ አካሉ ላይ ጆሮዋን እየለጠፈች የሕይወት ምልክት ፈለገች ። ሞት የቀደማት መሆኑን ለማመን ጥቂት ጊዜ አጠፋች ። ...

ሬሳውንም ቢሆን እዚያው ጥላ ላለመሄድ ወስና ካቀረቀረችበት ቀና ስትል አንድ ከቁመናው ዘለግ ያለ ሰው ፊቷ ላይ ተገትሯል ። አስተዋለችው ። ክላሽኗን ለማንሳት ጉንበስ ስትል በጠንካራ እጁ አፈፍ አድርጓት ፣ ፀጉሯን ጨምድዶ ያዘና ከአፎቱ የመዘዘውን አብረቅራቂ ሳንጃ ወደ ጉሮሮዋ አስጠጋው ። ...

ንጋት ላይ የሸሚዛቸውን እጅጌ ወደ ላይ የሰቀሰቁና ጭናቸው ላይ ገመድ የጠመጠሙ ፣ ጠርብ ጠርብ የሚያክሉ

ወታደሮች ይጨፍራሉ ። እንወይ መካከላቸው አለች ።

"ይለያል ይለያል ይለያል
ይለያል ዘንድሮ
የወንበዴ ኑሮ !" ... እያሉ ይዘላሉ ።

እጆቿ የኋሊት ተጠፍረዋል ። ደረቷ ላይ "ሻእቢያ !" የሚል ፅሁፍ የተፃፈበት ካርቶን እንጠልጥለውባታል ። እንወይን መካከላቸው ገትረው ዙሪያዋን እየዞሩ ይዘላሉ ። ይህ ሲበቃቸው ደግሞ እየነዷትና ጮቤ እየረገጡ ፣ "ይለያል ... ይለያል ..." እያሉ ወደ ህይቅ ከተማ ይገሰግሳሉ ።

ከህይቅ ከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው የጦር ግቢያቸው ሲቃረቡ ድምፃቸው በጣም ጮልቶ ይሰማ ጀመር ።

የጦር ግቢው በራፍ ሲደርሱ አንድ የሃምሳ አለቃ እጆቿ የኋሊት ተጠምዘው የታሰሩበትን ገመድ በግራ እጁ ይዞ ፣ በቀኝ እጁ የተቀባበለ ሽጉጡን ጭንቅላቷ ላይ እንደደገነ የግቢውን በር አልፎ ገባ ።

ወደ አንድ ቆርቆሮ በቆንቆሮ ወደተገጣጠመ ክፍል ወሰዳትና በሩን አንኳኩቶ ገባ ።

አንድ የመቶ አለቃ ማእረግ ያደረገ ራሰ በራ ወታደር አቀርቅሮ ይፅፋል ። ምናልባት የሚፅፈው ስለሌሊቱ ውጊያ ዝርዝር መግለጫ ይሆናል ።

"ጌታዬ ! የተማረከች ወንበዴ ናት !" አለ የሃምሳ አለቃው በተጠንቀቅ እንደቆመ ።

"ምን አስቀያሚዋ ናት ባካችሁ !?" አለና ምራቁን ጢቅ አደረገ ። ሰው አልመስል አለችው ፣ ። ሻምበሉ "አስቀምጣት !" አለና በሃምሳ አለቃው ላይ ደነፋ ። የሃምሳ

አለቃው በፀጉሯ ጉትታትና ወንበር ላይ ዘጭ አደረጋት ።

በገመድ የኋሊት ተጠምዘው የተተበተቡት እጆቿ ይጠዘጥዟታል ። ድካም አዝለፍልፏታል ። ለእንድቀን ተኩል ያክል እረፍት ያጡት አይኖቿ ይቆጠቁጧታል ። ረሃብ ይሞረሙራታል ። አልፎ አልፎ ሆዷ ይጮሃል ። አንገቷን ሰብራ ፣ አይኖቿን ወለሉ ላይ ተክላ እንደተቀመጠች "ይለ ያል ... የወያኔ የወንበዴ የሻእቢያ ኑሮ ... ይለያል ዘንድሮ !" የሚል የበርካታ ሰዎች ድምፅ የጆሮዋን ታምቡር ሊበጥሰው ነው ።

"ሂድና አራት ኮማንዶዎች ፣ ሾፌሩንም ጥራ !" አለ ሻምበሉ ። ሃምሳ አለቃው በተጠንቀቅ እንደቆመ ደረቱን ነፋና ትእዛዙን ከተቀበለ በኋላ ወጣ ።

ሻምበሉ ሲጋራውን ሳብ አደረገና እፍኩፍ ... አለባት ፣ በጥላቻ እየተመለከታት ። ዘላ የምትጐበርበት አውሬ መሰለችው ። በዚያች ክፍል ውስጥ ብቻውን ከሷ ጋር መቅረቱ ፍርሃት ፍርሃት አለው ። ሽጉጡን ከማህደሩ አወጣና አቀባብሎ ያዘ ።

"ጡት ነካሽ !" ከንፈሩን ነከሰባት ።

ትጥቃቸውን ያሳመሩ አራት ወታደሮች የሃምሳ አለቃውን ተከትለው ገቡ ፣ ታጣፊ ክላሽናቸውን እንዳነገቱ ።

"ነገውኑ በአስቸኳይ ደሴ ውሰዷትና ለሻምበል ክብረት አስረክቧት !" ብሏቸው ሽጉጡን ወደ ማህደሩ መለሰ ።

ይዘዋት ወጡ ። ...

'ልዩ የምርመራ ክፍል' የሚል ፅሁፍ አናቷ ላይ የተለጠፈባትን ጠባብ ክፍል በር ከፈቱና ወደ ውስጥ

ገፈተሯት ። በሯ ከውጪ ተቆለፈች ።

በክፍሏ ውስጥ የታመቀው ግማት ገና ከርቀት አፍንጫ ይሰረስራል ። ጥግ በኩል የቆመው ጉርድ በርሜል በሰገራና በሽንት ጢም ብሏል ። ግድግዳዎቹ ተባይ ይርመሰመስባቸዋል ። በጣራውና በግድግዳው መጋጠሚያ ላይ መስኮት ተብየ አንዲት ክፍተት አለች ።

እንወይ ገና እንደገባች አጥወለወላት ። ቋቅ አላት ። ግን ከሆዷ የምታስወጣው ነገር አልነበራትም ። አፍንና አፍንጫዋን ለማፈን ሞከረች ። የማይቻል ነገር ሆነባት ። እንቅልፍ ስላንጐላጃት እንደምንም እየዳኸችና እየተንገዳቀቀች ግድግዳውን ለመደገፍ ቻለች ። ሜንቅላቷን አንዴ ወደፊት ፣ አንዴ ወደ ግራ ፣ አንዴ ወደ ቀኝ እያዘነበለች ፣ እንቅልፍ ጸይበልው ፣ ሽልብ አደረጋት ።

በድንገት በሯ ብርግድ ብሎ ሲከፈት አይኖቿን ገለጠቻቸው ። አንድ ሰው ወደሷ ጠጋ አለና አንድ ትልቅ ጣሳ ውሃና ሁለት የደረቁ ዳቦዎች አስቀመጠላት ። ፀጉሯን ጨምድዶ በመጐተት ጥቂት አንፍቀቃትና የታሰረችበትን ገመድ ፈታላት ። ወዲያው እየተጣደፈ አፉንና አፍንጫውን አፍኖ ወጣ ። በሩን ደርግሞባት ከውጪ ቆለፈው ።

በገመድ ተተብትበው የነበሩት እጆቿ አባብጠዋል ። አንዱን እጇን በአንዱ እየዳሰሰች ጥቂት ካስተዋለች በኋላ አስቀድማ የያዘችውን ጣሳ አነሳችው ። ወደ ደረቁት ከንፈሮቿ በቀላሉ ልታቀርበው አልቻለችም ። አብዛኛው በደረቷ ላይ ፈሰሰ ።

የቀረውን ውሃ ሜንቅላቷ ላይ ደፋችውና ጣሳውን ወደ

ጥግ ወረወረችው ። አንዱን ደረቅ ዳቦ አንስታ ተያያዘችው ። ብዙ እያጣጣረችና እያንቋረረች የግድ ጨረሰችው ።

በደረቷ ኀፂ ብላ ተደፍታ ማሰብ ጀመረች ። በዚያን ወቅት ወገኖቿ አንድ ላይ ተሰብስበው የውጊያውን ሂደት ሲገመግሙ ታዩዋት ። "እንወይ የት ቀረች?" የሚል ጥያቄ በድንገት ተነስቶ "ተሰውታለች !" በሚል ድምፅ ሲደመድሙ ታሰባት ። ...

ያለችበት ግቢ ፀጥ ረጭ ብሏል ። አንዳችም ድምፅ አይሰማም ። ዙሪያውን ያሉ ተረኛ ዘቦች የብረት ቆባቸውን ደፍተው ፡ ክላሽናቸውን በረዥም ማንገቻ አንጠልጥለው ፡ አመልካች ጣቶቻቸውን ቃታቸው ላይ እንዳሳረፉ ይንጐራደዳሉ ። አልፎ አልፎ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ይሰማል ።

ሌሊት ዶሮ ሲጮህ ሻምበሉ ሁለት ወታደሮችን አስከትሎ የልዩ ቢሮውን በር ከፈተና ወንበሩን ያዘ ። ከፊት ለፊቱ አንድ መናኛ ጠረጴዛ ይገኛል ። ጠረጴዛው ላይ ደግሞ አንድ አኮርባጅና የተበታተኑ ወረቀቶች አሉ ። ክሯ አልቆባት የምትጨናበሰው ፋኖስ ጭል ጭል እያለች የደበዘዘ ብርሃን ትፈነጥቃለች ።

ሻምበሉ ፓኬት ሲጋራውንና ክብሪቱን ከኪሱ አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ አደረገ ። በረዥሙ አፋሽገና እንቅልፍ ያልጠገቡ አይኖቹን እያጉረጠረጠባቸው "አምጪት !" አላቸው ፡ ወታደሮቹን ።

ሁለት እጆቿን የኋሊት ጠምዘው መደገፊያ የሌለው ወንበር ላይ አስቀመጧትና እነሱ ግድግዳውን ተደግፈው ቆሙ ።

ሻምበሉ ሲጋራውን ለኮሰና ብእር አንስቶ ፡

"ስምሽ ማነው ?" አላት

ዝም ።

"አማርኛ ትሰማለች ለመሆኑ ?" ወታደሮቹን ቀና ብሎ አያቸው ።

"እረ ጌታዬ ሻእቢያ ናት አሉ ! እነሱ ደግሞ አረብኛ ቢሆን ነው ቋንቋቸው ..." ሲል ረዥሙና ቦርጫሙ ወታደር መለሰለት ።

"ስምሽን ንገሪን !" ሻምበሉ ለሶስተኛ ጊዜ ሞከረ ።

"እንወይ ?"

"እድሜሽ ?"

"ሃያ አራት !"

"አገርሽ የት ነው ?"

"ኢትዮጵያዊ አልመስልም ?" አለችው ስልል ባለ ድምፅ ።

"እሱን ተይው !" አለና ሻምበሉ ወታደሮቹን እያየ ፈገግ አለ ። ፈገግታው የለበጣ ነበር ።

"እሺ ያደግሽበት ?"

"ሰቆጣ !"

"ስራሽ ምንድነው ?" አፍጦ ተመለከታት ።

ዝም ።

"ስራሽ ምንድነው ?"

ጭጭ ።

"ግዴለም ! ገንጣይ ልንለው እንችላለን ! ... "

"ተጋዳይ !" አለችው በእልህ እስትንፋስ ።

"ውይ ! ተጋድለሽ ሞተሻል !" አለና ሻምበሉ አፈዘ
ባት ። ረዥሙና ቦርጫሙ ወታደር ፈገግ አለ ፤ ሻምበሉን
ተከትሎ ።

"የሚቀጥለው ወረራችሁ በየት በኩል ነው?" ሲጋራ
ውን ልምጥጥ አድርጉ ሳበና መተርከሻው ላይ አወደማት ።
መልሷን በጉጉት ይጠባበቃል ። ይቺን ጥያቄ በማስረጃ
አስደግፋ ከመለሰችለትና ካስፈረማት የሚጠብቀው ሹመት
ታየው ። በተለይም በዚህ ውጊያ በርካታዎቹ የተቀላጠፈ
ማእረግ አግኝተው ፤ ወር ሳይሞላቸው አዳዲስ መረጃዎች
በማጠናቀር ለአለቆቻቸው እያቀረቡ ለበለጠ ማእረግና ሽል
ማት ሲበቁ እሱ አልቀናውም ። በዚህ ምክንያት አዲስ ነገር
ለማግኘት ሲል የተመርማሪዎቹን የመመለስ አካላዊ ብቃት
እንኳ ግምት ውስጥ ለማስገባት አይፈልግም ። ካልመሰላችሁ
ልኝ ብሎ ደሙ ይፈላል ። በተለይም የተቃዋሚዎቹ የማጥ
ቃት አቅጣጫ ባልተጠበቀ ጊዜና ባልተገመተ አካባቢ
እየመጣ ፤ መንግሥት ሁኔታውን ለመቆጣጠር እንደተቸገረ
ከመከላከያ ሚኒስቴር የተሰራጨው መግለጫ አሳሳቢ ሆኖበ
ታል ። ስለዚህ ለማእረግና ለሹመት የመቋመጡን ያህል
አንገቱንም እንዳይቆረጥ ይሰጋል ።

ተመርማሪዎቹ ውሸታቸውን ቢቀዱለትም ግድ አልነበ
ረውም ። ብቻ የሚያስተላልፈው ነገር ይፈልጋል ። ታዲያ
እንወይ የምትመልስለት አልሆነችም ።

"የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?" ጥያቄውን
ደገመላት ፤ አኮርባጁን እየጠበጠበ ።

መልስ አልሰጠችውም ።

"ተናገሪ!"

ምንም ።

ወታደሮቹን በአይኑ ጠቀሳቸው ።

ረጅሙና ቦርጫሙ ወታደር በርጥበት የተኮማተረውን
የሸሚዟን ክሳድ ጨምድዶ ወደ ላይ አነሳትና ፊቷን በቡጢ
ለጋው ። ሲለቃት ወለሉ ላይ ድፍት አለች ። አንዳች
በሚያካክሉት ጫማዎቹ የተዘረጉ ሁለት እጆቿን ጨፈላለቃ
ቸው ። በጀርባዋ እንድትጋደም አደረጋትና ሆዷን ረገጣት ።
ከተዘረጋችበት ወለል እንደገና አነሳትና በሁለትእጆቹ በጥፊ
አጣደፋት ። ትንፋሽ ለማግኘት ቆም ሲል እሷ ዘሙአለች ።
የዝናብ ውሃ ከተጠራቀመበት በርሜል ባልዲ ሙሉ ቀድቶ
ላይዋ ላይ ቸለሰባት። ውሉን ማወቅ በሚያስችግር ዘዴ ሁለት
እግሮቿን ተበተባቸው ። በሁለት እግሮቿ የውስጥ ክፍሎች
ላይ ዘይት አፈሰሰባቸውና በጋለ ሽቦ ሲዳስሳቸው ተንፈራገ
ጠች ። ክፉኛ ተወራጨች ። የጣእር ድምፅ አሰማች ።

ሻምበሉ ፈገግ እያለ ሌላ ሲጋራ ለኮሰ ። ሁለቱ
ወታደሮች የወሳንሳ አንስተው ወንበር ላይ አስቀመጧት ።

ጭንቅላቷን ጠረጴዛው ላይ አስደገፈች ። ፊቷ ከመትጽ
በት ጥቅርሻ መሰለ ። የታሰሩት እጆቿ ብቻ ሳይሆኑ የጋለ ሽቦ
የዳሰሳቸው እግሮቿም ጠዘጠዟት ። በልቧ ሞትን ተመኘች ።
እሱም ቢሆን ሲፈልጉት ቶሎ የማይገኝ ሆነባትና የሞት
ጥማት ያዛት ።

"ይህ በጣም ቀላሉ እርምጃችን ነው ፤ አይግረምሽ!"
ሻምበሉ አሁንም አኮርባጁን ጠረጴዛው ላይ ይጠበጥባል ።
"ይልቅ ፍጠኝ! የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?"

መልስ ባለማግኘቱ የተናደደው ሻምበል ከፓኬቱ ሌላ ሲጋራ አውጥቶ ለኮሰና የማነውን ጢስ ወደ አይኖቿ እፍፍፍ… እያለ “እሺ ይህ ይቆይልን! በየትኛው ድርጅት ውስጥ ነበርሽ? አላት ።

“ኢህዴን!” አለችው ወኔ በሳለው አንደበት ።

“ከመቼ ጀምረሽ ወንበዴ ሆንሽ?”

“ወንበዴ አይደለሁም! ታጋይ ነኝ ። ወደ ትግል መስክ የገባሁትም በ82 ዓመተ ምህረት ነው ። የዋለለኝ ሬጂመንት አባል ነኝ!”

“የዋለለኝም በይው የሳዳም ሁሴን ፡ የንጉስ ፋአድም ይሁን የአንዋር ሳዳት ሬጅመንት ፡ ቡድናችሁ ያው ዞሮ ዞሮ ወያኔ ሻእቢያ ማለት አይደለም?”

“አይደለም!” ቀሪው አቅሟን መልስ ልትሰጥበት ቆርጣለች ።

“የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?” የጐሪጥ ተመለከታት።

“አላውቅም!”

“ለምን አታውቂም?”

“አላውቅም!”

ሻምበሉ ከመቀመጫው ብድግ አለና በያዘው አኮርባጅ ጀርባዋን ተለተላት ፡ ክንዱ እስኪዝል ድረስ ።…

“አትናገሪም?” በላብ የተዋለቀለቀውን ግንባሩን እየጠረገ ።

“ባልናገርስ!?” አይኖቿ እምባ አቅረዋል ።

“ባትናገሪማ ውሃ የሞላ በርሜል ውስጥ እንዘፍቅሻ

ለን። ከዚያ አውጥተን ደግሞ በአፍሽ የገማ ካልሲ ጎርሰሽ በዚህ አለንጋ ፍዳሽን ትቆጥሪያለሽ ፡ ወያኔ ውስጥ የገባሽበትን እለት እስክትረግሚ ድረስ!”

“ከዚያስ!?”

“ከዚያ በኋላማ ባስለታም ሳንጃ ይህ ገንጣይና አስገንጣይ ምላስሽ ይቆረጥና አንድ አይንሽ ተወግቶ ይፈስሳል ። ቀጥሎም እጆችሽ የኋሊት ተጠምዘው ሕዝብ ተሰብስቦ ‘ወያኔ ሌባ! ወያኔ ገንጣይ!’ እያለ እያጨበጨበብሽ ከተማውን ስትዞሪ ውለሽ ፡ በዛገ ምላጭ ይህን ቅጫማም ጐፈሬሽን ተላጭተሽ መቀመቅ ትወርጃለሽ!”

“አዲስ ነገር አልሰማሁም ። አድራጎታችሁ ይኸው እንደሆነም አላጣሁትም ። ማሳረጊያችሁ ዞሮ ዞሮ ያው ሞት ነው ፡ አይደል!”

አስፈሪ ዛቻው በአእምሮዋ እንዲቀረጽና ከዚያ ለመዳን እንድትዘጋጅ ለማድረግ ሻምበሉ ሌላ ነገር ሳይጨምር ክብሪቱንና ፓኬት ሲጋራውን ይዞ ወጣ ።

ቀጭኑና አጭሩ ወታደር እንደተደበተ ወደ መኝታው ሄደ ። ረዥሙና ቦርጫሙ ወታደር ሻምበሉን ተከትሎ ወጥቶ መኝታ ክፍሉ ድረስ ካጀበው በኋላ ፡ ሻምበሉ ገብቶ መብራቱን አጠፋ ። ቦርጫሙ ወታደርም ወደ ተመርማሪዋ ክፍል ተመለሰ ።

ፋኖቧ ጭል ጭል እያለች የተጨናበሰ ብርሃን መስጠቷን አላቆመችም ። ወደ እንወይ ተጠጋ ። ጐትቶ አስቆማት ። ለአንድ ሳምንት ያክል ከገላዋ ተጣብቆ ያልተለያትን ፡ በጭቃና በዝናብ የላሸቀ ሱሪዋን ማውለቅ ጀመረ ። ያባበሱት

እጆቿ ፈርጣማ ክንዶቹን መቋቋም እንደማይችሉ አውቋል ። ያስቸገረው ከሰውነቷ ጋር የተጣበቀው ሱሪዋ ነበርና ሳንጃውን ከአፍቱ መዝዞ ከላይ ጠርዙ እስከ ጉልበቷ ድረስ ተረተረው ። ሳንጃውን ወደ ቦታው መልሶ የራሱን ሱሪ ዝቅ አደረገ ። ባለ በሌላ ኃይሏ ተከላከለችው ። አልቻለችም ። ለመጮህ አፍን ከፈተች ። በአንድ እጁ ጥርቅም አድርጉ አፈነባት ። ስልምልም አለችበት ። የሞተች መስሎት ለቀቃት ። ትውከቷን ወለሉ ላይ ለቀቀችው ። ሀሞት ደፈቃት ። ...ንጭራት ። ያልተሳካለት ቦርጫሙ ወታደር ሱሪውን እየታጠቀ ወጣ ።

ይህን ዘግናኝ አድራጐቱን ብስርቆሽ ሲታዘብ የቆየው አጭሩና ቀጭኑ ወታደር በሳንጃው ተቀበለው ። ሬሳውን ጐትቶ አሳቻ ቦታ ወተፈና ጠባቂ መስሎ እንወይ በር ላይ አደፈጠ ።

እኩለ ሌሊት ላይ ምሬትና ብሶት እያንሰፈሰፋት ስብርብር ባለና በደከመ ድምፅ እንወይ ማዜም ጀመረች ፣ ትንፋሿ ተመልሶላት በሕይወት መኖሯን ስትገነዘብ ።

"የትላንቱን አልፈን — ዛሬም እንደገና ሌላ ቢከተለን
እንደ ልማዳችን — ንፁሕ ደም ገብረን እንወጣዋለን!
ችግርና ቀውጢ ወትሮም አንድ ላይ ነው
ቀውጢን አልፎ መቆም የታጋይ ፀጋ ነው!..."

ሌላ ዜማ ደግሞ ጀመረች ፣ በረሀ ውስጥ በምትማስንበት ወቅት የምትደጋግማቸውን ስንኞች እየደረደረች ።

"የከፋ የከረፋ—መአት ይውረድብን ፣
ልክ የለሽ መከራ—እንቅፋት ይግጠመን ፣

ደፋሽስቶች ነዲድ—ነበልባል ይግረፈን ፣
ክልሱ እምነታቸው—ውሸት ያናፋብን ፣
በትግል በእምቢታ—በአመፅ እንጠራለን!..."

አስራ አንድ ሰአት ላይ ሻምበሉ አጭሩንና ቀጭኑን ወታደር አልፎ በሯን በርግዶ ገባ ። "ሻእቢያ ያስማገሽ ሀቺቼ የሚጭርልሽ የእብሪት ስሜት ገና አልበረደልሽም?" አላት ። ጥርሶቹን ነክሰባት በንዴት እየተርገፈገፈ ።

"የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?" ንዝንዙን ቀጠለ ። ጭንቅላቱ ግሏል ። ፊቱ ተኮሳትሯል ። ጣቶቹን ይጨብጣል ፣ ይዘረጋል ። አይኖቹ ግሽርጥ መስለዋል ።

"ትናገሪያለሽ አትናገሪም?"

"ምን ልናገር?" አለችው የሞት ሞቷን ።

"የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?"

"አላውቅም!"

"አትናገሪም?"

"ምን ብየ?"

"ተናገሪ!"

"እናቸንፋለን!" አለችው ግራ ክንዷን ሽቅብ እየወረወረች ። ጭኑ ላይ አንጠልጥሎት የነበረውን ሳንጃ ከአፍቱ መዘዘና አንገቷ ላይ ሰካው ። መዘዘና ግራ ጡቷ ላይ ... ሽንጯ ላይ ... በደም አበላ የተነከረውን ሳንጃ ከግራ ሽንጯ መሐል መሐል አናቷ ላይ ተከለው ።...

አካባቢው ጭር እንዳለ ነው ። ሌሊቱ የሚዉለውሉ ሊነጋጋ ሲል ነው እንዲሉ ድቅድቁ ጨለማ የበለጠ ከብዷል። ከርቀት የጥይት ድምፅ ይሰማል ።

ሻምበሉ ያላበውን ማጅራቱንና ግንባሩን በመሀረብ እየጠራረገ በጉራ ተሞልቶ በመንጐራደድ ላይ ሳለ ሳያስበው ሳንጃ ከነእጁታው ከበስተጀርባው ተቀበቀበበትና ባፍጢሙ ተደፍቶ ፀጥ አለ ።

ተጭኑና አጭሩ ወታደር ከእንጀቱ የሚገነፍልበት ሀቃታውን ለማፈን ቢታገልም ጉንጮቹ በእንባው ራሱ ። ጭል ጭል የምትለዋ ፋኖስ በምትሰጠው የደበዘዘ ብርሃን በደም የጨቀየውን ወለልና በጀርባዋ የተንጋለለችውን ወጣት አየ ። በእልህ ሲቃ ተቅበጠበጠ ።

ለመጨረሻ ግዜ ትክ ብሎ ተመለከታትና መሳሪያውን እንዳነገተ ከግቢው ወጣ ። አልተመለሰም ። ፀጉሩን አንጨ ፍሮ ፡ ኮንጐ ጫማ አጥልቆና ፡ ሽጥ ታጥቆ ፡ ከ"ሚያዝያው የዋለለኝ ማእበልተኞች" ጋር ሰልፉን አስተካክሎ ደሴ ላይ ብቅ እስካለበት ጊዜ ድረስ የት እንደገባ የገመተ ማንም አልነበረም ።

ከ73 — 83 ዓ.ም.
'ለቀውጢ ቀን ኮከብ!'

ሞት ይርሳኝና ዘንግቻት የነበረውን የእድሜ ድባ ቤን ፣ የህይወት ርካቤን ፣ ያቺን ጐስቋላ ዛኒጋባየን ነው 'ሰውና ሰው' ያስታወሰችኝ ። የኑሮን ዝብርቅርቅ ፣ የአልሞት ባይተጋዳይን ትንቅንቅ አሳየችኝ ። 'ሰውና ሰው' ነፍሴን በትዝታ አንጥራ··· የነገ እይታየንም አጥ ርታ ፀንቶ መቅናትን ያስተማረችኝ ውብ ፅሁፍ ናት ።

ወጣቱ ደራሲ ፀሀዬ መሰለ እደግ — ተመንደግ የሚያሰኝ ስራ አበርክቷል ። ማንም አንባቢ "ሰውና ሰው'ን በደምብ ያጣጥማታል··· ይማርባታል ።

ሚሲግ ሚካኤል

ዋጋው ብር 5·75

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ